# ታሪክና ምሳሌ

## ፩ኛ መጽሐፍ

ከበደ ሚካኤል

## ፊደል

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሱ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ኰ | ኵ | ኲ | ኳ | ኴ |
| ጐ | ጕ | ጒ | ጓ | ጔ |
| ቈ | ቍ | ቊ | ቋ | ቌ |
| ኈ | ኍ | ኊ | ኋ | ኌ |

፩ ፪ ፫ ፬ ፭ ፮ ፯ ፰ ፱ ፲
፳ ፴ ፵ ፶ ፷ ፸ ፹ ፺ ፻ ፼

964

# ታሪክና ምሳሌ

## ፩ኛ መጽሐፍ

ከከበደ ሚካኤል

© ሜጋ አሳታሚና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር 1999

☎ 011-5-52 14 64
011-1-23 29 05
011-1-23 29 06
011-1-57 44 84

✉ 9144
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ሁለተኛ እትም 1999 ዓ.ም
የመጀመሪያ እትም

| ቁጥር | የአርስት ማውጫ | ገጽ |
|---|---|---|
| ፳፫ | እጅግም ስለት ይቀዳል አፎት | ፴ |
| ፳፬ | ጅጌ ፈፃና ጸመና | ፴፫ |
| ፳፭ | በአንድ ባለጠጋ በረት የሆነ ሁከት | ፴፬ |
| ፳፮ | የክፉ ሰው ስሙ ሁልጊዜ መጥፎ ነው | ፴፭ |
| ፳፯ | አንድ ፈላስፋ | ፴፮ |
| ፳፰ | ፋኖስና ብርጭቆ | ፵ |
| ፳፱ | ሾልቴር | ፵፩ |
| ፴ | አዝማሪና የውሃ ሙላት | ፵፩ |
| ፴፩ | እሮሮ | ፵፫ |
| ፴፪ | ሰነፍ ይከሥራል ሠራተኛ ይከብራል | ፶ |
| ፴፫ | ክፉ ሰው | ፶፫ |
| ፴፬ | የሠራተኞች ዋጋ | ፶፬ |
| ፴፭ | አስተዋይ ተማሪ | ፶፭ |
| ፴፮ | ፈሪ ጦረኛ | ፶፮ |
| ፴፯ | ሞት ሁሉን እኩል ያደርጋል | ፶፯ |
| ፴፰ | ሰው ለመሆን ብትፈልግ | ፶፰ |
| ፴፱ | አንድ ሰውና አንድ ዝንጀሮ | ፷ |
| ፵ | የፈላስፎች ንግግር | ፷፪ |
| ፵፩ | የሰው እንቢተኛነት | ፷፬ |

## አ ገ ር ።

አገር ፡ በታሪክ ፡ በቋንቋ ፡ በሃይማኖት ፡ በልማድ ፡ በተስፋ ፡ በደስታና ፡ በመከራ ፡ ተሳስሮ ፡ የሚኖር ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ ሕዝብ ፡ የሚኖርበት ፡ የዓለም ፡ ክፍል ፡ ነው ።

አገር ፡ ማለት ፡ አያት ፡ ቅድም ፡ አያት ፡ የተወለዱበት ፤ አድገውም ፡ በጀግንነት ፡ ከውጪ ፡ ጠላት ፡ እየተከላከሉ ፡ ለሕዝብና ፡ ለመንግሥት ፡ የሚጠቅም ፡ ሥራ ፡ ሠርተው ፡ ዕድሜያቸው ፡ ሲደርስም ፡ ልጆቻቸውን ፡ ተክተው ፡ የተቀበሩበት ፡ ጕድጓድ ፡ ነው ።

በመወለድ ፡ እትብት ፤ በመሞት ፡ አካል ፡ ከአፈሩ ፡ ጋራ ፡ ስለሚዋሐድ ፡ የአገሩ ፡ አፈር ፡ ሕዝቡ ፡ በላዩ ፡ የሚኖሩበት ፡ ማለት ፡ ነው ።

እግዚአብሔር ፡ ከምድሯ ፡ ፍሬ ፡ ሕይወት ፡ እንዲገኝባት ፡ በማድረጉ ፡ አገር ፡ እያጠባች ፡ የምታሳድግ ፤ ፍቅሯ ፡ በአጥንት ፡ በሥጋ ፡ ገብቶ ፡ የማይደመሰስ ፡ የሆነች ፡ እናት ፡ ማለት ፡ ነው ።

ከልጅነት ፡ ጀምሮ ፡ ወንዙን ፡ ተራራውን ፡ ሜዳውን ፡ ቆላውንና ፡ ደጋውን ፡ በማየት ፡ ስለ ፡ ማደግ ፤ አባቶች ፡ በሕይወትና ፡ በሞት ፡ የሠሩበት ፡ ደግ ፡ ሥራ ፡ በአእምሮ ፡ ታትሞ ፡ ስለቀረ ፡ በአገር ፡ እስካሉ ፡ ሲታይ ፤ በስደት ፡ ሲሆኑ ፡ ሲታሰብ ፤ ፍቅርና ፡ ናፍቆት ፡ የሚያሳድር ፡ አገር ፡ ነው ።

አገር ፡ አባት ፡ እናት ፡ ዘመድ ፡ ምግብ ፡ ጌጥና ፡ ሀብት ፡ በመሆኑ ፡ ድኽነትና ፡ ጥቃት ፡ በመጣ ፡ ቍጥር ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ እንዲሠራበት ፡ ከአያት ፡ ከቅድም ፡ አያትና ፡ ከአባቶች ፡ በጥብቅ ፡ አደራ ፡ የተሰጠ ፡ ገንዘብ ፡ ነው ።

* * *

## ሕ ዝ ብ ።

ሕዝብ ፡ በአንድ ፡ አገር ፡ በአንድ ፡ መንግሥት ፡ በአንድ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ በአንድ ፡ ሕግ ፡ ጥላ ፡ ተሰብስበው ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ማለት ፡ ነው ።

አንድ ፡ ሕዝብ ፡ በትውልድ ፡ በቋንቋና ፡ በሃይማኖት ፡ መገናኘት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ ባለፈው ፡ ኑሮው ፡ ደስታና ፡ መከራን ፡ በአንድነት ፡ የተካፈለ ፤ በአስተዳደሩም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ የተሳሰረ ፤ ለወደፊትም ፡ እሠራዋለሁ ፡ በሚለውና ፡ ስለ ፡ አገሩና ፡ ስለ ፡ መንግሥቱ ፡ ያለው ፡ ተስፋ ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ ማለት ፡ ነው ።

## ሰንደቅ ፡ ዓላማ ።

ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ የነጻነት ፡ ምልክት ፡ የአንድ ፡ ሕዝብ ፡ ማተብ ፤ የኅብረት ፡ ማሰሪያ ፡ ጥብቅ ፡ ሐረግ ፡ ነው ።

« ተመልከት ፡ ዓላማህን ፡
ተከተል ፡ አለቃህን ። »

ነጋሪቱ ፡ እየተጐሰመ ፤ ሠራዊቱ ፡ እየተመመ ፡ ሲሄድ ፤ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ትእምርተ ፡ ኀይል ፡ ትእምርተ ፡ መዊዕ ፡ ነው ።

ሰንደቅ ፡ ዓላማችን ፡ አረንጓዴ ፤ ብጫና ፡ ቀይ ፡ ሦስት ፡ ቀለማት ፡ ናቸው ። ምሳሌያቸውም ፡ አረንጓዴው ፡ ተስፋ ፤ ልምላሜና ፡ ሀብት ። ብጫው ፡ ሃይማኖት ፤ አበባና ፡ ፍሬ ። ቀዩ ፡ ፍቅር ፤ መሥዋዕትነትና ፡ ጀግንነት ፡ ነው ።

* * *



እኛ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በግድ ፡ ልንከተለውና ፡ ልንፈጽመው ፡ የሚገባን ፡ ዐሳብ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።

አንደኛ፣ ኢትዮጵያዊ የሆንህ ሰው ሁሉ ሰንደቅ ዓላማህ አገርህና ነጻነትህ የሚጠቁበትን ነገር ለማስወገድ፣ ወይም ደግሞ እነሱ የሚጠቀሙበትን ሥራ ለመፈጸም ብለህ በሞትህ ጊዜ በሰማይና በምድር ስምህ በወርቅ ቀለም የሚጻፍበትን የሰማዕትነት ሥራ መስራትህን ልብህ ተረድቶት ደስ ይበለው።

ሁለተኛ ፤ —አገርን ፡ መውደድ ፡ ማለት ፡ አገርህ ፡ የምትጠቀምበትንና ፡ የምትከበርበትን ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ነው ።

ሦስተኛ ፤ —አገርህንና ፡ ወገንህን ፡ የሚያስንቅ ፡ ወይም ፡ የሚጎዳ ፡ ሥራ ፡ ከመሥራት ፡ መሞት ፡ ይሻልኻል ።

አራተኛ ፤— እኛ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የምንሠራው ፡ ሥራ ፡ መልካም ፡ ቢሆን ፡ አገራችን ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንደምትከበር ፤ የምንሠራው ፡ ሥራ ፡ መጥፎ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ እንደምትዋረድ ፡ አትርሳ ።

አምስተኛ ፤— ኢትዮጵያ ፡ አገርህ ፡ ከሌሎቹ ፡ ከማንኛዎቹም ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ የምትበልጥብህ ፡ መሆንዋ ፡ ቀንም ፡ ሆነ ፡ ሌሊት ፡ በዐሳብህ ፡ ውስጥ ፡ ሳይረሳና ፡ ሳይዘነጋ ፡ ተጽፎ ፡ ይኑር ።

ስድስተኛ ፤— ማንኛውም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ለተወለደባት ፡ አገሩ ፡ የሚያስብላት ፡ መልካም ፡ ዐሳብ ፤ ወይም ፡ የሠራላት ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ ሲነገር ፡ በሰማህ ፤ ወይም ፡ ተጽፎ ፡ ባየህ ፡ ጊዜ ፤ አንተም ፡ ደግሞ ፡ እንደዚሁ ፡ ይህንኑ ፡ ያህል ፡ ላገርህ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ልታስብላትና ፡ ልትሠራላት ፡ የሚገባህ ፡ መሆኑን ፡ ዕወቀው ።

ሰባተኛ ፤— አንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሲበደልና ፡ ሲጠቃ ፡ ባየህ ፡ ጊዜ ፡ የተበደለችውና ፡ የተጠቃችው ፡ እናትህ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መሆንዋን ፡ ተረዳው ።

ስምንተኛ ፤— ኢትዮጵያ ፡ አገርህ ፡ በእውነት ፡ ትልቅ ፡ ሳትሆንና ፡ ወንድሞችህም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሁሉ ፡ ሳይደላቸው ፡ አንተ ፡ ብቻህን ፡

የምታገኘው ፡ ደስታ ፡ ገንዘብና ፡ ተድላ ፡ በሕልም ፡ እንደ፡ተገኘ፡ ወርቅ ፡ መና ፡ ባዶ ፡ ሆኖ ፡ የሚቀር ፡ መሆኑን ፡ ልብህ ፡ አይዘንጋው ።

<u>ዘጠነኛ</u> ፤— ብዙ ፡ ገንዘብና ፡ ብዙ ፡ ርስት ፡ ከማግኘት ፡ ይልቅ ፡ ለአገሩ ፡ ትልቅ ፡ ሥራ ፡ የሠራላት ፡ ሰው ፡ ስሙ ፡ ለዘለዓለም ፡ በታሪክ ፡ ሲጠራ ፡ ይኖራል ።

<u>ዐሥረኛ</u> ፤— ሌሎቹ ፡ የዓለም ፡ ነገሥታት ፡ ከደረሱበት ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ አገራችን ፡ ኢትዮጵያ ፡ በቶሎ ፡ እንድትደርስ ፡ እኛ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሁሉ ፡ ማሰብና ፡ መጣጣር ፡ ይገባናል ። ድካማችንና ፡ ትጋታችንም ፡ በተለየ ፡ ለዚሁ ፡ ዐሳብ ፡ ብቻ ፡ እንዲሆን ፡ ያስፈልጋል ።

በአንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ አምስት፡ ቀኖች፡ አሉ ። በአራት ፡ ዓመት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ስድስት ፡ ቀኖች ፡ ይሆናሉ ። ይኸውም ፡ የሚሆነው ፡ ጳጉሜ ፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ በምትውልበት ፡ ዘመን ፡ ነው ።

በአንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ወሮች፡ አሉ ። እነሱም፡ መስከረም ፡ ጥቅምት ፤ ኅዳር ፤ ታኅሣሥ ፤ ጥር ፤ የካቲት ፤ መጋቢት ፤ ሚያዝያ ፤ ግንቦት ፤ ሰኔ ፤ ሐምሌ ፤ ነሐሴ ፡ ናቸው ። በመጨረሻም ፡ በሦስቱ ፡ ዓመት ፡ አምስት ፡ ቀን ፤ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ የምትውል ፡ ጳጉሜ ፡ አለች ።

ዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ወሮች ፡ በያንዳንዳቸው ፡ ውስጥ ፡ ሠላሳ ፡ ቀኖች ፡ አሏቸው ።

በአንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ዐምሳ ፡ ሁለት ፡ ሳምንቶች ፡ አሉ ። በአንድ ፡ ሳምንት ፡ ውስጥ ፡ ሰባት ፡ ቀኖች ፡ አሉ ። እነሱም ፡ ሰኞ ፤ ማክሰኞ ፡ ረቡዕ ፤ ኀሙስ ፤ ዐርብ ፤ ቅዳሜ ፤ እሑድ ፡ ናቸው ።

በአንድ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ሐያ ፡ አራት ፡ ሰዓቶች ፡ አሉ ። በአንድ ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ ስድሳ ፡ ደቂቃዎች ፡ አሉ ።

የዓመቱ ፡ ወሮች ፡ በአራት ፡ ክፍል ፡ ይከፈላሉ ። እነዚህ ፡ አራቱ ፡ የዓመት ፡ ክፍሎች ፤ ጥቢ ፡ በጋ ፡ በልግ ፡ ክረምት ፡ ናቸው ።

*



እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ የጥበብ ፡ ሁሉ ፡ መጀመሪያ ፡ ነው ።

*

ከማዘዝ ፡ በፊት ፡ አስቀድሞ ፡ መታዘዝን ፡ ማወቅ ፡ ያስፈልጋል ።

*

ጥሩም፡ ነገር ፡ ቢሆን ፡ ከመጠን ፡ ካለፈ ፡ ሁል፡ጊዜም ፡ መጥፎ ፡ ነው ።

*

ትዕቢትና፡ ውርደት ፡ አካልና ፡ ጥላ ፡ ናቸው ። ሳይለያዩ ፡ ሁል፡ጊዜ፡ ቀዳሚና ፡ ተከታይ ፡ ሆነው ፡ ተያይዘው ፡ ሲሄዱ ፡ ይኖራሉ ።

*

እህልና ፡ ውሃ ፡ ሰውነትን ፡ እንደሚመግቡት ፡ ሁሉ ፡ መጻሕፍትን፡ ማንበብም ፡ እንደዚሁ ፡ መንፈስን ፡ ይመግበዋል ።

*

ከበላይህ ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ እያየህ ፡ በልብህ ፡ ቅናት ፡ አይደርብህ። ይልቅስ ፡ ካንተ ፡ በታች ፡ ያሉትን ፡ ችግረኞች ፡ እየተመለከትህ ፡ ዕድልህ ፡ ከነሱ ፡ የተሻለ ፡ በመሆኑ ፡ ፈጣሪህን ፡ አመስግነው ።

*

ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ መከራ ፡ ወድቆበት ፡ ባየህ ፡ ጊዜ ፡ አትፍረድበት ። ወይም ፡ አትጨክንበት ። በእሱ ፡ ላይ ፡ የደረሰ ፡ መከራ ፡ ምናልባት ፡ ባንተም ፡ ላይ ፡ ወደፊት ፡ ሳይደርስብህ ፡ አይቀርም ፡ ይሆናል ።

*

ምንም ፡ እንኳን ፡ የሚያስመሰግንህ ፡ ትልቅ ፡ ሥራ ፡ ብትሠራ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ አትመካበት ። ትምክሕት ፡ ማንኛውንም ፡ ዋጋ ፡ ቢሆን ፡ ያቀሰዋል ፤ ትሕትና ፡ ግን ፡ ከሁሉ ፡ ሞያ ፡ የበለጠ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ባሕርይ ፡ ነው ።

*

ሰው ፡ በሕይወቱ ፡ ሲኖር ፡ የሚያገኘውን ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የሚቀበለው ፡ ከተወለደባት ፡ አገር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ አስፈላጊ ፡ ምክንያት ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ያለውን ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ሕይወቱን ፡ እንኳን ፡ ሳይቀር ፡ ሳያመነታ ፡ ላገሩ ፡ ሲል ፡ ሊሠዋ ፡ ይገባዋል ።

*

የፈረንሳዊ ፡ ተወላጅ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ዐዋቂ ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ቃል፡ ለሰው ፡ የተሰጠው ፡ ዐሳቡን ፡ ሊገልጥበት ፡ ነው ፡ ይባላል ። ይህ ፡ ግን ፡ ሐሰት ፡ ነው ፤ ቃልስ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ የተሰጠው ፡ ዐሳቡን ፡ እንዲሸፍንበት ፡ ነው ።

*

አንድ ፡ ትልቅ ፡ ሊቅ ፡ ስለ ፡ ስንፍና ፡ መጥፎነት ፡ ሲናገር ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ ጥፋት ፡ ያጠፋ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይቅርታ ፡ ቢደረግለት ፡ የተገባ ፡ ነው ። ምሕረት ፡ ሊደረግለት ፡ የማይገባው ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ አለ ፤ እሱም ፡ ሰነፍ ፡ ሰው ፡ ነው ።

*

ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ሲነገር ፡ የሚኖር ፡ አንድ ፡ የላቲን ፡ ተረት ፡ እንዲህ ፡ ይላል ። ጦርነት ፡ እንዳይመጣብህ ፡ ብትፈልግ ፡ ሁልጊዜ ፡ ለጦርነት ፡ የተሰናዳህ ፡ ሆነህ ፡ መቀመጥ ፡ ይገባሀል ።

*

በጌታና ፡ በድኻ ፡ ሰው ፡ መካከል ፡ የሚገኘው ፡ ልዩነት ፡ በጣም ፡ የተራራቀ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ጌትነትና ፡ ድኽነት ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ሲሄዱ ፡ ይኖራሉ ።

*

ፀሓይ ፡ ጡዋት ፡ ጡዋት ፡ የምትወጣው ፡ የሱን ፡ ድምጥ ፡ ሰምታ ፡ እየመሰለው ፡ በልቡ ፡ ሲኰራ ፡ የሚኖር ፡ አንዳንድ ፡ አውራ ፡ ዶሮ ፡ አለ ፡ ይባላል ። በሕዝብም ፡ መካከል ፡ እንደዚሁ ፡ ሊሠሩት ፡ የማይችሉትን ፡ ትልቅ ፡ ሥራ ፡ የሠሩት ፡ እየመሰላቸው ፡ በከንቱ ፡ ሲመኩ ፡ የሚታዩ ፡ ሰዎች ፡ ይገኛሉ ።

*

ምቀኛ ፡ ሰው ፡ የክፋቱ ፡ ብዛት ፡ የሞቱ ፡ ሰዓት ፡ በደረሰች ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ ከሞትኩኝ ፡ በኋላ ፡ ዓለም ፡ ጨለማ ፡ ሁና ፡ ትቅር ፡ ብሎ ፡ በማሰብ ፡ የሚቻለው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ፀሓይን ፡ አጥፍቶዋት ፡ ለመሞት ፡ በወደደ ፡ ነበር ። ቅን ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ለዓለም ፡ የሚጠቅም ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ሲል ፡ ሕይወቱን ፡ ይሠዋል ።

*



የሰው: ሙያ: ሦስት: ዐይነት: ነው:: አንደኛው: ማሰብን: ማወቅ፤ሁለተኛው: መናገርን: ማወቅ፤ሦስተኛው: መሥራትን:ማወቅ፤ አብዛኞቹ: ብልኆች: የሚባሉ: ሰዎች: ከእነዚህ: ከሦስቱ: አንደኛውን: ብቻ: ነው: የሚይዙ: ወይም: መሥራት: ያውቁና: ትክክል: ማሰብ: አይችሉም: ይሆናል:: ስለዚህ: ትክክል: ካለማሰባቸው: የተነሣ: ደክመው: የሠሩት: ሥራ: ሁሉ: ይፈርሳል:: ወይም: ደግሞ: ንግግር: አሳማሪዎች: ዐሳባቸውና: ሥራቸው: ብላሽ: ይሆናል:: ትክክል: ዐስቦ: ያሰበውን: ትክክል: አድርጎ: በቃል፤ ወይም: በጽሕፈት: አስረድቶ: እንዳሰበውና: እንደተናገረውም: አድርጎ: ትክክል: የሚሠራ: ሰው: እውነት: ትልቅ: ዐዋቂ: ነው: ሊባል: ይቻላል::

*

ደስታ: ምንድን: ነው: ብለው: ቢጠይቁት: አንዱ: ሊቅ: ደስታ+ ማለት: ጤንነት: ነው: ብሎ ተናገረ:: ጤንነትሳ: ደግሞ: ምንድን: ነው: ብለው: መልሰው: ቢጠይቁት፤ ጤንነት: ማለት: ሁሉም: ነው: ብሎ መለሰ:: እውነት: ነው: ጤንነት: ከሌለ: ሁሉ: ነገር: ከንቱ: ነው:: ጤንነት: ካለ : ግን: ሁሉም: ነገር: መገኘቱ: አይቀርም::

*

በዓለም: ላይ: ትልቅ: ሥራ: ለመሥራት: የሚቻለው: ሠሪው: ሰውና: ለመሥራት: የተመቸበት: ጊዜ: እነዚህ: ሁለቱ: ሲገናኙ: ነው:: ትልቁን: ሥራ: ለመሥራት: የሚችለው: ሰው: ባልተመቸ: ጊዜ: ሲፈጠር: ሊሠራው: የሚችለውን: ሥራ: ሳይሠራው: መቅረት: ግድ: ይሆንበታል:: ልሥራም: ቢል: ጊዜው: አይደለምና: አይሆንለትም:: ትልቅ: ሥራ: ለመሥራት: የተመቸ: በሆነበት: ጊዜ: ደግሞ: ሊሠራው: የሚችል: ሰው: ባለመፈጠሩ: መልካሙ: ጊዜ: በከንቱ: ያልፋል:: እነዚህም: ሁለቱ: ተፈላላጊ: ነገሮች: የሚገናኙት: በብዙ: ዘመን: ወስጥ: ጥቂት: ጊዜ: ነው::

*

አንድ: ትልቅ: ሊቅ: እንዲህ: ተናገረ: በእጅ: ከማይቧጠጥ፤ በእግር: ከማይቈነጠጥ: ከትልቅ: ገደል: ወጥቶ: ከጫፉ: ላይ ለመድ

*

ረስ ፡ የሚችል ፤ ወይም ፡ በክንፎቹ ፡ የሚበር ፡ ንስር ፤ ወይም ፡ በሆዷ ፡ የምትጐተት ፡ ትል ፡ እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። በዓለም ፡ ላይም ፡ ከትልቅ ፡ ማዕርግ ፡ ለመድረስ ፡ የሚችሉ ፡ ወይም ፡ በገዛ ፡ ራሳቸው ፡ ዋጋ ፡ የሚነሡ ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በተንኰልና ፡ በወራዳ ፡ ሥራ ፡ እየተልከሰከሱ ፡ ጺያፍ ፡ በሆነ ፡ ምግባር ፡ ራሳቸውን ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ቀብረው ፡ ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ የሚጐተቱ ፡ ዝቅተኞችና ፡ ተንኰለኞች ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ።

*

ሰው ፡ ደስ ፡ ባለውና ፡ በተመቸው ፡ ሰዓት ፡ የጊዜው ፡ ሁኔታ ፡ ሳይለወጥ ፡ እንዳለ ፡ ሆኖ ፡ ቢኖር ፡ ይፈቅዳል ። ደግሞ ፡ ሰው ፡ በከፋውና ፡ በተበሳጨ ፡ ጊዜ ፡ ዓለም ፡ ብትበጠበጥና ፡ የጊዜውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢለዋወጥለት ፡ ይወዳል ። ግን ፡ መሬትን ፡ ከመዞርዋና ፡ ከመሽከርከርዋ ፡ አንዲት ፡ ደቂቃ ፡ እንኳን ፡ ሊያቆማት ፡ የሚችል ፡ ነገር ፡ እንደሌለ ፡ የዓለምንና ፡ የጊዜውን ፡ ሁኔታም ፡ እንደዚሁ ፡ ቢከፋም ፡ ቢበጅም ፡ ከመለዋወጡ ፡ ሊያግደውና ፡ ሊከለክለው ፡ የሚችል ፡ ሰው ፡ አይገኝም ።

*

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ በዓለም ፡ ፊት ፡ ሲመለከቱት ፡ ኢምንት ፡ መሆኑን ፡ ቢገልጥ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ዐዋቂ ፡ እንዲህ ፡ ተናገረ ።

በግራዬና ፡ በቀኜ ፤ በፊቴና ፡ በኋላዬ ፡ ዞሬ ፡ የዓለምን ፡ ሰፊነት ፡ አይቼ ፤ ደግሞ ፡ የኔን ፡ የራሴን ፡ የቁመቴን ፡ አጭርነትና ፡ የጐኔን ፡ ጠባብነት ፡ ከተመለከትኹ ፡ በኋላ ፡ የዓለምን ፡ ትልቅነትና ፡ የኔን ፡ ትንሽነት ፡ አስተያይቼ ፡ ሳመዛዝነው ፡ ኢምንትነቴን ፡ እየተረዳሁት ፡ ከኀፍረት ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ መንፈሴ ፡ ይኰማተራል ። ነፍሴም ፡ ትርገበገባለች ።

* * *





<u>የብረት ፡ ድስትና ፡ የሸክላ ፡ ድስት ።</u>

አንድ ፡ ቀን ፡ ብረት ፡ ድስት ፡ ሸክላ ፡ ድስትን ፡ አለው ።
እኔን ፡ ነው ፡ በሁሉም ፡ መልክህ ፡ የሚመስለው ።
ወንድሜ ፡ ነህ ፡ እኮ ፡ ባታውቀው ፡ ነው ፡ እንጂ ፤
ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እንሁን ፡ ወዳጂ ።
እኔን ፡ እንደ ፡ መቅረብ ፡ መሸሽህ ፡ ለምን ፡ ነው ?
አካሌ ፡ አካላትህ ፡ የኔ ፡ ቤት ፡ ያንተም ፡ ነው ።
አሁንም ፡ በል ፡ ተነሥ ፡ ፍቅራችንም ፡ ይጥና ፤
ሽር ፡ ሽር ፡ እያልን ፡ እንናፈስና ።
መፋቀራችንን ፡ ይይልን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፤
የማንተዋወቅ ፡ ለምን ፡ ነው ፡ መምሰሉ ።
አጥቂ ፡ ቢመጣብህ ፡ ዘሎ ፡ የሚማታ ፤
እኔ ፡ እሆንሃለሁ ፡ ኀይለኛ ፡ መከታ ፤
ለፀሐይ ፡ ላቧራው ፡ እየሆንኩህ ፡ ድንኳን ፤
እደግፍሃለሁ ፡ ቢያንቅፍህ ፡ እንኳን ።
በደካማነቱ ፡ ቅር ፡ እያለው ፡ ሆዱ ።
ተነሣ ፡ ሸክላ ፡ ድስት ፡ አንድነት ፡ ሊሄዱ ፤
አንድ ፡ መቶ ፡ እርምጃ ፡ እንደ ፡ ተራመዱ ፤

ድንገት፡ ተጋጩና፡ እቶ፡ ብረት፡ ድስት፤
ረግተው፡ ሲቆሙ፡ ያላንዳች፡ ጉዳት።
የሸክላ፡ ድስት፡ ግን፡ በፈራው፡ ጐዳና፤
ተሰብሮ፡ ወደቀ፡ እንክትክት፡ አለና።
ወዮ፡ እንኳ፡ ለማለት፡ ጊዜ፡ ሳያደርሰው፤
የገሉ፡ ስባሪ፡ ምድሩን፡ አሰበሰው።
እንዲያው፡ ሰው፡ ያላቻ፡ እየተንጠራራ፤
ለመሻረክ፡ ቢያስብ፡ ከበላዩ፡ ጋራ።
መቼም፡ አይጠፋና፡ ከጎይለኛ፡ ግፍ፤
ከጉዳት፡ በተቀር፡ ምንም፡ አያተርፍ።
ሰዎች፡ ከሰው፡ ጋራ፡ ሽሪክ፡ ስትሆኑ።
ዐቅማችሁን፡ በፊት፡ አይታችሁ፡ መዝኑ።

* * *

## እ ብ ደ ት ።

እብደት፡ ከሁሉ፡ የባሰ፡ ትልቅ፡ በሽታ፡ ነው። ከሁሉም፡ የባሰ፡ የሚያደርገው፡ ሰው፡ የሚከበርበትን፡ አእምሮውን፡ ስለሚያበላሸውና፡ እንደ፡ እንስሳ፡ ስለሚያደርገው፡ ነው። ለዚሁም፡ ታሪካዊ፡ የሆነ፡ አንድ፡ ምሳሌ፡ ልሰጣችሁ፡ እወዳለሁ።

ካሊጎላ፡ የሚባለው፡ አንዱ፡ የሮማ፡ ንጉሥ፡ አስቀድሞ፡ አእም ሮው፡ የተካከለ፡ ደኅና፡ ሰው፡ ነበር። ኋላ፡ ግን፡ አእምሮው፡ ወደ ፡ ክፋትና፡ ወደ ፡ ጭካኔ፡ ተለውጦ ፡ የሚሠራው፡ ሥራ፡ ሁሉ፡ የእብ ደት፡ ሥራ፡ ሆነ።

ከዕለታት፡ አንድ፡ ቀን፡ ከሁለት፡ አማካሪዎቹ፡ ጋራ፡ በምክር፡ ቤት፡ ውስጥ፡ ተቀምጦ፡ ስለ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ የመንግሥት፡ ጉዳዮች፡ ሲነ ጋገሩ፡ ንጉሡ፡ ከት፡ ብሎ፡ ልቡ፡ እስኪፈርስ፡ ድረስ፡ ሣቀ። ቁም፡ ነገር፡ በሆነው፡ ይነጋገሩበት፡ በነበረው፡ ጉዳይ፡ ውስጥ፡ ምንም፡ የሚያሥቅ፡ ነገር፡ ስላልነበረበት፡ ሁለቱ፡ አማካሪዎች፡ ገርሟቸው፡ ንጉሥ፡ ሆይ፡ ምን፡ የሚያሥቅ፡ ነገር፡ አገኙ፡ ብለው፡ ጠየቁት። ካሊጎላም፡ አሁን፡ እኔ፡ ቢያሰኘኝ፤ በኩል፡ ሰዓት፡ ውስጥ፡ ሁለታችሁንም፡ ለማስገደድ፡ የማቻለኝ፡ መሆኔን፡ ሳስበው፡ በጣም፡ ያሥቀኛል፡ ብሎ፡ መለሰላቸው።



ይህ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ጨርሶ ፡ ለማበዱ ፡ ዋዜማው ፡ ሆነ ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ያለ ፡ ፍርድ ፡ የብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ንጹሕ ፡ ደም ፡ በከንቱ ፡ አፈሰሰ ። ከጭካኔውም ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ በሰይፍ ፡ ቈርጬ ፡ ለመ ጣል ፡ እንዲመቸኝ ፡ ምነው ፡ የሮማውያን ፡ ሕዝብ ፡ አንገታቸውና ፡ ራሳቸው ፡ የሁሉም ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ በሆነ ፡ ኖሮ ፡ እያለ ፡ በገሃድ ፡ ይና ገር ፡ ነበር ፡ ይባላል ። እንደዚህ ፡ እንደ ፡ ተመኘው ፡ ለማድረግ ፡ በቻለ ፡ ኖሮ ፡ እንዴት ፡ መልካም ፡ ነበር ። ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የካሊጎላን ፡ ጭካኔ ፡ በእብደት ፡ ተርጕመውታል ።

* * *

## <u>አስቸጋሪ ፡ ፍርድ ።</u>

ባንድ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ማረሻና ፡ ማጭድ ፡ ቢላዎና ፡ መጥረቢያ ፡ ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ብረታ ፡ ብረት ፡ የሆነ ፡ የሥራ ፡ መሣሪያ ፡ እየሠራ ፡ ለባላገሩ ፡ የሚሸጥ ፡ አንድ ፡ ባለጅ ፡ ነበር ። እሱም ፡ በነፍስ ፡ ግዳይ ፡ ተከሶ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቀረበና ፡ ይሙት ፡ በቃ ፡ ተፈረደበት ። ያገሩም ፡ ሕዝብ፡ ይህን ፡ ሲሰማ፡ ለሥራ፡ የሚያገለግለን ፡ መሣሪያ ? በያይ ነቱ ፡ ቀጥቅጦ ፡ የሚሠራልን ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ። እሱ ፡ ከተገደለ ፡ እን ግዴህ ፡ ወደፊት ፡ ማን ፡ ሊሠራልን ፡ ይችላል ፡ ሲል ፡ ባለጁ ፡ እንዳይ ገደልበት ፡ አቤቱታውን ፡ ላገረ ፡ ገዢው ፡ አቀረበ ።

አገረ ፡ ገዢው ፡ ነፍስ ፡ የገደለ ፡ ሰው ፡ በግድ ፡ መሞት ፡ አለበት ፡ ይህም ፡ የማይሻር ፡ ፍርድ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ መለሰላቸው ፤ ያገሩ ፡ ሰዎች ፡ ሰው ፡ የገደለ ፡ ሰው ፡ መሞት ፡ ግድ ፡ ከሆነበት ፡ በዚህ ፡ በኛ ፡ ወረዳ ፡ ሁለት ፡ ሸማኔዎች ፡ ይገኛሉ ። ለኛ ፡ አንድ ፡ ሸማኔና ፡ አንድ ፡ ቀጥ ቃጭ ፡ በቂያችን ፡ ናቸው ። ስለዚህ፡ በቀጥቃጩ ፡ ፈንታ ፡ ከሁለቱ ፡ ሸማ ኔዎች ፡ ዕጣ ፡ አውጥታችሁ ፡ የወጣበትን ፡ አንደኛውን ፡ ግደሉት ፡ እንጂ ፤ ቀጥቃጩ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ አይገደለም ፡ ብለው ፡ ዳኛውን ፡ አስ ጨንቀው ፡ ያዙት ። በዳኝነት ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ጣጣ ፡ ብዙ ፡ ነው ።

* * *

## ረኃብን ፡ የሚሻ ፡ ሀብታም ።

ብዙ ፡ ሚሊዮን ፡ ብር ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ ሀብታም ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ እሱም ፡ ልቡ ፡ እኽል ፡ መብላት ፡ እየወደደ ፡ ሆዱ ፡ አልቀበልህ ፡ ብሎት ፡ በጣም ፡ ሲያማርር ፡ ይኖር ፡ ነበረ ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ምናልባት ፡ ቢርበኝ ፡ ብሎ ፡ እየተንጐራደደ ፡ በመንገድ ፡ ሲንሸረሸር ፤ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ በረኃብ ፡ መሞቴ ፡ ነውና ፡ እባክዎ ፡ የቸርነትዎን ፡ ያድርጉልኝ ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ ለማኝ ፡ ምጽዋት ፡ ቢጠይቀው ፡ እንዴት ፡ ያለኸው ፡ ቀልደኛ ፡ ነህ ፡ እኔ ፡ ረኃብን ፡ ፈልጌ ፡ ሳላገኘው ፡ እኖራለሁ ። አንተ ፡ ደግሞ ፡ ቀብራሬ ፡ ራበኝ ፡ ብለህ ፡ ታማርራለህ ፡ ምነው ፡ እኔም ፡ እንዳተ ፡ በታደልኩኝ ፡ ኖሮ ፡ ብሎ ፡ ሀብታሙ ፡ ሰውዬ ፡ ለድኻው ፡ ምንም ፡ ሳይሰጠው ፡ ዝም ፡ ብሎት ፡ አለፈ ።

* * *


## ደራሲና ፡ ሌባ ።

አንድ ፡ ደራሲ ፡ በጣም ፡ ድኻ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ገንዘብ ፡ ከእጁ ፡ እያጣ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ምሳውን ፡ ሳይበላ ፡ ጦሙን ፡ ይውል ፡ ነበረ ። አንድ ፡ ቀን ፡ ሌሊት ፡ ሌባ ፡ በር ፡ ሰብሮ ፡ ከመኝታ ፡ ቤቱ ፡ ገብቶ ፡ የደራሲውን ፡ ኮትና ፡ ሱሪ ፡ አንሥቶ ፡ ኪሱን ፡ እየበረበረ ፡ ደግሞም ፡ የገበታውን ፡ ኪሶች ፡ እየከፈተ ፡ ፈልጎ ፡ ምንም ፡ ገንዘብ ፡ ሳያገኝ ፡ በከንቱ ፡ ሲደክም ፡ ለካ ፡ ደራሲው ፡ ከመጀመሪያው ፡ ነቅቶ ፡ ይመለከት ፡ ኖሮ ፡ ከት ፡ ብሎ ፡ ካንጀቱ ፡ ሣቀ ፤ እንዲህ ፡ ያሣቀህ ፡ ነገር ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሌባው ፡ ቢጠይቀው ፤ ጂሎ ፡ ያሣቀኝማ ፡ እኔ ፡ ቀን ፡ በስድስት ፡ ሰዓት ፡ በብርሃን ፡ ጊዜ ፡ ሲርበኝ ፡ ፈልጌ ፡ በኪሴ ፡ ውስጥ ፡ ያላገኘሁትን ፡ ገንዘብ ፡ አሁን ፡ በእኩለ ፡ ሌሊት ፡ በጨለማ ፡ አገኛለሁ ፡ ብለህ ፡ በከንቱ ፡ ስትደክም ፡ በማየቴ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ እያሾፈ ፡ መለሰለት ።



## ሁለት ፡ አፍ ፡ ያለው ፡ ወፍ ።

እየለቃቀሙ ፡ የሚበሉለት ፤
አንድ ፡ ወፍ ፡ ነበረ ፡ ሁለት ፡ አፍ ፡ ያሉት ።
ከሁለቱ ፡ አንደኛው ፡ ጐበዝ ፡ ብርቱ ፡ ነበር ፤
ጥራጥሬ ፡ ሲገኝ ፡ ስንዴ ፡ ወይም ፡ አተር ።
በኀይል ፡ እየሄደ ፡ ይደርስና ፡ ቀድሞ ፤
ቀምቶ ፡ ለብቻው ፡ ይበላል ፡ ለቃቅሞ ፤
ምንም ፡ ደካማው ፡ አፍ ፡ አይደርሰው ፡ ፈጽሞ ።



የባቄላ ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ ያተር ፡ ፍሬ ፤
አንድ ፡ ቀን ፡ እንዲሁ ፡ አገኙና ፡ ጥሬ ።
ያ ፡ ብርቱ ፡ ጐበዝ ፡ አፍ ፡ ቀድሞ ፡ እንደለመደው ፤
ተሽቀዳደመና ፡ አሁንም ፡ ቢወሰድው ።
እንዲህ ፡ ተናገረ ፡ ያ ፡ ደካማው ፡ አፍ ፤
የምትሠራው ፡ ሥራ ፡ ነውር ፡ ነው ፡ ጸያፍ ።
እንካፈል ፡ ሳትል ፡ ምንም ፡ ሳትሰጠኝ ፤
ሁሉን ፡ ትበላለህ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ሲገኝ ።

እኔም ፡ ወንድምህ ፡ ነኝ ፡ ምነው ፡ ብንካፈል ፤
እባክህ ፡ ይቅርብህ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ በደል ።
ባወቅሁማ ፡ ኖሮ ፡ ልብህ ፡ መከጀሉን ፤
አሳልፌ ፡ ላንተ ፡ እተው ፡ ነበር ፡ ሁሉን ።
ልብህ ፡ እየጓጓ ፡ መመኘት ፡ መድፈሩ ፤
እንዴት ፡ ወገኛ ፡ ነህ ፡ እንዲያው ፡ ለነገሩ ።
እኔ ፡ ስበላ ፡ አይተህ ፡ ደስ ፡ ይበልህ ፡ እንጂ ፤
ያንተ ፡ መከጀልስ ፡ ለምንም ፡ አይበጂ ?
ብሎ ፡ መለሰለት ፡ በጣም ፡ እያሾፈ ፤
ይኸን ፡ ተባብለው ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ አለፈ ።
ወፉ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ድንገት ፡ እዛፍ ፡ ላይ ፡ ዐረፈ ።
ያረፈበትም ፡ ዛፍ ፡ ፍሬው ፡ የመረረ ።
ቢበሉት ፡ የሚገድል ፡ መርዘኛ ፡ ነበረ ፤
የተበደለው ፡ እፍ ፡ እንጀቱ ፡ ያረረ ።
ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ ምግብ ፡ ከተከለከልኩ ፤
አተርና ፡ ስንዴ ፡ ጤፍ ፡ ካልተመገብኩ ።
ስራብ ፡ ብግደረደር ፡ ምንም ፡ አልጠቀም ፤
አለና ፡ ፍሬውን ፡ አደረገው ፡ ለቀም ።
ያ ፡ ግፈኛው ፡ እፍ ፡ ግን ፡ ይቅርብህ ፡ ቶሎ ፡ ጣል ፤
ይህ ፡ መርዘኛ ፡ ፍሬ ፡ መሞትን ፡ ያመጣል ።
አትብላ ፡ እንሞታለን ፡ ይኸን ፡ መርዝ ፡ ፍሬ ፤
ይቅርብህ ፡ አትብላ ፡ አንድንም ፡ ዛሬ ።
የሚያዋዛ ፡ አይደለም ፡ ይቅር ፡ ተው ፡ አትበድ ፤
እያለ ፡ ደንግጦ ፡ ፈርቶ ፡ ሲርበደበድ ።
ያ ፡ ግን ፡ የቀድሞውን ፡ ቂሙን ፡ ስላልረሳ ፤
እሞታለሁ ፡ ብሎ ፡ ለነፍሱ ፡ ሳይሳሳ ።
ብድር ፡ መመለሱ ፡ ሆኖለት ፡ ደስታ ፤
ፈርቶ ፡ የሚጥለው ፡ መስሎ ፡ ያመነታ ፤
ቈይቶ ፡ በፍርሀት ፡ ያንን ፡ ሲያንገላታ ፤
ኋላ ፡ ግን ፡ ነቅንቆ ፡ ራሱን ፡ በእንቢታ ።



ፍሬውን፡ በላና፡ ከነሁለት፡ አፉ፤
እዚያው፡ ሳይነሣ፡ ወዲያው፡ ሞተ፡ ወፉ፡፡
ይህ፡ የህንዶች፡ ተረት፡ የሰጠን ባጭሩ፤
ብንመለከተው፡ ጉልህ፡ ነው፡ ምስጢሩ፡፡
ክፉ፡ ልሥራ፡ ብሎ፡ ቂም፡ ይዞ፡ ሲነሣ፤
ሰው፡ እንኳ፡ ለሌላ፡ ለነፍሱም፡ አይሳሳ፡፡
ደግሞም፡ በግል፡ ጠብ፡ ሰው፡ ልቡ፡ እያቄመ፤
የቂሙቱን፡ ብድር፡ መስሎት፡ የፈጸመ፡፡
መካፈሉ፡ ላይቀር፡ አንድነት፡ ጉዳቱን፤
ሲበድል፡ ይገኛል፡ የጋራ፡ ንብረቱን፡፡

* * *

<u>አንዲት፡ አህያ፡ ርጎራጌን፡ አስተማረች፡፡</u>

ሁለት፡ ልጆች፡ በመንገድ፡ ሲያልፉ፡ አንዲት፡ እንቁራሪት፡ አግኝተው፡ ሊገድሏት፡ ዐለቡና፡ ድንጋይ፡ እየወረወሩባት፡ ተከታተሏት፡፡ በዚያውም፡ መንገድ፡ አንዲት፡ አህያ፡ ስታልፍ፡ እንቁራሪቷ፡ ላይ፡ በእግርዋ፡ ልትቆምባት፡ ስትል፡ አየቻትና፡ እንዳትረግጣት፡ እርምጃዋን፡ በቶሎ፡ አቃንታ፡ በጐን፡ ሳትነካት፡ አለፈች፡፡

ከሁለቱ፡ ልጆች፡ አንደኛው፡ ወዳጁን፡ አለው፡፡ ይህችን፡ አህያ፡ ተመለከትሀት፡ ወይ? እንቁራሪቷን፡ እንዳትረግጣት፡ አዝና፡ መንገዷን፡ አሳብራ፡ አለፈች፤ እኛስ፡ የዚችን፡ አህያ፡ ያህል፡ ርጎራጌ፡ ሳይኖረን፡ ቀርቶ፡ ነውን፡ ይህችን፡ እንቁራሪት፡ ለመግደል፡ ዐስበን፡ እንዲህ፡ የምናሳድዳት፤ አይሆንም፡ ተው፡ ይቅርብን፡ ብሎ ወዳጁን፡ መልካም፡ ምክር፡ መክሮ፡ እንቁራሪቷን፡ በሰላም፡ ትተዋት፡ ተመለሱ፡፡

* * *

<u>መልካም፡ ምላስ፡ ቁጣን፡ ታበርዳለች፡፡</u>

እናቱ፡ በጣም፡ አድርጋ፡ የምትወደው፡ አንድ፡ ልጅ፡ ነበር፡፡ እሱም፡ ከዐጥር፡ ግቢያቸው፡ ውስጥ፡ ከሚገኙት፡ የኮክ፡ ዛፎች፡ ላይ፡ እየወጣ፡ ፍሬውን፡ ሲቈርጥ፡ እናቱ፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ ታየው፡ ነበርና፡ ከዛፉ፡

ላይ ፡ ወድቆ ፡ አደጋ ፡ ያገኘዋል ፡ በማለት ፡ ስለ ፡ ሥጋት ፡ እንዳይወጣ ፡ መላልሳ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከልክላው ፡ ነበር ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ከቤት ፡ ውስጥ ፡ ሆና ፡ ልጅዋ ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ከኮኩ ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ፍሬ ፡ ሲለቅም ፡ በመስኮት ፡ አየችው ። ከቤት ፡ ሲገባ ፡ ጠርታው ፡ ከዛፍ ፡ ላይ ፡ አትውጣ ፡ ብዬ ፡ ከልክዬህ ፡ አል ነበረምን ? ለምንድን ፡ ነው ፡ ዛሬ ፡ ደግሞ ፡ የወጣኸው ፡ ብላ ፡ ጠየቀችው ።

እሱ ፡ ግን ፡ ደንግጦ ፡ አልወጣሁም ፡ ብሎ ፡ካደ ። እሷዋም ፡ በጣም ፡ ተቈጣችና ፡ ደግሞ ፡ ከማጥፋትህ ፡ መዋሸትህ ፡ ይባስ ፡ ባይኖቼ ፡ እያየ ሁህ ፡ ትክደኛለህ ፡ ብላ ፡ ልትመታው ፡ ተነሣች ።

እሱም ፡ አሳዛኝ ፡ የሆኑትን ፡ ዐይኖቹን ፡ እያንከራተተ ፡ ለዛ ፡ ባለው ፡ አንደበቱ ፡ እማማ ፡ እወድሀለሁ ፡ ትይኛለሽ ፤ እንደምትይኝም ፡ እው ነት ፡ የምትወጅኝ ፡ ከሆንሽ ፡ ባይኖችስ ፡ ካየሽው ፡ ይልቅ ፡ እኔ ፡ የም ነግርሽን ፡ አብልጠሽ ፡ ማመን ፡ ይገባሻል ፡ አላት ። ደግሞ ፡ ልጅ ፡ ይህን ፡ ማለቱ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ፍቅር ፡ ብለሽ ፡ ያየሽውን ፡ እንዳላየሽ ፡ አድ ርገሽ ፡ አሳልፊው ፡ እንጂ ፤ በጥፋቴ ፡ ለምን ፡ ትምግችኛለሽ ፡ ብሎ ፡ መለ ማመጡ ፡ ነው ። እናቱም ፡ በዚህ ፡ ለዛ ፡ ባለው ፡ ንግግር ፡ ከቍጣዋ ፡ በርዳ ፡ በመምታት ፡ ፈንታ ፡ ልጅዋን ፡ አቅፋ ፡ ሳመችው ። ዐይኖችዋም ፡ ዕንባ ፡ አቅርረው ፡ ይታዩ ፡ ነበር ።

* * *

## ከባለቤት ፡ ያወቀ ፡ ቡዳ ፡ ነው ።

አቶ ፡ ተገኝ ፡ የሚባሉ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበሩ ። አንድ ፡ ቀን ፡ ሥራ ፡ በዝቶባቸው ፡ እቤታቸው ፡ ውለው ፡ ኖሮ ፡ አሽከራቸውን ፡ ጠርተው ፡ ዛሬ ፡ ብርቱ ፡ ሥራ ፡ ይዣለሁና ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ መጥቶ ፡ እኔን ፡ ቢጠይ ቅህ ፡ የለም ፡ ወደ ፡ ውጪ ፡ ወጥቶአል ፡ ብለህ ፡ መልሰው ፡ አሉና ፡ አዘ ዙት ። አሽከርዩውም ፡ እንደ ፡ ታዘዘው ፡ አድርጎ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ሲመጣ ፡ የሉም ፡ እያለ ፡ መለሰ ። አንድ ፡ ሰው ፡ በኋላ ፡ መጥቶ ፡ አቶ ፡ ተገኝ ፡ በቤታቸው ፡ ውስጥ ፡ ካንዱ ፡ ወደ ፡ አንደኛው ፡ ክፍል ፡ ሲተላለፉ ፡ በመ ስኮት ፡ አይቷቸው ፡ ኖሮ ፡ አሽከሩን ፡ ንገርልኝ ፡ አለው ። አሽከር ፡ ግን ፡




እንደ ፡ ልማዱ ፡ የሉም ፡ ወደ ፡ ውጪ ፡ ወጥተዋል ፡ ብሎ ፡ መለሰ ። እንግዳው ፡ ግን ፡ አሁን ፡ ባይኔ ፡ አይቻቸዋለሁና ፡ ታልነገልርከልኝ ፡ አይሆንም ፡ ብሎ ፡ አስቸገረው ። አሽከር ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ላቶ ፡ ተገኝ ፡ ይህንኑ ፡ ነገሩቸው ፡ እሳቸውም ፡ ተቈጥተው ፡ በሩን ፡ ከፍተው ፡ ወጡና ፡ እንግዳውን ፡ ወዳጄ ፡ ምን ፡ ትፈልጋለህ ፡ አሉት ። እርስዎን ፡ ነው ፡ ቢላቸው ፡ እኔን ፡ ከሆነ ፡ እኔ ፡ የለሁም ፡ ወደ ፡ ውጪ ፡ ወጥቻለሁ ፡ ብለው ፡ በሩን ፡ በኀይል ፡ ወርውረው ፡ ዘግተው ፡ እቤታቸው ፡ ተመል ሰው ፡ ገቡ ።

* * *

## አንድ ፡ ሀብታምና ፡ አንድ ፡ ድኻ ፡ ሰው ።

የቃሉ ፡ አሰባበር ፡ የድምጡ ፡ ማማር ፤
እጅግ ፡ የሚያስደንቅ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበር ፤
ጫማ ፡ ሰፊ ፡ ሆኖ ፡ አንዲት ፡ መደብር ፤
ከፍቶ ፡ እዚያ ፡ እየሰፋ ፡ በዚሁ ፡ ሲኖር ።



ሁልጊዜ ፡ ማለዳ ፡ ልምድ ፡ ሆኖበት ፤
ሲዘፍን ፡ ያረፍዳል ፡ ተነሥቶ ፡ በጠዋት ፤
አንዱ ፡ ሀብታም ፡ ደግሞ ፡ የሱ ፡ ጎረቤት ።

ገንዘብ ፡ የተረፈው ፡ እጅግ ፡ አለመጠን ፤
እየተደነቀ ፡ በዚህ ፡ በሰው ፡ ዘፈን ።
ይልቁንም ፡ ደግሞ ፡ በድምጡ ፡ ማማር ፤
ጡዋት ፡ ጡዋት ፡ እየነቃ ፡ ይሰማው ፡ ነበር ።
እንዲህ ፡ ሲል ፡ ዐሰበ ፡ ይኸም ፡ ባለጠጋ ፤
ይኸ ፡ ጫማ ፡ ሰፊ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ሳይነጋ ።
ማለዳ ፡ ተነሥቶ ፡ እንደዚህ ፡ መዝፈኑ ፤
ቢደላው ፡ ይሆናል ፡ ጌታ ፡ በመሆኑ ።
እቤቱ ፡ አስጠራና ፡ ያንን ፡ ጫማ ፡ ሰፊ ፤
ሀብታም ፡ ነህ ፡ መሰለኝ ፡ ብዙ ፡ ብር ፡ አትራፊ ።
ሁል ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ ብሎህ ፡ ስትዘፍን ፡ መኖርህ ፤
ቢደላህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ገንዘብ ፡ ባይቸግርህ ።
ስንት ፡ ታተርፋለህ ፡ ዓመት ፡ ስትሠራ ?
ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ከሣራ ።
ልፋት ፡ ነው ፡ ትርፋችን ፡ ምንም ፡ ብንደክም ፤
ከድካም ፡ በተቀር ፡ አይገኝም ፡ ጥቅም ።
ማጠራቀም ፡ ቀርቶ ፡ የገንዘብ ፡ ስብሰባ ፤
የለት ፡ ጕርሳችንን ፡ ይዘን ፡ ስንገባ ፤
ይህ ፡ ነው ፡ የኛ ፡ ክብረት ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ፤
እሺ ፡ ይሁን ፡ ደግሞ ፡ ይቅርና ፡ የዓመት ።
ስትሠራ ፡ ውለህ ፡ ያተረፍከ ፡ ለታ ፤
ስንት ፡ ገንዘብ ፡ ይዘህ ፡ ትገባለህ ፡ ማታ ፤
ብሎ ፡ መለሰና ፡ ቢጠይቀው ፡ ደግሞ ፤
እንደኔ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ደክሞ ፤
ሲሠራ ፤ ሲማስን ፡ ሲደክም ፡ ቢውል ፤
አይችልም ፡ ለማትረፍ ፡ የላቡን ፡ ያህል ።
እየሠራ ፡ ኖሮ ፡ ሲለፋ ፡ እየዋለ ፤
ለቀለብ ፡ ለልብሱ ፡ ራሱን ፡ ከቻለ ፤
በየቀኑ ፡ ትርፌ ፡ ይኸንን ፡ እከለ ፤
በማለት ፡ ሒሳቡን ፡ እያስላሰለ ፤



ለመቍጠር ፡ አይችልም ፡ የትርፉን ፡ ልክ ፡ መጠን ፤
መቼም ፡ አይበልጥና ፡ ከችግሩ ፡ ወሰን ።
ይኸን ፡ ጊዜ ፡ ሀብታም ፡ ከት ፡ ብሎ ፡ ሥቆ ፤
ይህ ፡ ሰው ፡ ባለጠጋ ፡ እንዳልሆነ ፡ ዐውቆ ።
ተነሥቶ ፡ ሄደና ፡ አንድ ፡ ከረጢት ፡ ወርቅ ፤
ከጓዳው ፡ አውጥቶ፡ ያ ፡ ድኻ ፡ ሲደነቅ ።
ይኸውልህ ፡ እንካ ፡ ለቤት ፡ ለትዳርህ ፤
ይኸንን ፡ ወርቅ ፡ ውሰድ ፡ ዳግመኛ ፡ አይቸግርህ ።
ለጕዳይህ ፡ እርገው ፡ ብሎ ፡ ቢያስታቅፈው ፤
እያመሰገነ ፡ መልካም ፡ ቃል ፡ ሳይተርፈው ፤
በደስታ ፡ ብዛት ፡ ዐሳቡ ፡ ተናውጦ ፤
መንገዱን ፡ ሳያውቀው ፡ ደረሰና ፡ ሮጦ ።
እቤቱ ፡ ገባና ፡ ጓዳውን ፡ ቈፍሮ ፤
ከነከረጢቱ ፡ ወርቁን ፡ እዚያ ፡ ቀብሮ ።
እንግዲህ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጥፎ ፡ መጥፎ ፡ ነገር ፤
ሳይወድ ፡ በዐሳቡ ፡ ይመጣበት ፡ ጀመር ።
ወርቅ ፡ መቀበሌን ፡ ምናልባት ፡ የሰማ ፤
ሌባስ ፡ ቢመጣብኝ ፡ ገድሎ ፡ የሚቀማ ።
ዕረፍት ፡ የሚነሣ ፡ አሸባሪ ፡ አደጋ ፤
በጣም ፡ መጥፎ ፡ ዐሳብ ፡ እጅግ ፡ የሚያሠጋ ።
በልቡ ፡ እየመጣ ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፤
የአይጦች ፡ ኮሽታ ፡ ወይም ፡ የድመት ፤
ያሸብረው ፡ ጀመር ፡ እንቅልፉን ፡ ነሥቶት ፤
ማለዳ ፡ መዝፈኑ ፡ ሌሊት ፡ መተኛቱ ፤
መሥራቱም ፡ ቀረና ፡ ጠፋ ፡ ጤንነቱ ።
ይህ ፡ የፍርሀት ፡ ዐሳብ ፡ ልቡን ፡ የመረዘው ፤
እየከነከነ ፡ ስለ ፡ ወዘወዘው ፤
ነገሩን ፡ መዝኖ ፡ አይቶ ፡ በመመልከት ፤
ምንም ፡ የሚጠቅም ፡ ነገር፡ ስላጣበት ፤
ተነሥቶ ፡ ሄደና ፡ ከሀብታሙ ፡ ዘንድ ፤
ሥጋቱ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ የማይለመድ ፤
ይኸውልህ ፡ በቃኝ ፡ ወርቅህን ፡ ውሰድ ።

በወርቅህም ፡ ፈንታ ፡ ዘፈኔን ፡ ለውጠኝ ፤
እንቅልፍና ፡ ድምጤን ፡ መልስና ፡ ስጠኝ ።
አለና ፡ ከልቡ ፡ ያን ፡ ሁሉ ፡ ሥጋት ፤
ከወርቁ ፡ ጋር ፡ ወስዶ ፡ መልሶ ፡ ሰጥቶት ።
በጣም ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ሊኖር ፡ እንደ ፡ ጥንቱ ፤
ተመልሶ ፡ ሄደ ፡ ወደ ፡ ድኽነቱ ።
ደስ ፡ ይለው ፡ መስሏችሁ ፡ ገንዘብ ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፤
እስኪ ፡ ባለማወቅ ፡ እንዳትታለሉ ።

* * *

## ሰ ነ ፍ ፡ ተ ማ ሪ ።

አንድ ፡ ሰነፍ ፡ ልጅ ፡ ገና ፡ መጀመሪያ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ የገባ ፡ ዕለት ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ ፊደል ፡ መቍጠር ፡ ጀመረ ።

ከሀ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፐ ፡ ድረስ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ የፊደሉን ፡ ተራ ፡ ወጣና ፡ ከሁለተኛው ፡ ላይ ፡ መምህሩ ፡ መልሶ ፡ ሲመራው ፤ ሀ ፡ በል ፡ ቢለው ፡ ተማሪው ፡ እንቢ ፡ አለ ። ቢያባብለው ፡ ቢለምነው ፤ ቢለው ፡ ቢያደርገው ፡ አሻፈረኝ ፡ ብሎ ፡ እስከ ፡ ጭራሹም ፡ እያለቀሰ ፡ ሸሽቶ ፡ ከተማሪ ፡ ቤት ፡ ወጥቶ ፡ ሄደ ።

በባቡር ፡ መንገድ ፡ እያለቀሰ ፡ ሲሄድ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አግኝቶት ፡ ምነው ፡ ምን ፡ አገኘህና ፡ እንደዚህ ፡ ታለቅሳለህ ፡ ቢለው ፡ መምህሬ ፡ ሀ ፡ በል ፡ ቢለኝ ፡ እንቢ ፡ ብዬ ፡ በዚህ ፡ ተጣልተን ፡ ነው ፡ የማለቅሰው ፡ አለው ። ሀ ፡ ለማለት ፡ ታዲያ ፡ ምን ፡ የሚያስቸግር ፡ ነገር ፡ አገኘህበት ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ እነዚህ ፡ መምህሮች ፡ መቼ ፡ ጣጣቸው ፡ በሀ ፡ ብቻ ፡ ያልቃል ። ሀ ፡ ስል ፡ ሁ ፡ በል ፡ ይሉኛል ፤ ሁ ፡ ስል ፡ ሂ ፡ በል ፡ ይሉኛል ፡ ሂ ፡ ስል ፡ መልሰው ፡ ሃ ፡ በል ፡ ይሉኛል ። እንደዚህ ፡ እያሉ ፡ እስከ ፡ ፐ ፡ ድረስ ፡ የተጻፉትን ፡ ፊደሎች ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ሲያስቈጥሩኝ ፡ ያለበትን ፡ ድካም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቀምሼው ፡ አንገፈገፈኝ ። ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ይገድሉኛል ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ሁለተኛ ፡ ሀ ፡ ብዬ ፡ አል ጀምርም ፡ ብሎ ፡ ተማሪው ፡ መለሰለትና ፡ እንደገና ፡ እያለቀሰ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄደ ። ለሰነፍ ፡ ተማሪ ፡ ፊደል ፡ ትልቅ ፡ ተራራ ፡ መስሎ ፡ ይታየዋል ።

* * *



## ታማኝነት ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ነገር ፡ ነው ።

የንጉሥ ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ሆኖ ፡ የሚሠራ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበር ። እሱም ፡ የንጉሡን ፡ ገንዘብ ፡ እየሰረቀ ፡ በጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ሀብት ፡ ሰብስቦ ፡ ከበረ ። ኋላም ፡ ከንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ ቀርቦ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ እየነገድሁ ፡ ለመኖር ፡ ዐስቤያለሁና ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ፈቅዶልኝ ፡ ቢያሰናብተኝ ፡ እወድ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ ለመነው ። ንጉሡም ፡ መልሱን ፡ በኋላ ፡ እሰጥሃለሁ ፡ አለውና ፡ አሰናበተው ። እሱም ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ የእሱ ፡ ተቈጣጣሪ ፡ ሆኖ ፡ የሚሠራውን ፡ ሰው ፡ አስጠርቶ ፡ ይህ ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ሥራውን ፡ በትክክል ፡ ይሠራል ፡ ወይ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። ተቈጣጣሪውም ፡ የጐደለውን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ በመዝገቡ ፡ አመልክቶ ፡ የሰረቀውን ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ ለንጉሡ ፡ አስረዳው ።

ንጉሡ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግምጃ ፡ ቤቱን ፡ አስጠርቶ ፡ እንዲህ ፡ አለው ። አንድ ፡ ሰው ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከገበታው ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ጠርሙስ ፡ ወተት ፡ አስቀምጦ ፡ ሳይወትፈው ፡ ረስቶ ፡ ትቶት ፡ ሄደ ። አንድ ፡ እባብ ፡ በጠርሙሱ ፡ አፍ ፡ ገብቶ ፡ ወተቱን ፡ ሁሉ ፡ ጭልጥ ፡ አድርጎ ፡ ጠጣው ። ከጠጣውም ፡ በኋላ ፡ ተመልሶ ፡ በዚያው ፡ በጠርሙሱ ፡ አፍ ፡ ሊወጣ ፡ ቢሞክር ፡ ሰውነቱ ፡ በጣም ፡ ደነደነና ፡ የጠርሙሱ ፡ አፍ ፡ አላስወጣህ ፡ አለው ። ምንም ፡ ቢታገል ፡ ለመውጣት ፡ የማይቻል ፡ ሆነበት ።

እንግዴህ ፡ እንዳንተ ፡ ዐሳብ ፡ ይህ ፡ እባብ ፡ ከጠርሙሱ ፡ ውስጥ ፡ ለመውጣት ፡ እንዲችል ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይገባዋል ፡ ይመስልሃል ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። የጠጣውን ፡ ወተት ፡ ሁሉ ፡ መመለስ ፡ ያሻዋል ፤ ይህን ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሰውነቱ ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ተመልሶ ፡ ይቀጥንና ፡ የጠርሙሱ ፡ አፍ ፡ ያስወጣዋል ፤ አለዚያ ፡ ግን ፡ ለመውጣት ፡ አይችልም ፡ ብሎ ፡ ግምጃ ፡ ቤቱ ፡ መለሰለት ። ንጉሡም ፡ ያንተም ፡ ነገር ፡ እንደዚሁ ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በምሳሌ ፡ አስረዳው ።

አደራ ፡ በተረከበው ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለመንግሥቱና ፡ ለንጉሡ ፡ ታማኝ ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ ለሰው ፡ ከቀረው ፡ ሙያ ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነው ።

* * *

## ስ ካ ሮ ን ።

ስካሮን ፡ የሚባለው ፡ የፈረንሳዊ ፡ ተወላጅ ፡ የሆነ ፡ ባለቅኔ ፡ ክፉ ፡ የቁርጥማት ፡ ደዌ ፡ አድሮበት ፡ የሚበልጠው ፡ ዕድሜውን ፡ ካልጋ ፡ ሳይ ነሣ ፡ ሲማቅቅ ፡ ኖሮ ፡ ከዚሀ ፡ ሕመሙ ፡ ሳይፈወስ ፡ እንደ ፡ ታመመ ፡ ኖሮ ፡ ሞተ ። ከመሞቱም ፡ በፊት ፡ ይህንን ፡ መከራውን ፡ የሚገልጥ ፡ ቃል ፡ በግጥም ፡ አድርጎ ፡ ጽፎ ፡ በሞትሁ ፡ ጊዜ ፡ በመቃብሬ ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ እንድትጽፉት ፡ ብሎ ፡ አደራ ፡ ሰጠ ። የተቻለንን ፡ ያህል ፡ አስመ ስለን ፡ በግጥም ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ስንተረጕመው ፡ ቃሉ ፡ የሚለው ፡ እን ዲህ ፡ ነው ።

ሕይወቴን ፡ በሙሉ ፡ ዐልጋ ፡ ላይ ፡ ታስሬ ፤
ታምሜ ፡ ስማቅቅ ፡ ስንገላታ ፡ ኖሬ ።
ሥቃዬን ፡ ጨርሼ ፡ ይኸው ፡ ዛሬ ፡ ገና ፤
እንቅልፌን ፡ አገኘሁ ፡ ማረፌ ፡ ነውና ።
የምትሄዱ ፡ በዚህ ፡ በመቃብር ፡ ቦታ ፤
እንዳትቀሰቅሱኝ ፡ እለፉ ፡ በርጋታ ።


* * *

## አውራ ፡ ዶሮ ፤ ድመትና ፡ የአይጥ ፡ ግልገል ።

የትም ፡ የትም ፡ ቢሆን ፡ ሄዳ ፡ የማታውቅ ፤
አንዲት ፡ ያይጥ ፡ ግልገል ፡ ደጅ ፡ የምትናፍቅ ።
እናትዋ ፡ ሳታያት ፡ ተደብቃ ፡ ወጥታ ፤
ከጕሬዋ ፡ ርቃ ፡ ስትዞር ፡ ቈይታ ።
ተመልሳ ፡ መጥታ ፡ ያየችውን ፡ ሁሉ ፤
ለናትዋ ፡ እንዲህ ፡ ብላ ፡ ነገረቻት ፡ አሉ ።
በጣም ፡ የሚያስደንቅ ፡ የሚያስገርም ፡ ወሬ ፤
እናቴ ፡ ላውራልሽ ፡ ያየሁትን ፡ ዛሬ ።
ተራራ ፡ ቍልቍለት ፡ ወጥቼ ፡ ወርጄ ፤
ስሙ ፡ እማይታወቅ ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ ሄጄ ፤
ዓለምን ፡ ስጐበኝ ፡ ስጓዝ ፡ ወደ ፡ ታች ፤



አንዱ ፡ የዋህ ፡ መሳይ ፡ አይኖቹ ፡ የማያምሩ ፤
ረጅም ፡ ጢም ፡ ያለው ፡ ከንፈሩ ፡ ከዳሩ ።
ጅራቱ ፡ ረጅም ፡ ነው ፡ ገላውም ፡ ልስልስ ፤
የኛን ፡ የመሰለ ፡ ጠጕር ፡ የሚለብስ ።
ፊቱ ፡ የተዋበ ፡ ደርባባ ፡ የረጋ ፤
እኔ ፡ ላጫውተው ፡ ወደሱ ፡ ስጠጋ ።
እንደኛው ፡ ቀኸርቃግ ፡ የተንቀዋለለ ፤
የቀይ ፡ ሥጋ ፡ ቁንጮ ፡ ራሱ ፡ ላይ ፡ ያለ ።
ባረማመዱ ፡ እንኳ ፡ በጣም ፡ የሚኩራ ፤
ሲመለከቱትም ፡ መልኩ ፡ የሚያስፈራ ።
ባሽባሪው ፡ ድምጡ ፡ ጮኸና ፡ ቈይቶ ፤
ሁለት ፡ እጅ ፡ መሳይ ፡ ከጐያው ፡ ዘርግቶ ።



አራግፎ ፡ እንደ ፡ ቁርበት ፡ አንዴ ፡ ቢያንኳኳብኝ ፤
የተከታተለኝ ፡ መስሎኝ ፡ የመጣብኝ ።
ወደዚያው ፡ ልሄድ ፡ ሳለውሁ ፡ ተነሥቼ ፤
ደነገጥሁኝና ፡ መሄዱንም ፡ ትቼ ።
ተመልሼ ፡ እየሮጥሁ ፡ እስኪዝል ፡ ጕልበቴ ፤
እንዲህ ፡ አይምሰልሽ ፡ የቀድሞ ፡ ፍርሀቴ ።

ያን ፡ መልከ ፡ መልካሙን ፡ ሳልተዋወቀው ፤
ሳላነጋግረው ፡ ስሙን ፡ ሳልጠይቀው ።
ፈጥኜ ፡ ሸሽቼ ፡ መጣሁ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፤
የዚያኛውን ፡ ማማር ፡ ባየሽው ፡ እናቴ ።
እዚያ ፡ ምን ፡ ወሰደሽ ፡ አንቺ ፡ ቅልብልብ ፤
አይጦች ፡ ስትባሉ ፡ የላችሁም ፡ ልብ ።
አይጥ ፡ ሞትዋን ፡ ስትሻ ፡ ስታብዛ ፡ ሩጫ ፤
ሄዳ ፡ ታሸታለች ፡ የድመት ፡ አፍንጫ ፤
ሲባል ፡ የነበረው ፡ እስከነ ፡ ተረቱ ፤
ባንቺ ፡ ላይ ፡ ደረሰ ፡ በክልፍልፈቱ ።
ያ ፡ ደግ ፡ ገር ፡ መስሎ ፡ ፊቱ ፡ የሚታይ ፤
ድመት ፡ የሚባለው ፡ አውሬ ፡ አይደለሞይ ፤
መልኩ ፡ ቅልስልስ ፡ ነው ፡ ያ ፡ ክፉ ፡ አታላይ ።
ዋ ፡ የሠራው ፡ ሥራ ፡ እሱ ፡ በኛ ፡ ላይ ።
ባታውቂው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ጥንቱን ፡ ሲፈጠር ፤
አጥፊያችን ፡ እሱ ፡ ነው ፡ የትውልዳችን ፡ ጠር ።
ይልቅስ ፡ ቀውላላው ፡ የደነገጥሽለት ፤
እኛን ፡ የሚጐዳ ፡ ክፋትም ፡ የለበት ።
ስሙም ፡ አውራ ፡ ዶሮ ፡ ይሉሻል ፡ እሱ ፡ ነው ፤
እንዲያውም ፡ አንዳንዶ ፡ ሰው ፡ ሊበላ ፡ ሲያርደው ።
ለእኛም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያገለግለናል ፤
አጥንቱና ፡ ሥጋው ፡ ሲጣል ፡ ይተርፈናል ።
ብላ ፡ እናቲቱ ፡ እየዘረዘረች ፤
ሁሉን ፡ አስረድታ ፡ ለልጇዋ ፡ መከረች ።
የመልኩ ፡ ደም ፡ ግባት ፡ ይመር ፡ አይመር ፤
ሰው ፡ ጠባዩ ፡ ታውቆ ፡ ፊት ፡ ሳይመረመር ።
መልኩን ፡ አይቶ ፡ ብቻ ፡ ይረባል ፡ አይረባም ፤
ክፉ ፡ ነው ፡ ደግ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ አይገባም ።

* * *



## የአንድ ፡ ዐዋቂ ፡ መልስ ።

አንድ ፡ ዐዋቂ ፡ ሰውና ፡ አንድ ፡ ማይምን ፡ በጀልባ ፡ ሲሄዱ ፡ ትልቅ ፡ ነፋስ ፡ ተነሥቶ ፡ ጀልባውን ፡ ሊገለብጠው ፡ በወዲያና ፡ በወዲህ ፡ እያንገላታው ፡ በጣም ፡ የሚያስፈራ ፡ ሆነ ። ዐዋቂው ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ፈርቶ ፡ ተንቀጠቀጠ ። ማይምኑ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ሳይፈራ ፡ ጀልባው ፡ እንዳይገለበጥባቸው ፡ ከማዕበሉ ፡ ጋራ ፡ እየታገለ ፡ ከብዙ ፡ ጭንቅ ፡ በኋላ ፡ በደኅና ፡ ከጠረፍ ፡ ደረሱ ።

ማይምኑ ፡ በጣም ፡ እየሣቀ ፡ አዬ ፡ የኛ ፡ ሊቅ ፡ እኔ ፡ ደንቆሮ ፡ የተባልኹት ፡ ሰው ፡ ምንም ፡ ሳልፈራ ፡ አንተ ፡ ተምረሀል ፤ ብዙ ፡ ነገር ፡ ታውቃለህ ፡ የተባልኸው ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ በፍርሀት ፡ ስትንቀጠቀጥ ፡ በማየቴ ፡ እጅግ ፡ አድርጎ ፡ ያሥቀኛል ፡ እያለ ፡ ቢያሾፍበት ፤ ዐዋቂው ፡ ተናዶ ፡ አንተ ፡ ያልፈራህበት ፡ ምክንያት ፡ ብትኖርም ፤ ብትሞትም ፡ ለዓለም ፡ ምንም ፡ የማታጐድል ፡ መሆንህን ፡ ስለምታውቀው ፡ ነው ። እኔ ፡ ግን ፡ ብሞት ፡ ለዓለም ፡ ብዙ ፡ እንደማጐድል ፡ ዐውቃለሁና ፡ ሞትን ፡ በጣም ፡ አድርጌ ፡ መፍራቴ ፡ ለዚህ ፡ ነው ፡ አለው ።

የተማሩ ፡ ሰዎች ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ የሚመልሱት ፡ መልስ ፡ አያጡም ፡ ለማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ይህን ፡ የጻፍንላችሁ ፡ ይህ ፡ ዐዋቂ ፡ ማይምኑ ፡ ስለ ፡ ሣቀበት ፡ በንዴት ፡ የተናገረው ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ የተገባ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ አይደለም ።

በሞት ፡ ፊት ፡ ድኻና ፡ ባለጸጋ ፤ ጐበዝና ፡ ፈሪ ፤ ትልቅና ፡ ትንሽ ፤ ዐዋቂና ፡ ደንቆሮ ፡ ሁሉም ፡ ትክክል ፡ ናቸው ። ሁሉም ፡ ደግሞ ፡ ሞትን ፡ መፍራት ፡ አለባቸው ።

## መልክና ፡ መስታዎት ።

እጅግ ፡ አድርጎ ፡ መልኩ ፡ የሚያስቀይም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበር ። እሱም ፡ በሕይወቱ ፡ መስታዎት ፡ አግኝቶ ፡ መልኩን ፡ በዐይኖቹ ፡ ተመልክቶት ፡ አያውቅም ፡ ነበር ። መልኩ ፡ የማያምር ፡ አስቀያሚ ፡ መሆኑንም ፡ የሚሰማው ፡ የሐሜት ፡ ሐሜት ፡ እንጂ ፤ ፊት ፡ ለፊት ፡ ገልጦ ፡

ሊነግረው ፡ የደፈረ ፡ ሰው ፡ እንኳ ፡ አልነበረም ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ድንገት ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ የግድግዳ ፡ መስታዎት ፡ አግኝቶ ፡ መልኩን ፡ ሊመለከት ፡ ወደ ፡ እሱ ፡ ቀረበ ። እውነትም ፡ መልኩን ፡ ቢመለከተው ፡ በጣም ፡ የሚያስከፋ ፡ ሆኖ ፡ አገኘው ። ወደ ፡ መስታዎቱም ፡ በጣም ፡ ተጠግቶ ፡ ትክ ፡ ብሎ ፡ ቢያስተውል ፡ መልክ ፡ ጥፉነቱ ፡ እጅግ ፡ የሚያስ ቅቅና ፡ የሚያሳፍር ፡ ሆኖ ፡ አገኘው ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በልቡ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ይህ ፡ የምመለከተው ፡ የሚያስጠይፍ ፡ መልክ ፡ እውነት ፡ የእኔ ፡ ሆኖ ፡ ነውን ? በሰው ፡ አፍ ፡ ስታማ ፡ የምሰማውስ ፡ ለካ ፡ እርግጥ ፡ ኖሮ ዋልን ? በዓለምም ፡ ላይ ፡ የምኖረው ፡ እንደዚህ ፡ የሚያስከፋ ፡ መልክ ፡ ይዤ ፡ ነውን ? ይህ ፡ ሁሉ ፡ በፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ። በዚህ ፡ መስታ ዎት ፡ ውስጥ ፡ የምመለከተውን ፡ ያህል ፡ የእኔ ፡ መልክ ፡ አያስከፋም ። በእውነቱ ፡ ነገር ፡ እኔ ፡ ቆንጆ ፡ ነኝ ። ቁንጅናዬንም ፡ ልቡናዬ ፡ ያውቀዋል ። ይህ ፡ መስታዎት ፡ ግን ፡ ሐሰተኛ ፡ ነው ፤ ለሰው ፡ ያለ ፡ መልኩ ፡ መጥፎ ፡ መልክ ፡ ይሰጣል ። በዚህ ፡ ቦታም ፡ ተቀምጦ ፡ ሊኖር ፡ አይገባውም ፡ ብሎ ፡ ትልቅ ፡ ድንጋይ ፡ አነሣና ፡ ወርውሮ ፡ መስታዎቱን ፡ ሰባበረው ።

መስታዎት ፡ በምን ፡ ይመስላል ? እውነቱን ፡ ገልጦ ፡ በሚናገር ፡ ሰው ፡ ይመሰላል ። መልክ ፡ ደግሞ ፡ በምን ፡ ይመሰላል ? በመጥፎ ፡ ጠባይ ፡ ይመሰላል ። እኛ ፡ ግብዞቹ ፡ የአዳም ፡ ልጆች ፡ ሁላችንም ፡ በጠባ ያችን ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ክፋት ፡ ለመስማትና ፡ ለማወቅ ፡ አንፈልግም ። ልቡናችንም ፡ ሲረዳው ፡ ትዕቢታችን ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ አይቀበልም ። ጉድለታ ችንን ፡ ደፍሮ ፡ የሚነግረንም ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ተቈጥቶ ፡ መስ ታዎቱን ፡ እንደ ፡ ሰበረው ፡ እኛም ፡ እንዲሁ ፡ ያነን ፡ ሰው ፡ እንጣላዋለን ። እኛ ፡ ግብዞቹ ፡ የምንወደው ፡ የሕሊናችንን ፡ ዐይን ፡ ጨፍነን ፡ አለ ፡ ባሕ ርያችን ፡ መልካም ፡ ባሕርይ ፡ አለን ፡ ብለን ፤ እያሰብን ፡ ልባችንን ፡ ሐሰ ተኛ ፡ ደስታ ፡ መመገብ ፡ የገዛ ፡ ራሳችንን ፡ መልሰን ፡ እያታለልን ፡ ለመ ኖር ፡ ነው ። ትዕቢታቸውን ፡ አሸንፈው ፡ እውነትን ፡ የሚወዱና ፡ ጠባ ያቸውን ፡ የሚያሻሽሉ ፡ ሰዎች ፡ በጣም ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ።



## ትክክለኛ ፡ ዳኛ ።

በሚሠራው ፡ በዳኝነት ፡ ሥራ ፡ ፍርድ ፡ እንዳይጐድልበት ፡ በጣም ፡ አድርጎ ፡ የሚጠነቀቅ ፡ አንድ ፡ እውነተኛ ፡ ዳኛ ፡ ነበር ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ወዳጁ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ተጣልቶ ፡ ከሰ ሰና ፡ ወደ ፡ እሱ ፡ ዘንድ ፡ መጣ ። ግን ፡ ከመቋቋማቸው ፡ በፊት ፡ ወዳጁ ፡ እዳኛው ፡ ቤት ፡ ሄዶ ፡ እንዲህ ፡ አለው ። ከእቶ ፡ እገሌ ፡ ጋራ ፡ ተካሰሰን ፡ ለሙግት ፡ ከአንተ ፡ ላይ ፡ መቅረባችን ፡ ነውና ፡ እንግዲህ ፡ የወዳጅነት ህን ፡ ሥራ ፡ እንድትሠራልኝ ፡ አደራህን ፡ አለው ።

ዳኛው ፡ ግን ፡ እኔ ፡ በዳኝነቴ ፡ የሁለታችሁንም ፡ ነገር ፡ ያለ ፡ አድ ልዎ ፡ በማመዛዘን ፡ እመለከታለሁ ፡ እንጂ ፡ ወዳጄ ፡ ነህ ፡ ብዬ ፡ ላንተ ፡ የምሠራህል ፡ ነገር ፡ የለም ፡ አለው ። ወዳጁ ፡ ተቈጥቶ ፡ ያንተ ፡ ሥራ ፡ ዳኝነት ፡ ነው ፡ በዚህ ፡ በዳኝነት ፡ ሥራህ ፡ እኔን ፡ ወዳጅህን ፡ ልትረዳ ኝና ፡ ልትጠቅመኝ ፡ ካልፈቀድህ ፡ እንግዴህ ፡ ያንተ ፡ ፍቅር ፡ ለኔ ፡ ምን ፡ ይጠቅማኛል ፡ አለው ። ዳኛውም ፡ መልሶ ፡ አንተስ ፡ ደግሞ ፡ በእውነት ፡ ወዳጄ ፡ ከሆንህ ፡ ፍርድ ፡ ማጕደልን ፡ የሚያህል ፡ ትልቅ ፡ ኀጢአት ፡ እንዳልሠራ ፡ ሲሆን ፡ ትከለክለኝ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፤ ሕሊናዬንና ፡ ክብሬን ፡ የሚያዋርድ ፡ ይህን ፡ ያልተገባ ፡ ሥራ ፡ እንድሠራ ፡ የምትፈቅድ ፡ ወዳጅ ፡ ከሆንህ ፡ ወዳጅነትህና ፡ ፍቅርህ ፡ ከቶ ፡ ለምን ፡ ሊጠቅመኝ ፡ የሚችል ፡ መሰሎህ ፡ ይሆን ፡ አለው ፡ ይባላል ።

ሰው ፡ ወዳጁን ፡ ሲወደው ፡ በግል ፡ ገንዘቡ ፡ ሊጠቅመው ፡ ይች ላል ፡ እንጂ ፤ ከእግዚአብሔርና ፡ ከመንግሥት ፡ አደራ ፡ የተቀበለውን ፡ የራሱ ፡ ገንዘብ ፡ ያልሆነውን ፡ የተቀደሰውን ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ እያጐ ደለ ፡ ወዳጁን ፡ ቢጠቅምበትና ፡ ጠላቱን ፡ ቢጐዳበት ፡ በምድር ፡ በሥ ጋው ፤ በሰማይ ፡ በነፍሱ ፡ ይዋረድበታል ።

* * *

## የዱባ ፡ ፍሬና ፡ የሾላ ፡ ፍሬ ።

አንዱ ፡ ባላገር ፡ ሰው ፡ እገበያ ፡ ውሎ ፤
ሲመለስ ፡ ቢደክመው ፡ በፀሐይ ፡ ቃጠሎ ።
ከሾላ ፡ ዛፍ ፡ ጥላ ፡ ሄዶ ፡ ተጠግቶ ፤
ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ እየ ፡ ዛፉ ፡ አፍርቶ ፤
ቁመቱን ፡ ውፍረቱን ፡ ግንዱን ፡ ተመልክቶ ።
ፍሬው ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ዛፉ ፡ በጣም ፡ ትልቅ ፤
ሆኖ ፡ መፈጠሩን ፡ እያየ ፡ ሲደነቅ ።



ከሾላው ፡ አጠገብ ፡ ጥቂት ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፤
እየ ፡ ከነፍሬው ፡ የዱባ ፡ ዕንጨት ፡ በቅሎ ።
ያንዱን ፡ ፍሬ ፡ ካንዱ ፡ መዝኖ ፡ አስተያይቶ ፤
እንዲህ ፡ ሲል ፡ ፈረደ ፡ ባምላኩ ፡ ሥራ ፡ ገብቶ ።



እውነትም ፡ ፈጣሪ ፡ ዓለምን ፡ ዘርግቶ ፤
ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ሲሠራው ፡ አስማምቶ ፤
የተፈጠሩ ፡ ለት ፡ እነዚህ ፡ ሁቱ ፡
በጣም ፡ ተሳስቶዋል ፡ ባለመመልከቱ ።
የሾላ ፡ ዛፍ ፡ ትልቅ ፡ ተራራ ፡ የሚያህል ፤
ፍሬው ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ጠጠር ፡ የምትመስል ።
የዱባ ፡ ዕንጨት ፡ ሽባ ፡ መሬት ፡ የሚጐተት ፤
ፍሬው ፡ ጕልቻ ፡ አህሎ ፡ ተወዝፎዋል ፡ መሬት ።
ለትንሹ ፡ ትልቅ ፡ ለትልቁ ፡ ትንሽ ፤
አዛውሮ ፡ ሰጥቶ ፡ እንዲህ ፡ ከሚያበላሽ ።
ትልቁን ፡ አውጥቶ ፡ ሾላው ፡ ላይ ፡ ቢሰቅለው ፤
ትንሹን ፡ አውርዶ ፡ ዱባው ፡ ላይ ፡ ቢጥለው ።
ይስማማ ፡ ነበረ ፡ ሲሆን ፡ በየመልኩ ፤
ሲያሸክሙትማ ፡ መጠኑን ፡ ሳይለኩ ።
ያስጠይፍ ፡ የለም ፡ ወይ ፡ ለተመለከተው ፤
ዱባ ፡ ፍሬው ፡ ከብዶት ፡ መሬት ፡ ሲጐትተው ።
አልገባኝም ፡ ከቶ ፡ የዚህ ፡ ነገር ፡ ፍች ፤
ለምን ፡ አደረገው ፡ የላዩን ፡ አታች ።
እንዴት ፡ እንዲህ ፡ አርጎ ፡ ፈጠረው ፡ እግዜር ፤
ብሎ ፡ ይኸን ፡ ምስጢር ፡ በመመራመር ።
ዛፉን ፡ ተጠግቶ ፡ ትንሹ ፡ ፈላስፋ ፤
ከማሰቡ ፡ ብዛት ፡ ደክሞት ፡ እንቀላፋ ።
እዚያም ፡ እደተኛ ፡ እንቅልፉ ፡ ወስዶት ፤
አንድ ፡ የሾላ ፡ ፍሬ ፡ ነፋስ ፡ የጣላት ፤
ካፍንጫው ፡ ላይ ፡ ዐርፋ ፡ ብትመታው ፡ ድንገት ፤
ደንግጦ ፡ ተነሣ ፡ ሕመም ፡ ተሰምቶት ፤
ፈጥኖም ፡ የነካውን ፡ ነገር ፡ ለማየት ፤
ተነሥቶ ፡ ቢያስተውል ፡ ወዲያው ፡ እንደ ፡ ነቃ ፤
የሾላ ፡ ፍሬ ፡ እየ ፡ ደረቱ ፡ ላይ ፡ ወድቃ ።
በጁም ፡ አፍንጫውን ፡ ቶሎ ፡ ዳበሰና ፤
ኧረ ፡ ጉድ ፡ ነው ፡ አለ ፡ ደምቻለሁና ።

አሁን ፡ ገና ፡ ገባኝ ፡ ትልቁ ፡ ስሕተቴ ፤
ከማሰቤም ፡ ደግሞ ፡ ይባስ ፡ የድፍረቴ ፤
አበላሽ ፡ ብዬ ፡ ካምላክ ፡ መምዋገቴ ፤
እንዲህ ፡ ባጭር ፡ ነገር ፡ ሳለ ፡ መረታቴ ።
ቢፈጸምስ ፡ ኖሮ ፡ የኔ ፡ መቀባጠር ፤
ከዚያ ፡ ላይ ፡ ወድቆብኝ ፡ ዱባን ፡ ያህል ፡ ነገር ።
አናቴን ፡ ፈጥፍጦ ፡ በገደለኝ ፡ ነበር ።
እንዲህ ፡ እንዲሆን ፡ ግን ፡ እግዜር ፡ አልፈቀደም ፤
እሱ ፡ ሁሉን ፡ ያውቃል ፡ እንደኔ ፡ አላበደም ።
የኔንስ ፡ ማበዴን ፡ አየሁት ፡ እያለ ፤
ዐሳቡን ፡ መልሶ ፡ ንቆ ፡ እያቃለለ ።
እግዜር ፡ ተሳሳተ ፡ ብሎ ፡ ማለት ፡ ከንቱ ፤
መሆኑን ፡ ተረድቶት ፡ ሄደ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ።
በምትሠራው ፡ ሥራ ፡ መቼም ፡ አትሳሳት ፤
የለብህም ፡ አንተ ፡ መታለል ፡ ወይ ፡ መርሳት ።
እኛ ፡ ግን ፡ ሰዎቹ ፡ ጥንቱን ፡ ስንፈጠር ፤
ጠባይ ፡ ሆኖብናል ፡ ሁሉን ፡ መቀባጠር ።
እያደር ፡ ይታያል ፡ ጥራቱ ፡ ሲያበራ ።
እንከን ፡ የለበትም ፡ በምትሠራው ፡ ሥራ ።
ሰዎች ፡ ተሳስተው ፡ ትክክል ፡ ሳይፈርዱ ፤
ይጠረጥሩሀል ፡ እየዘላበዱ ።
ዘላለም ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ የፍርዱ ፡ መምህር ፤
ስሕተት ፡ የሌለብህ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔር ።
አንተን ፡ የሞገተ ፡ ተሳሳትህ ፡ ብሎ ፤
ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አይቈይም ፡ ይረታል ፡ በቶሎ ።

* * *



## ሰቅራጥስ ።

ሰቅራጥስ ፡ በሚባለው ፡ በትልቁና ፡ በስመ ፡ ጥሩው ፡ የግሪክ ፡ ፈላስፋ ፡ አርኬላዎስ ፡ የሚባለው ፡ የመቄዶንያ ፡ ንጉሥ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ መጥተህ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቴ ፡ ተቀመጥ ፡ እኔም ፡ ሀብትና ፡ ክብር ፡ ሰጥቼህ ፡ በምቾትና ፡ በደስታ፡ እኖርሀለሁ ፡ ብሎ ፡ ቢልክበት ፡ በአገሬ ፡ በአቴና ፡ ከተማ ፡ እህል ፡ ርካሽ ፡ ነው ፤ ውሃም ፡ ያለ ፡ ዋጋና ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ልብ ፡ ይገኛል ። ከዚያ ፡ ከርስዎ ፡ አገር ፡ ድረስ ፡ የሚያደክም ፡ ችግር ፡ አላገኘኝም ። ግን ፡ መልካም ፡ ዐሳብ ፡ ስለ ፡ ዐሰቡልኝ ፡ አመሰግንዎታለሁ ፡ ብሎ ፡ ሰቅራጥስ ፡ ለንጉሡ ፡ መለሰለት ፡ ይባላል ።

ፈላስፋው ፡ ይኸን ፡ ማለቱ ፡ በባዕድ ፡ አገር ፡ ሀብታም ፡ ሆኖ ፡ ከመኖር ፡ ይልቅ ፡ በተወለዱበት ፡ አገር ፡ ተቸግሮ ፡ መኖር ፡ መሻሉን ፡ ሲናገር ፡ ነው ። አንድም ፡ ደግሞ ፡ ከእህልና ፡ ከውሃ ፡ በቀር ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ሌላው ፡ ሁሉ ፡ ትርፍ ፡ ነገር ፡ <u>መሆኑን ፡ ሲያስተምረን</u> ፡ ነው ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ከተማሪዎቹ ፡ መካከል ፡ አንደኛው ፡ ተነሥቶ ፡ መምህር ፡ ሆይ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ መርምረው ፡ካገኙዋቸው ፡ ዕውቀቶች ፡ ሁሉ ፡ የሚበልጡት ፡ የትኞቹ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ሰቅራጥስን ፡ ቢጠይቀው ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ከመረመርሁ ፡ በኋላ ፡ ከሁሉም ፡ ዕውቀቴ ፡ የበለጠ ፡ ዋና ፡ ሆኖ ፡ ያገኘሁት ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ እሱም ፡ ምንም ፡ አለማወቄን ፡ መረዳቴን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ትልቁ ፡ ፈላስፋ ፡ መለሰ ።

* * *

## ኤ ዞ ፕ ።

ኤዞፕ ፡ የሚባለው ፡ የግሪክ ፡ ሊቅ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በመንገድ ፡ ሲያልፍ ፡ አንድ ፡ ኬለኛ ፡ አቆመውና ፡ ወዴት ፡ ትሄዳለህ ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ ኤዞፕ ፡ የምሄድበትንም ፡ አላውቀው ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። ኬለኛው ፡ በዚህ ፡ ባልተለመደ ፡ መልስ ፡ ተቈጥቶ ፡ እስር ፡ ቤት ፡ አገባው ። ጥቂት ፡ ቈይቶም ፡ መጥቶ ፡ አንተ ፡ ሰው ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ የምትሄደው ፡ ብዬ ፡ ብጠይቅህ ፡ አልናገርም ፡ብለህ ፡ እንግዲህ ፡ እንቢ ፡ ማለ

ትህ ፡ ነው ? ብሎ ፡ ቢናገረው ፡ ኤቦፕ ፡ መለሰና ፡ ይልቅስ ፡ ልቀቀኝና ፡ ልሂድበት ፡ ለወደፊቱም ፡ ቢሆን ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ጥያቄ ፡ አይልመድህ ፡ ወዴት ፡ ትሄዳለህ ፡ ብለህ ፡ የጠየቅኸኝ ፡ አሁንስ ፡ ቢሆን ፡ የምሄድበትን ፡ ቦታ ፡ ዐውቄ ፡ ለመናገር ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ይቻለኝ ፡ መስሎህ ፡ ነው ፡ ሌላው ፡ ይቅርና ፡ እስኪ ፡ እዚህ ፡ እስር ፡ ቤት ፡ እንደምገባ ፡ በምን ፡ ዐውቀው ፡ ኖሮዋል ፡ ብሎ ፡ በቊጣ ፡ ቃል ፡ ቢናገር ፡ ኬለኛው ፡ ይህስ ፡ ቀልደኛ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሥቆ ፡ ፈታና ፡ ለቀቀው ።

* * *

<u>ተጫዋች ፡ ሰው ።</u>

አንድ ፡ ተጫዋች ፡ ሰው ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በመንገድ ፡ ሲያልፍ ፡ ነገር ፡ በሆዱ ፡ ገብቶ ፡ ያሰላስል ፡ ኖሮ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ተላላፊ ፡ መንገደኛ ፡ ሰው ፡ አይቶ ፡ ጤና ፡ ይስጥልኝ ፡ አለና ፡ ሰላምታ ፡ ሰጠው ።

ግን ፡ ወዲያው ፡ ልብ ፡ ብሎ ፡ ቢመለከተው ፡ በመልክ ፡ እንደ ፡ ተሳሳተ ፡ ተረዳውና ፡ ቀረብ ፡ ብሎ ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ ይቅርታህን ፡ አድርግልኝ ፡ ሰላምታ ፡ የሰጠሁህ ፡ አንድ ፡ የማውቀው ፡ ሰው ፡ አለ ፡ በገጥታህ ፡ እሱን ፡ መስለኸኝ ፡ ነው ፡ አለው ። ያ ፡ መንገደኛ ፡ ደግሞ ፡ በበኩሉ ፡ ኧረ ፡ ታልህስ ፡ እኔም ፡ እንደዚሁ ፡ መጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ እንዳየሁህ ፡ አንድ ፡ ወዳጄ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ አለ ፡ እሱን ፡ መስለኸኝ ፡ ሰላምታ ፡ ልሰጥህ ፡ ቃጥቶኝ ፡ ነበረ ፡ አለው ። ተጫዋቹ ፡ ሰው ፤ ይኸን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ፊቱን ፡ በደስታ ፡ አብርቶ ፡ እየሣቀ ፡ የተሳሳትነው ፡ ለካ ፡ ሁለታችንም ፡ ነንና ፡ እንግዲያውስ ፡ በል ፡ ተወው ፡ እኔም ፡ እኔ ፡ አይደለሁ ፤ አንተም ፡ አንተ ፡ አይደለህ ፡ ብሎት ፡ መንገዱን ፡ ቀጠለ ።

* * *

እጅግም ፡ ስለት ፡ ይቀዳል ፡ አፎት ፤
እጅግም ፡ <u>ብልኀት ፡ ያደርሳል ፡</u> ከሞት ፤

ዕድሜያቸውን ፡ ሙሉ ፡ መጽሐፍ ፡ በማንበብና ፡ ጥበብን ፡ በመመርመር ፡ የሚኖሩ ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። እነሱም ፡ በጣም ፡ የጠለቀና ፡ የረቀቀ ፡ ዕውቀት ፡ ስለ ፡ ነበራቸው ፡ ለጥበባችን ፡ የተገባ ፡ ክብርና ፡



ማዕርግ ፡ ማግኘት ፡ ይገባናል ፡ ብለው ፡ ሥራ ፡ ለመለመንና ፡ ደጅ ፡ ለመጥናት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሊሄዱ ፡ ጕዞ ፡ ጀመሩ ። የዘመናቸውም ንጉሥ ፡ ጥበብ ፡ የሚወድ ፡ መሆኑን ፡ ያውቁ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፤ ይህ ፡ ምኞታቸው ፡ እንደሚፈጸምላቸው ፡ ባለመጠራጠር ፡ ተረድተውት ፡ እየተጫወቱ ፡ ሲሄዱ ፡ እነሱ ፡ ወደሚሄዱበት ፡ ከተማ ፡ የሚሄድ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ መንገደኛ ፡ አግኝቶዋቸው ፡ አብሮዋቸው ፡ ይጓዝ ፡ ጀመረ ። እርሱም ፡ የተማረው ፡ ትምህርቱ ፡ ጥቂት ፡ ነበር ። ግን ፡ ከነሱ ፡ የበለጠ ፡ የተፈጥሮ ፡ አስተዋይነት ፡ ነበረው ። እነዚያ ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ የጥበብን ፡ ነገር ፡ አንሥተው ፡ እየተከራከሩና ፡ ወደፊትም ፡ የሚያገኙትን ፡ ክብር ፡ እየተጫወቱ ፡ ቢሄዱ ፡ ካንድ ፡ ጫካ ፡ ውስጥ ፡ ደረሱ ። እዚያም ፡ ቦታ ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ አንበሳ ፡ ሞቶ ፡ ኖሮ ፡ አጥንቱ ፡ በያለበት ፡ ተበታትኖ ፡ አገኙ ። ከሦስቱ ፡ ሀኞቿዎች ፡ አንደኛው ፡ እንግዴህ ፡ የዕውቀታችን ፡ ልክ ፡ የሚታወቀው ፡ አሁን ፡ ነው ። እነሆ ፡ ይህ ፡ ተበታትኖ ፡ የምናየው ፡ የአንበሳ ፡ ዐጥንት ፡ ነው ። እኔ ፡ ጥቂት ፡ ቃል ፡ ደግሜ ፡ ይህ ፡ ዐጥንት ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስቦ ፡ ቀድሞ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ በየቦታው ፡ ገብቶ ፡ እንዲገጣጠም ፡ አደርገዋለሁ ፡ አለ ። ሁለቱ ፡ ባልንጀሮቹ ፡ እስኪ ፡ በል ፡ አድርግ ፡ እንደይህ ፡ አሉት ። እሱም ፡ ድግምቱን ፡ ደገሞ ፡ እውነትም ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ የአንበሳውን ፡ ዐጥንት ፡ ሁሉ ፡ በየቦታው ፡ ገብቶ ፡ እንዲገጣጠም ፡ አደረገው ።

ሁለተኛው ፡ ዐዋቂ ፡ ይኸንን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ሥጋውን ፡ መልሼ ፤ ደሙን ፡ ሞልቼ ፡ ቆዳውን ፡ አለብሰዋለሁ ፡ ብሎ ፡ ድግምቱን ፡ ደገመና ፡ እሱም ፡ እንዲሁ ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ አደረገ ። ያ ፡ ብዙ ፡ ትምህርት ፡ የሌለው ፡ አራተኛው ፡ መንገደኛ ፡ የአንበሳው ፡ ዐጥንት ፡ እንደ ፡ ተገጣጠመና ፡ ሥጋውን ፤ ደሙንና ፡ ቆዳውን ፡ አግኝቶ ፡ አካላቱ ፡ እንደ ፡ ሞላለት ፡ በዐይኑ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፤ የነገሩ ፡ አኳኋን ፡ አላምርህ ፡ ስላለው ፡ ወደ ፡ ግራ ፤ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ደግሞም ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ተገላምጦ ፡ ቢመለከት ፡ አንድ ፡ ዛፍ ፡ አጠገቡ ፡ አየ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ልቡ ፡ ረጋ ። ሦስተኛው ፡ ዐዋቂ ፡ ተነሣና ፡ እናንተ ፡ ይህነን ፡ ብታደርጉ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ የሕይወት ፡ ትንፋሽ ፡ የሚሰጥ ፡ ድግምት ፡ ዐውቃለሁ ፡

ብሎ ፡ ሊደግም ፡ ሲጀምር ፡ አራተኛው ፡ መንገደኛ ፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡
ይህ ፡ እያያዛችሁ ፡ ከቶ ፡ አላማረኝም ፡ እናንተም ፡ ዕውቀታችሁን ፡
ብቻ ፡ እንጂ ፤ ይህ ፡ የምታስነሡት ፡ አውሬ ፡ አንበሳ ፡ መሆኑን ፡ ዘንግታች
ሁታል ፡ መሰለኝ ። ነፍስ ፡ ዘርቶ ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከያዝነው ፡
ብትር ፡ በቀር ፡ የምንከላከልበት ፡ ሌላ ፡ የበቃ ፡ መሣሪያ ፡ በእጃችን ፤
ስለሌለ ፡ ሁላችንንም ፡ ያበላሸናልና ፡ ተዉ ፡ ይቅር ፡ ብሎ ፡ ቢያሳስባ
ቸው ፡ ያ ፡ መጀመሪያ ፡ የአንበሳውን ፡ ዐጥንት ፡ የገጣጠመ ፡ ዐዋቂ ፡
ከት ፡ ብሎ ፡ ሣቀና ፡ አዬ ፡ የኛ ፡ ጅል ፡ ደንቈሮ ፡ እኛ ፡ የምንሠራውን ፡
ጥበብ ፡ እየተመለከትህ ፡ መደነቅ ፡ አነሰህና ፡ ምን ፡ ጥልቅ ፡ አርጎህ ፡
በማታውቀው ፡ ሙዩያ ፡ ገብተህ ፡ ምክር ፡ ልትሰጠን ፡ ደፈርህ ፡ ብሎ ፡
ዘለፈው ። ለአንበሳው ፡ ሥጋ ፤ ደምና ፡ ቆዳ ፡ የመለሰለት ፡ ሁለተኛው ፡
ዐዋቂ ፡ ደግሞ ፡ ተቈጥቶ ፡ ምንስ ፡ ዐሥር ፡ ደንቈሮ ፡ ብትሆን ፡ ከሞት ፡
ያስነሣነው ፡ አውሬ ፡ መልሶ ፡ እኛኑ ፡ ይበላናል ፡ ብለህ ፡ ማሰብህ ፡ ከጅ
ልም ፡ ጅል ፡ ነህ ፡ ብሎ ፡ ሣቀበት ። እንግዲያውስ ፡ ለኔ ፡ ለደንቈሮው ፡
ፍቀዱልኝና ፡ እዚያ ፡ እዛፍ ፡ ላይ ፡ እስከወጣ ፡ ድረስ ፡ ጊዜ ፡ ስጡኝ ፡ ብሎ ፡
ሸሽቶ ፡ ከዛፉ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ መጨረሻቸውን ፡ ይመለከት ፡ ጀመር ።

ሦስተኛው ዐዋቂ ፡ ከጓደኞቹ ፡ አንሼ ፡ አልቀርም ፡ በማለት ፡ ድግ
ምቱን ፡ ደግሞ ፡ ሲጨርስ ፡ አንበሳው ፡ ነፍስ ፡ ዘርቶ ፡ ተነሥቶ ፡ በትራብ ፡
አንጀቱ ፡ ዘልሎ ፡ አጠገቡ ፡ የነበረውን ፡ ነፍስ ፡ የዘራለትን ፡ ሰው ፡ መጀ
መሪያ ፡ በላው ። ቀጥሎ ፡ ሥጋ ፤ ደምና ፡ ቆዳ ፡ የሰጠውን ፡ ሰው ፡ ደገ
መው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ራቡ ፡ ታገሥ ፡ ሲልለት ፡ ዐጥንቱን ፡ የገጣጠ
መለትን ፡ ሰው ፡ ገድሎ ፡ ሬሳውን ፡ ጐትቶ ፡ ወደ ፡ ዋሻው ፡ ይዞት ፡ ሄደ ።

ደንቈሮ ፡ የተባለውን ፡ ሰው ፡ ድንቍርናው ፡ አዳነው ። ሦስቱን ፡ ጥበ
በኞች ፡ ግን ፡ የሠሩት ፡ የጥበብ ፡ ሥራ ፡ አጠፋቸው ። ማንኛውም ፡ ነገር ፡
በመጠን ፡ ሲሆን ፡ መልካም ፡ ነው ። ከመጠን ፡ ሲያልፍ ፡ ግን ፡ ይልቁ
ንም ፡ ፉክክር ፡ ሲጨመርበት ፡ ሌላው ፡ ይቅርና ፡ ያቺ ፡ መልካሚቱ ፡
ጥበብ ፡ እንኳን ፡ ትጐዳለች ፤ ከጥፋትም ፡ ታደርሳለች ።

* * *



## ጽጌ ፡ ረዳና ፡ ደመና ።

የፀሓዩ ፡ ንዳድ ፡ ያጠቃት ፡ በብዙ ፤
ጠውልጎ ፡ የሚታይ ፡ የቅጠልዋ ፡ ወዙ ።
አንዲት ፡ ጽጌ ፡ ረዳ ፡ ቃልዋን ፡ አስተዛዝና ፤
እንዲህ ፡ ተናገረች ፡ ለሰማይ ፡ ደመና ።
ድርቀት ፡ በጣም ፡ ጐድቶኝ ፡ እየኝ ፡ ስንገላታ ፤
እባክህ ፡ ጣልልኝ ፡ የዝናም ፡ ጠብታ ።
ቶሎ ፡ ካላራስኸኝ ፡ ጕልበቴ ፡ እንዲጥናና ፤
ምንም ፡ ተስፋ ፡ የለኝ ፡ መሞቴ ፡ ነውና ።
አሁን ፡ መሄዴ ፡ ነው ፡ ለትልቅ ፡ ጕዳይ ፤
ስመለስ ፡ መጥቼ ፡ ሳልፍ ፡ ባንቺ ፡ ላይ ።
አዘንምልሻለሁ ፡ ጠብቂኝ ፡ እያለ ፤
ምንም ፡ ሳይጥልላት ፡ መንገዱን ፡ ቀጠለ ።
ጕዳዩን ፡ ጨርሶ ፡ ቈይቶ ፡ ሲመጣ ፤
ያቺ ፡ ጽጌ ፡ ረዳ ፡ ሥርዋ ፡ ውሃ ፡ ያጣ ።
እንደዚያ ፡ አስተዛዝና ፡ ጭንቋን ፡ ያዋየችው ፤
የፀሓዩ ፡ ንዳድ ፡ አድርቋት ፡ ቈየችው ።
እስኪጐርፍ ፡ ድረስ ፡ የወንዝ ፡ ውሃ ፡ ሙላት ፤
ወዲያው ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ ዝናቡን ፡ ጣለላት ፤
ግን ፡ ደርቃለችና ፡ አልቻለም ፡ ሊያድናት ።
ሳልደርስላት ፡ ቀረሁ ፡ አዬ ፡ ጉድ ፡ እያለ ፤
ደመናም ፡ ጕዞውን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ቀጠለ ።
ሰውም ፡ እንደዚሁ ፡ ጭንቁን ፡ እያዋየ ፤
በችግሩ ፡ ብዛት ፡ እየተሠቀየ ።
ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ኖሮ ፡ ቈይቶ ፡ ሲጐላላ ፤
የሚረዳው ፡ አጥቶ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ።
ዘመድ ፡ ወዳጆቹ ፡ እንባ ፡ እያፈሰሱ ፡
ተዝካር ፡ ቢያወጡለት ፡ አርባ ፡ ቢደግሱ ፤
ይህ ፡ ሁሉ ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ አይጠቅመውም ፡ ለሱ ።
እውነት ፡ ከወደደው ፡ ሲቸገር ፡ ሲጐዳ ፤
በሕይቱ ፡ ሳለ ፡ ሰው ፡ ወዳጁን ፡ ይርዳ ።

* * *

## በአንድ ፡ ባለጠጋ ፡ በረት ፡ የሆነ ፡ ሁከት ።

ቍጥራቸው ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ የሚጠጋ ፡ የቀንድ ፡ ከብቶች ፡ የነበሩት ፡ አንድ ፡ ከብት ፡ አርቢ ፡ የሆነ ፡ ባለጠጋ ፡ ሰው ፡ እነሆ ፡ ከጥቂት ፡ ቀን ፡ ወዲህ ፡ ከብቶቼ ፡ ሌሊት ፡ ሌሊት ፡ በበረታቸው ፡ ውስጥ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ እየተተራመሱ ፡ ሲታወኩ ፡ ያድራሉ ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በመካከላቸው ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ ሁከት ፡ አልነበረም ። አሁን ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የሆነበት ፡ ምክንያቱ ፡ ጠፍቶኛል ፡ ምን ፡ ይሆን ? ብሎ ፡ ጎረቤቶቹን ፡ ቢያማክራቸው ፤ አስተዋይ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ለዚህ ፡ ነገር ፡ ብልኀቱ ፡ አጭር ፡ ነው ። ሌላ ፡ ትልቅ ፡ በረት ፡ አሠርተህ ፡ ከብቶችህን ፡ ከሁለት ፡ ከፈላቸውና ፡ ለየብቻ ፡ አሳድራቸው ፡ አለው ። ባለጠጋውም ፡ ሽማግሌው ፡ እንዳለው ፡ አደረገ ። ይኸንን ፡ ባደረገ ፡ በማግሥቱ ፡ ከብቶችህ ፡ ዛሬስ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አደሩ ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፤ ያንደኛው ፡ በረት ፡ ከብቶች ፡ ደኅና ፡ አደሩ ፡ ያንደኛው ፡ ግን ፡ ሲተራመሱ ፡ አደሩ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። በል ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ትልቅ ፡ በረት ፡ አሠርተህ ፡ ሲታወኩ ፡ ያደሩትን ፡ ከብቶች ፡ ከሁለት ፡ ከፍለህ ፡ ለየብቻ ፡ አሳድራቸው ፡ አለው ።

አሁንም ፡ ደግሞ ፡ ባለጠጋው ፡ እንዲሁ ፡ ሽማግሌው ፡ እንደ ፡ መከረው ፡ አደረገ ። በማግሥቱም ፡ ቢጠይቀው ፡ ባንዱ ፡ በረት ፡ ያሉት ፡ ከብቶች ፡ ደኅና ፡ አደሩ ፤ ባንደኛው ፡ የነበሩት ፡ ግን ፡ ሲበጠበጡ ፡ አደሩ ፡ አለው ። ሽማግሌውም ፡ መለሰና ፡ እነዚያን ፡ ደኅና ፡ ያደሩትን ፡ ከፊተኞቹ ፡ ጋራ ፡ ቀላቅለህ ፡ ሲታወኩ ፡ ያደሩትን ፡ ከብቶች ፡ አሁንም ፡ ከሁለት ፡ ከፈላቸውና ፡ ለየብቻ ፡ አሳድራቸው ፡ አለው ። እንዲሁ ፡ እያደረገ ፡ የታወኩትን ፡ ከብቶች ፡ ከሁለት ፡ እየከፈለ ፡ ደኅና ፡ ያደሩትን ፡ ግን ፡ ለብቻ ፡ ለይቶ ፡ ከደኅናዎቹ ፡ ጋራ ፡ እየቀላቀለ ፡ ስድስት ፡ ጊዜ ፡ ይኸንን ፡ ሥራ ፡ ደጋግሞ ፡ ከሠራ ፡ በኋላ ፤ በመጨረሻ ፡ ከሚተራመሱ ፡ ከብቶች ፡ ወገን ፡ ዐሥር ፡ ብቻ ፡ ቀሩ ።

በነዚህ ፡ በዐሥሩ ፡ ከብቶች ፡ መካከል ፡ የቀሩትን ፡ ሁሉ ፡ የሚበጠብጡ ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ ከብቶች ፡ ሳይሆኑ ፡ አይቀሩምና ፡ ሌሊት ፡ ጨረቃ ፡ ስትወጣ ፡ ጠብቀህ ፡ ከዳር ፡ ቆመህ ፡ ከብቶችን ፡ ተመልከታ



ቸው ፡ አለው ። እውነትም ፡ ባለጠጋው ፤ ሽማግሌው ፡ እንደ ፡ መከረው ፡ አድርጎ ፡ ቢመለከት ፡ በከብቶቹ ፡ መካከል ፡ እየሮጠ ፡ ሌሎቹን ፡ እየወጋ ፡ ጸጥታ ፡ ነሥቶ ፡ ሁሉንም ፡ የሚበጠብጣቸው ፡ አንድ ፡ ወይፈን ፡ መሆኑን ፡ አየ ። እንግዲህ ፡ ይኸን ፡ ወይፈን ፡ ወይም ፡ ሽጠው ፡ ወይም ፡ እረደው ፡ አለው ።

ወይፈኑም ፡ ከከብቶቹ ፡ መካከል ፡ ከተወገደ ፡ በኋላ ፡ ከብቶቹን ፡ ሁሉ ፡ መልሶ ፡ እንደ ፡ ቀድሞዋቸው ፡ ቢቀላቅላቸው ፡ ረግተው ፡ በሰላምና ፡ በጸጥታ ፡ ያድሩ ፡ ጀመረ ።

እነዚያን ፡ ሁሉ ፡ ከብቶች ፡ የሚበጠብጣቸው ፡ ለካ ፡ አንድ ፡ ወይፈን ፡ ብቻ ፡ ኖርዋል ። በሰዎችም ፡ መካከል ፡ ሰላምና ፡ ስምምነት ፡ ጠፍቶ ፡ ሁከትና ፡ ብጥብጥ ፡ ሲነሣ ፡ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ እያጣሩ ፡ ቢመረምሩት ፡ እንዲሁ ፡ ሆኖ ፡ እንደሚገኝ ፡ አይጠረጠርም ።

* * *

## የከፋ ፡ ሰው ፡ ስሙ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ መጥፎ ፡ ነው ።

በዘመኑ ፡ የነበሩትን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ወዳጆቹንም ፡ እንኳን ፡ ሳይቀር ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲያጣላቸውና ፡ ሲያበጣብጣቸው ፡ የሚኖር ፡ አንድ ፡ ክፍፉ ፡ ሰው ፡ ነበረ ። ክፉም ፡ ቢሆን ፤ ደግም ፡ ቢሆን ፤ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ተፈጥሮ ፡ መሞት ፡ አይቀርምና ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፤ የዚህን ፡ ሰው ፡ የክፋቱን ፡ አያሌነት ፡ አንሥተው ፡ ሰዎች ፡ ሲጫወቱ ፡ ይህ ፡ ክፉ ፡ ሰው ፡ ሞተ ።

እንግዴህ ፡ መቼም ፡ መኰነኑ ፡ አይቀርምና ፡ በሕይወቱ ፡ የሠራው ፡ ክፋት ፡ እጅግ ፡ አለመጠን ፡ የበዛ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እዚያ ፡ እገሃነም ፡ ቦታ ፡ በተገናኙ ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ የክፋት ፡ ሁሉ ፡ ምንጭ ፡ የሆነው ፡ ሰይጣን ፡ እንኳን ፡ ሳይቀር ፡ አንተም ፡ እጅግ ፡ አበዛኸው ፡ እኔ ፡ ለኰነኔ ፡ የሚያበቃህን ፡ ያህል ፡ መጠነኛ ፡ ኀጢአት ፡ ሥራ ፡ አልሁህ ፡ እንጂ ፤ ይህን ፡ ያህል ፡ ስፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌለው ፡ የተትረፈረፈ ፡ ክፋት ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ ሥራ ፡ ብዬ ፡ አልመከርሁህም ፡ ነበር ፡ እያለ ፡ እንደሚወቅሰው ፡ አይጠረጠርም ፡ ብሎ ፡ ከመካከላቸው ፡ አንዱ ፡ ቀልደኛ ፡ ሰው ፡ ተናገረ ፡ እየተባለ ፡ ሲተረት ፡ ይኖራል ። ልጆች ፡ ሆይ ፡ ክፋት ፡ ለምንም ፡ አይበጅም ፤ ክፉ ፡ ሰው ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፤ ከሞተም ፡ በኋላ ፡ ስሙ ፡ በሰዎች ፡ መካከል ፡ በመጥፎ ፡ ሲጠራ ፡ ይኖራል ።

* * *

## አንድ ፡ ፈላስፋ ።

አንድ ፡ ብልኀ ፡ ሰው ፡ ሦስት ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ። ሰው ፡
ሆኖ ፡ መሞት ፡ አይቀርምና ፡ ታሞ ፡ ሕመሙ ፡ እየጠናበት ፡ ኍልበት ፡
እያነሰው ፡ ሄደ ። የዕድሜው ፡ ፍጻሜ ፡ እንደ ፡ ተቃረበ ፡ ስለ ፡ ተሰ
ማው ፡ ሦስት ፡ ሣጥን ፡ አሠርቶ ፡ ሦስቱንም ፡ እንዳይከፈቱ ፡ አድርጎ ፡
በጥብቅ ፡ ዘግቶ ፡ በምስማር ፡ ቸንከረና ፡ ለአንድ ፡ ለሚያምነው ፡ ወዳጁ ፡
ለሆነ ፡ ሰው ፡ እንግዴህ ፡ ይኸውና ፡ እኔ ፡ በጣም ፡ ታምሜ ፡ ደክሜያለሁ ፡
የሞቴ ፡ ቀን ፡ መድረሱም ፡ ለልቤ ፡ ተሰማኝ ። እነዚህን ፡ ልጆቼን ፡ ከት
ምህርት ፡ ቤት ፡ ገብተው ፡ እየተማሩ ፡ እንዲያድጉ ፡ እንድታደርግልኝ ፡
አደራ ፡ ስጥቼሃለሁ ፤ ትምህርታቸውን ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ በነዚህ ፡ በሦ
ስቱ ፡ ሣጥኖች ፡ በያንዳንዳቸው ፡ ላይ ፡ የልጆቼን ፡ ስም ፡ ስማቸውን ፡
ለይቼ ፡ ጽፌበታለሁና ፡ ስማቸውን ፡ እያነበቡ ፡ ድርሻ ፡ ድርሻቸውን ፡
ይውሰዱ ፤ እስከዚያ ፡ ድረስ ፡ ግን ፡ በአንተ ፡ እጅ ፡ ይቀመጥላቸው ፡
ያለኝን ፡ ቅርስ ፡ ሁሉ ፡ አከፋፍዬ ፡ ሰጥቻቸዋለሁ ፤ በከፈቱት ፡ ጊዜ ፡
በሣጥኑ ፡ ውስጥ ፡ ያገኙታል ፤ የሰጠኋቸውን ፡ መቀበል ፡ እንጂ ፤ አነሰን ፡
ብለው ፡ መከራከር ፡ አይገባቸውም ፡ ብሎ ፡ አደራ ፡ ትቶለት ፡ ሞተ ።
አደራውን ፡ የተቀበለውም ፡ ሰውዬ ፡ ልጆቹን ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ አግ
ብቶ ፡ አሳድጎ ፡ ትምህርታቸውን ፡ ጨርሰው ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ አባታቸው ፡
እንደ ፡ አዘዘው ፡ ይኸውና ፡ አባታችሁ ፡ እነዚህን ፡ ሦስት ፡ ሣጥኖች ፡ ትቶ
ላችኋልና ፡ ተቀበሉኝ ፡ ብሎ ፡ አስረከባቸው ። ልጆቹ ፡ ስም ፡ ስማቸውን ፡
እያነበቡ ፡ ድርሻቸውን ፡ ወሰዱ ። ትልቅየው ፡ ልጅ ፡ ስሙ ፡ የተጻፈበ
ትን ፡ ሣጥን ፡ ቢከፍተው ፡ ሙሉውን ፡ ወርቅ ፡ አገኘ ። ሁለተኛው ፡
ልጅ ፡ ድርሻውን ፡ ሣጥን ፡ ቢከፍተው ፡ ሙሉውን ፡ ኩበት ፡ አገኘ ። ሦስ
ተኛውም ፡ ልጅ ፡ ድርሻውን ፡ ሣጥን ፡ ቢከፍተው ፡ ሙሉውን ፡ አፈር ፡
አገኘ ። እንግዴህ ፡ ሁለቱ ፡ ታናሾች ፡ ልጆች ፡ ወርቅህን ፡ አካፍለን ፡
እንጂ ፤ እኛ ፡ ኩበትና ፡ አፈር ፡ ምን ፡ ያደርግልናል ፡ ሲሉ ፡ ታላቅ ፡ ወን
ድማቸውን ፡ ጠየቁት ።

እሱ ፡ ግን ፡ አባታችን ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ በፈቃዱ ፡ አካፍሎ ፡ የተ
ወልንን ፡ ጥሰን ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ የኑዛዜውን ፡ ቃል ፡ እናፈርሳለን ፡
ሲል ፡ እንቢ ፡ አላቸው ። በዚህ ፡ ተካስሰው ፡ ሄዱና ፡ ዳኛ ፡ ዘንድ ፡



ቀረቡ ። ዳኛው ፡ ነገሩን ፡ ተመልክቶ ፡ ብይን ፡ ለመስጠት ፡ ችግር ፡ ስለ
ሆነበት ፡ ያገር ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሰብስቦ ፡ በነገሩ ፡ ሲመከሩበት ፡ ቈይተው ፡
ሁለቱ ፡ ታናሾች ፡ ልጆች ፡ ባዶ ፡ እጃቸውን ፡ ይቅሩ ፡ ለማለት ፤ ወይም ፡
ደግሞ ፡ አባታቸው ፡ በጥበብ ፡ አካፍሎ ፡ የተወላቸውን ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡
አፍርሶ ፡ ወርቁን ፡ ይካፈሉ ፡ ለማለት ፤ በሁለቱም ፡ ወገን ፡ ዐሳባቸውን ፡
መቍረጥ ፡ ስላልተመቻቸው ፤ ይህ ፡ የአባታችሁ ፡ ኑዛዜ ፡ በጣም ፡ አስ
ቸጋሪ ፡ የሆነ ፡ ምስጢር ፡ አለበት ። ወርቁን ፡ ተካፈሉ ፡ እንዳንል ፡
ለሁለታችሁ ፡ ኩበትና ፡ አፈር ፡ የሰጠበት ፡ ምክንያቱ ፡ አልተገለጠል
ንም ። ኑዛዜውም ፡ ይርጋ ፡ እንዳንል ፡ አንዱ ፡ ብቻ ፡ ተጠቅሞ ፡ ሁለቱ ፡
የሚጐዱ ፡ ሆኑ ። ስለዚህ ፡ ወደ ፡ ፈላስፋ ፡ ዘንድ ፡ ሄዳችሁ ፡ ብት
ታረቁ ፡ ይሻላል ፤ መቼም ፡ ምስጢር ፡ ከፈላስፋ ፡ አያመልጠውምና ፡
ብለው ፡ ወደ ፡ ፈላስፋ ፡ ዘንድ ፡ ላኳቸው ። ሦስቱ ፡ ወንድማማቾች ፡ የፈ
ላስፋውን ፡ ቤት ፡ እየጠየቁ ፡ ሲሄዱ ፡ ከመንገዳቸው ፡ ላይ ፡ አንዲት ፡ እር
ጉዝ ፡ ውሻ ፡ ከድካምዋ ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ የሞተች ፡ መስላ ፡ ከሜዳ ፡
ላይ ፡ ተዘርግታ ፡ በሆድዋ ፡ ውስጥ ፡ የተረገዙት ፡ ልጆችዋ ፡ በኀይል ፡
እየተላወሱ ፡ ሲዘሉ ፤ እናቲቱ ፡ ግን ፡ ሳትንቀሳቀስ ፡ ተዘርራ ፡ ተኝታ ፡ ስት
ጨነቅ ፡ አዩ ። በዚህ ፡ ነገር ፡ ተደንቀው ፡ እየተጫወቱ ፡ ሲሄዱ ፡ ከአ
ፈር ፡ በቀር ፡ ሣር ፡ ቅጠል ፡ በማይታይበት ፡ ባንድ ፡ ደረቅ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡
አንድ ፡ ጌኛ ፡ ፈረስ ፡ አለ ፡ መጠን ፡ ጠግቦ ፡ ሰምሰማ ፡ እየተራመደ ፤ እየ
ዘለለ ፤ እየፈነጨ ፤ ሽምጥ ፡ እየጋለበ ፡ የጥጋቡ ፡ ብዛት ፡ መሬት ፡ ጠብ
ቦት ፡ ሲፈነድቅ ፡ ተመለከቱ ። ይህ ፡ ሲደንቃቸው ፡ እልፍ ፡ ብለው ፡
ደግሞ ፡ ባንድ ፡ ለምለም ፡ በሆነ ፡ መስኖ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፤ መልኩ ፡ በጣም ፡
ያማረ ፡ የኮርቻ ፡ ፈረስ ፡ አለ ፡ መጠን ፡ ከስቶ ፡ ሣር ፡ እፊቱ ፡ ተርፎ ፡ ሳለ ፡
እንዳይበላ ፡ አፉ ፡ ተሸብቦ ፡ ታስሮ ፡ ቆሞ ፡ ተመለከቱ ። ይህ ፡ ፈረስ ፡
እንዲህ ፡ ተጐድቶና ፡ ከስቶ ፡ ሳለ ፡ እንዳይበላ ፡ የተሸበበበት ፡ ምክን
ያቱ ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ እየተባባሉ ፡ ነገሩ ፡ ደንቋቸው ፡ እየተጫወቱ ፡
ሲሄዱ ፡ እልፍ ፡ ብለው ፡ ደግሞ ፡ ወንዝ ፡ አገኙና ፡ ሲሻገሩ ፡ አንዲት ፡ አዞ ፡
ከአንገቷ ፡ በታች ፡ ከውሃ ፡ ውስጥ ፡ ተኝታ ፡ ራስዋን ፡ ብቻ ፡ ከወንዙ ፡
ዳር ፡ አውጥታ ፡ በጨሌው ፡ ሣር ፡ ላይ ፡ ተንጠባጥቦ ፡ የሚገኘውን ፡
ጤዛ ፡ በመላስዋ ፡ ስትልስ ፡ ተመለከቱ ። በነዚህ ፡ ባዩዋቸው ፡ ነገሮች ፡
ሁሉ ፡ ተገርመው ፡ እየተጫወቱ ፡ ሲጓዙ ፡ ከፈላስፋው ፡ ቤት ፡ ደረሱ ፡

እሱንም ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ ጠጕሩ ፡ ሙሉውን ፡ በፍጹም ፡ የሸበተ ፤ ሰውነቱ ፡ በጣም ፡ የደከመና ፡ እርጅና ፡ የጐዳው ፡ ሽማግሌ ፡ ሆኖ ፡ አገኙት ።

የመጡበትን ፡ ጕዳያቸውን ፡ ቢያጫውቱት ፡ አባታችሁ ፡ በጣም ፡ ብልኅ ፡ ኖርዋል ፡ ግን ፡ የዚህ ፡ የኑዛዜው ፡ ቃል ፡ እውነትም ፡ ምስጢሩ ፡ በጣም ፡ የረቀቀ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ የኔ ፡ ታላቅ ፡ ወንድሜ ፡ አለ ፡ በዕውቀት ፡ ከኔ ፡ ይልቅ ፡ በጣም ፡ የበለጠ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ እሱ ፡ አጣርቶ ፡ ሳይፈታላችሁ ፡ አይቀርምና ፡ ሂዳችሁ ፡ እሱን ፡ ብትጠይቁት ፡ ይሻል ፡ ይመስለኛል ፡ ብሎ ፡ ቤቱን ፤ በሩቁ ፡ አሳያቸውና ፡ አሰናበታቸው ። የዚህ ፡ ታላቅ ፡ ደግሞ ፡ እንዴት ፡ በጣም ፡ ያረጀ ፡ ይሆን ፡ እያሉ ፡ በልባቸው ፡ እያሰቡ ፡ ሂደው ፡ እዚያ ፡ ሲደርሱ ፡ በያዩት ፡ ጠጕሩ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ አንዳንድ ፡ ሸበት ፡ የጣለበት ፤ ሰውነቱም ፡ ከዚያኛው ፡ በጣም ፡ የበረታና ፡ የተሻለ ፡ ሆኖ ፡ አገኙት ። ለሱም ፡ ደግሞ ፡ እንደዚሁ ፡ የመጡበትን ፡ ጕዳይ ፡ ቢነግሩት ፡ ይኸንን ፡ ምስጢር ፡ እኔ ፡ ጠንቅቄ ፡ ልደርስበት ፡ አልችልምና ፡ የሁለታችን ፡ ታላቅ ፡ ወንድማችን ፡ አለ ፡ እሱ ፡ ዘንድ ፡ ብትሄዱ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ብሎ ፤ ቤቱን ፡ በሩቅ ፡ አሳይቶ ፡ ሸኛቸው ። ከሦስተኛው ፡ ፈላስፋ ፡ ቤት ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ እቤቱ ፡ ውሎ ፡ ኖሮ ፡ በመልካም ፡ ተቀብሎ ፡ የመጡበትን ፡ ጕዳይ ፡ ጠየቃቸው ። ሦስቱ ፡ ወንድማማቾች ፡ ያባታቸውን ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ ነግረውት ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ እሱ ፡ ሲመጡ ፡ በመንገድ ፡ የተመለከቱትን ፡ ሁሉ ፡ ከሥር ፡ ጀምረው ፡ እየተደነቁ ፡ አጫወቱት ።

እንግዴህ ፡ በማስተዋል ፡ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ ካዳመጣቸው ፡ በኋላ ፡ ፈላስፋው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገራቸው ። ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ ይኸውና ፡ እንዳያችሁን ፡ እኛ ፡ ሦስታችን ፡ ያንድ ፡ አባት ፡ ያንድ ፡ እናት ፡ ልጆች ፡ ወንድማማቾች ፡ ነን ። ያ ፡ በጣም ፡ አርጅቶ ፡ መጀመሪያ ፡ ያያችሁት ፡ የሁላችንም ፡ ታናሽ ፡ ነው ። ግን ፡ ባንዋንዋሩ ፡ ንዴትና ፡ ብስጭት ፡ ስለሚበዛበት ፡ ያው ፡ እንዳያችሁት ፡ በጣም ፡ አርጅቷል ። ሁለተኛው ፡ ያያችሁት ፡ ወንድሜ ፡ ደግሞ ፡ የኔ ፡ ተከታይ ፡ ነው ። እሱም ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ አይኖርም ። በጣምም ፡ ደግሞ ፡ ንዴት ፡ አይበዛበትም ።



ስለዚህ ፡ በጣም ፡ አላረጀም ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ታላቁ ፡ ቢሆን ፡ ከዚያኛው ፡ ይሻላል ። እኔ ። ግን ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ሰው ፡ ፍጹም ፡ ደስታ ፡ ባያገኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ንዴትና ፡ ብስጭት ፡ ስላልበዛብኝ ፡ እነሆ ፡ እንደምትመለከቱኝ ፡ የወንድሞቼ ፡ ታናሽ ፡ እንጂ ፡ ታላቃቸው ፡ አልመስልም ። ወደኔ ፡ ዘንድ ፡ ስትመጡ ፡ በመንገድ ፡ ያያችሁት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እውነትም ፡ በጣም ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነው ። ያቺ ፡ ልጆችዋ ፡ በማሕፀንዋ ፡ ውስጥ ፡ ሲጩሁ ፡ ተኝታ ፡ ስትጨነቅ ፡ ያያችኋት ፡ እናት ፡ ውሻ ፡ በነገርና ፡ በጨዋታ ፡ እኛ ፡ ይበልጥ ፡ እናውቃለን ፡ እያሉ ፡ አባታቸውንና ፡ እናታቸውን ፡ የዘመናቸውንም ፡ ሽማግሌዎችንና ፡ አሮጊቶችን ፡ አናናግርም ፡ እያሉ ፡ አፍ ፡ አፋቸውን ፡ የሚሉዋቸው ፡ በስምንተኛው ፡ ሺሕ ፡ የሚፈጠሩ ፡ ሕፃናቶች ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።

ያ ፡ ሣር ፡ ቅጠል ፡ በማይታይበት ፡ በደረቅ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ጠግቦና ፡ ወፍሮ ፡ የሚፈነጭ ፡ የጭነት ፡ ጌኛ ፡ እከሌ ፡ ቀብሎ ፡ ስሙ ፡ ከማይታወቅ ፡ አባት ፡ የተወለዱ ፡ ከድኽነት ፡ ቦታ ፡ ተነሥተው ፡ ዓለምን ፡ የሚበጠብጡ ፡ ሕዝብን ፡ የሚያፋጁ ፡ መሬት ፡ ጠበቦችን ፡ የሚሉ ፤ በስምንተኛው ፡ ሺሕ ፡ ተፈጥረው ፡ የሚነሡ ፡ ሰዎችን ፡ የሚያሳይ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ። ያ ፡ በለምለም ፡ መስኖ ፡ ውስጥ ፡ ታስሮና ፡ አፉን ፡ ተሸብቦ ፡ ያያችሁት ፡ መልኩ ፡ የሚያምር ፡ ከስቶ ፡ የቆመ ፡ የኮርቻ ፡ ፈረስ ፡ ገንዘብና ፡ ሀብት ፡ ሳይጠፉ ፡ ተርፎ ፡ ሳለ ፡ እንዳያገኙ ፡ ተከልክለው ፡ ተረስተውና ፡ ተገዶ ፡ ተው ፡ የሚኖሩ ፡ በስምንተኛው ፡ ሺሕ ፡ የሚወለዱ ፡ የጨዋች ፡ ልጆች ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።

ያቺ ፡ ከአንገትዋ ፡ በታች ፡ በወንዝ ፡ ውሃ ፡ ውስጥ ፡ ተኝታ ፡ ራስዋን ፡ ወደ ፡ ውጪ ፡ አውጥታ ፡ ጤዛ ፡ ስትል ፡ ያያችኋት ፡ አዞ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብና ፡ ብዙ ፡ ሀብት ፡ ሰብስበው ፡ አከማችተው ፡ ተርፎዋቸው ፡ ሳለ ፡ ሳይቸግራቸው ፡ የተቸገሩ ፡ መስለው ፡ በጊዜያቸው ፡ የተፈጠሩትን ፡ ድኾች ፡ ያለ ፡ ርኅራኄ ፡ እየቀሙና ፡ እየነጠቁ ፡ የሚያስርቡዋቸውና የሚያራቁቱዋቸው ፡ በስምንተኛው ፡ ሺሕ ፡ የሚፈጠሩ ፡ ጠግብን ፤ ቢቃን ፡ ማለትን ፡ የማያውቁ ፡ ሀብታሞች ፡ ምሳሌ ፡ ነው ። እንግዴህ ፡ ወደ ፡ መጣችሁበት ፡ ዋና ፡ ጕዳያችሁ ፡ እንመለስና ፡ አባታችሁ ፡ ይኸንን ፡ ኑዛዜ ፡ ትቶላችሁ ፡ መሞቱ ፡ አንዳችሁን ፡ ካንዳችሁ ፡ አብልጦ ፡ በመውደድ ፡

ለማዳላት ፡ አንዱን ፡ ጠቅሞ ፡ አንዱን ፡ ሊጐዳ ፡ አይደለም ። ለአንተ ፡ ለታላቁ ፡ ወርቅ ፡ ትቶልህ ፡ መሞቱ ፡ እንጀራህ ፡ በንግድ ፡ መሆኑን ፡ ሲነግርህና ፡ ካንዱ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ አገር ፡ ስትመላለስ ፡ ለመቋቋሚያ ፡ እንዳይቸግርህ ፡ ገንዘብ ፡ ሲሰጥህ ፡ ነው ።

ለአንተ ፡ ለሁተኛው ፡ ከብት ፡ ማውረሱ ፡ ኑሮህ ፡ ከብት ፡ በማርባት ፡ መሆኑን ፡ ሲያስታውቅህ ፡ ነው ። ለአንተ ፡ ለሦስተኛው ፡ ደግሞ ፡ አፈር ፡ መስጠቱ ፡ ትዳርህ ፡ በግብርና ፡ ሥራ ፡ መሆኑን ፡ ሲያስረዳህ ፡ ነው ። እንግዴህ ፡ እናንተ ፡ ማድረግ ፡ የሚገባችሁ ፡ ታላቅ ፡ ወንድማችሁን ፡ ሳትመቀኙ ፡ እሱም ፡ እየነገደ ፤ አንተም ፡ ከብት ፡ እያረባህ ፤ አንተም ፡ ደግሞ ፡ እያረስህ ፤ ሦስታችሁም ፡ የአባታችሁን ፡ ቃል ፡ ተከትላችሁ ፡ መኖር ፡ ነው ፤ ይኸን ፡ ብታደርጉ ፡ በጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሀብታችሁ ፡ እግኝታችሁ ፡ ሦስታችሁም ፡ ደስ ፡ ብሎዋችሁ ፡ ትኖራችሁ ፡ ብሎ ፡ ምስጢሩን ፡ ፈታላቸው ። ሦስቱም ፡ ልጆች ፡ ፈላስፋው ፡ ይኸንን ፡ ሁሉ ፡ ሲናገር ፡ በመደነቅ ፡ ብዛት ፡ አፋቸውን ፡ ከፍተው ፡ ያዳምጡት ፡ ነበር ። ንግግሩን ፡ በጨረሰ ፡ ጊዜ ፡ አመስግነው ፡ ቃሉን ፡ ተቀብለው ፡ በዚሁ ፡ ተስማምተው ፡ ኖሩ ። እሱ ፡ እንደ ፡ ነገራቸው ፡ ሆኖ ፡ በጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ሦስቱም ፡ ሀብታሞች ፡ ሆኑ ።

* * *

## ፋኖስና ፡ ብርጭቆው ።

አንድ ፡ የፋኖስ ፡ መብራት ፡ በግብሩ ፡ የኩራ ፤
እንዲስ ፡ ሲል ፡ ተጣላ ፡ ከብርጭቆው ፡ ጋራ ።
እኔ ፡ ነኝ ፡ መብራቱ ፡ ብርሃን ፡ የምሰጥ ፤
ጨለማን ፡ አጥፍቼ ፡ የምገላልጥ ።
አንተ ፡ ግን ፡ እሬቴ ፡ እንዲህ ፡ ተደንቅረህ ፤
ዙሪያዬን ፡ ከበኸኝ ፡ እንዲያው ፡ ተገትረህ ።
አልገባኝም ፡ ከቶ ፡ የምትሠራው ፡ ሥራ ፤
ብርሃኔ ፡ ሩቅ ፡ ደርሶ ፡ ደምቆ ፡ እንዳያበራ ።
ተሰራጭቶ ፡ በጣም ፡ እንዳይዘረጋ ፤
አንተን ፡ ፈጠረብኝ ፡ መንገድ ፡ የምትዘጋ ።
ፅንቅፋት ፡ እየሆንህ ፡ ሥራዬን ፡ እታጥፋ ፤
ገለል ፡ በል ፡ ከፊቴ ፡ ብርሃኔ ፡ ይስፋፋ ።



አገልግሎቴማ ፡ ከሆነብኝ ፡ ጥፋት ፤
እውነትማ ፡ ላንተ ፡ ከሆንኩህ ፡ ዕንቅፋት ።
ልሂድልህ ፡ ብሎ ፡ ሲለቅለት ፡ ቦታ ፤
ከጐን ፡ የነፈሰ ፡ የነፋስ ፡ ሽውታ ፤
መጣና ፡ መብራቱን ፡ አጠፋው ፡ ባንድ ፡ አፍታ ።
አጭር ፡ እየሆነ ፡ ተመልካችነቱ ፤
መለየት ፡ አቅቶት ፡ ጥቅሙን ፡ ከጉዳቱ ።
እወቁኝ ፡ እወቁኝ ፡ እያለ ፡ ሲነሣ ፤
ሰውም ፡ እንደዚሁ ፡ ያመጣል ፡ አበሳ ።

* * *

## ቦ ል ቴ ር ።

ቦልቴር ፡ የሚባለው ፡ የፈረንሳዊ ፡ ፈላስፋ ፡ በጣም ፡ ሥራ ፡ ያበዛ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ ወዳጁ ፡ እባክህ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እንኳን ፡ ዕረፍት ፡ አድርግ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ሠርተህ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ትችላለህ ፡ ቢለው ፤ ወዳጄ ፡ ሆይ ፤ ሰው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ የተፈጠረው ፡ ለመሥራትና ፡ ለመድከም ፡ ብቻ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እኛ ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ የሚቻለንስ ፡ በሆነ ፡ ኖሮ ፡ አንዲት ፡ ደቂቃ ፡ እንኳን ፡ ሳናቋርጥ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ብንሠራ ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ ነበረ ፡ ዕረፍቱንማ ፡ እስኪታከተን ፡ ድረስ ፡ እንጠግበዋለን ፡ ሞትን ፡ የሚያህል ፡ የዘለዓለም ፡ መኝታ ፡ ተሰናድቶልን ፡ ይጠብቀናልና ፡ ብሎ ፡ ቮልቴር ፡ መለሰለት ።

* * *

## አዝማሪና ፡ የውሃ ፡ ሙላት ።

አንድ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተነሥቶ ፡ ሲሄድ ፤
የወንዝ ፡ ውሃ ፡ ሞልቶ ፡ ደፍርሶ ፡ ሲወርድ ።
እዚያው ፡ እወንዙ ፡ ዳር ፡ እያለ ፡ ጐርደድ ።
መሰንቆ ፡ እየመታ ፡ ድምጡን ፡ አሳምሮ ፤
አንድ ፡ አዝማሪ ፡ አገኘ ፡ ሲዘፍን ፡ አምርሮ ።
ምነው ፡ አቶ ፡ አዝማሪ ፡ ምን ፡ ትሠራለህ ?
ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ ምን ፡ ሁን ፡ ትላለህ ።
አላሻግር ፡ ብሎኝ ፡ የውሃ ፡ ሙላት ፤፡

እያሞጋገስኩት ፡ በግጥም ፡ ብዛት ፤
አባብለዋለሁ ፡ እስኪ ፡ ምናልባት ።
ልቡን ፡ አራርቶልኝ ፡ ቢያሻግረኝ ፡ ብዬ ፤
አሁን ፡ ገና ፡ ሞኝ ፡ ሆንህ ፡ ምነዋ ፡ ሰውዬ ።
ነገሩስ ፡ ባልከፋ ፡ ውሃውን ፡ ማሞገስ ፤
ግን ፡ እንደዚህ ፡ ፈጥኖ ፡ በችኰላ ፡ ሲፈስ ።



አስተውለህ ፡ እየው ፡ አንተም ፡ ብትሆን ፡ ደግሞ ፤
እንዴት ፡ መስማት ፡ ይቻል ፡ የሰው ፡ ነገር ፡ ቆሞ ።
እስኪ ፡ ተመልከተው ፡ ይህ ፡ አወራረድ ፤
ያልሰማው ፡ ሲመጣ ፡ የሰማው ፡ ሲሄድ ፤
ድምጡን ፡ እያውካካ ፡ መገሥገሡን ፡ ትቶ ፤
ማን ፡ ይሰማኝ ፡ ብለህ ፡ ትደክማለህ ፡ ከቶ ።
ተግሣጽም ፡ ለጠባይ ፡ ካልሆነው ፡ አራሚ ፤
መናገር ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ ካልተገኘ ፡ ሰሚ ።



## እ ር ር ።

ሀምሆና ፡ ቅዳሜ ፡ በክረምት ፡ ወራት ፤
የጣሊያን ፡ ተወላጅ ፡ ቼሊ ፡ የሚሉት ፤
ልዩ ፡ ልዩ ፡ ወሬ ፡ ስንጫወት ፤
በሰው ፡ ዘር ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፤
ብዙ ፡ ነው ፡ እያለ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ አመጣ ፤
እኛ ፡ ፋሺስቶቹ ፡ ሕግ ፡ ስናወጣ ።
በጣሊያኖችና ፡ ባበሾች ፡ መካከል ፤
አብሮ ፡ መብላትና ፡ ጋብቻ ፡ መከልከል ።
ለብቻ ፡ መወሰን ፡ የጥቍሮችን ፡ መንደር ፤
ይኸን ፡ የመሰለ ፡ ሌላም ፡ ብዙ ፡ ነገር ፤
በክፍል ፡ በክፍሉ ፡ ዐይነቱን ፡ መዘርዘር ።
ጣሊያን ፡ ባበሻ ፡ ላይ ፡ የበላይነቱን ፤
የሚያሳይበትን ፡ ሰጥተናል ፡ ሥርዐቱን ።
እናንተ ፡ አበሾች ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ መደረጉ ፤
ክብራችን ፡ መውረዱ ፡ ከጥንት ፡ ማዕርጉ ።
ዘራችን ፡ ስማችን ፡ እንደዚህ ፡ መናቁ ፤
እያላችሁ ፡ ምነው ፡ ባትሞላቀቁ ።
የክብትነታችሁ ፡ ትልቅነት ፡ ብዛት ፤
የዋጋችሁን ፡ ልክ ፡ መርምሮ ፡ መረዳት ፤
አለመቻላችሁ ፡ በጣም ፡ ያሳዝናል ፤
እኛ ፡ ግን ፡ ሁሉንም ፡ አይተን ፡ መዝነናል ።
የምትመኩበት ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ ክብራችሁ ?
ባቡር ፡ አቶሞቢል ፡ ስልክስ ፡ ፈጠራችሁ ?
ከመንፈስስ ፡ ጥበብ ፡ ምን ፡ ፈለሰፋችሁ ፤
እስኪ ፡ የሚጠቅም ፡ ምን ፡ ነገር ፡ ሠራችሁ ።
ቀድሞ ፡ አባቶቻችን ፡ እንደሚያኑት ፤
ትንሽ ፡ ጎጆ ፡ መሥራት ፡ መቀመጥ ፡ በከብት ።
የጥበብ ፡ ምልክት ፡ ባገራችሁ ፡ የለ ፤
ለምለሙ ፡ አገራችሁ ፡ ዱር ፡ እየመሰለ ።

ፋብሪካና ፡ ሐውልት ፡ የሥልጣኔ ፡ ውበት ፤
ቢሄዱ ፡ ቢሄዱ ፡ የማይታይበት ።
ጥሩ ፡ አገር ፡ ይዛችሁ ፡ በከንቱ ፡ ስትኰሩ ፤
ወይ ፡ አትሠሩበት ፡ ወይ ፡ ሰው ፡ አታሠሩ ።
የምትኰሩበት ፡ እንግዴህ ፡ እናንተ ፤
እኔ ፡ እዚህ ፡ ተወለድሁ ፡ አባቴ ፡ እዚህ ፡ ሞተ ።
ካያት ፡ ከቅድም ፡ አያት ፡ የመጣው ፡ ርስቴ ፤
የሠራሁት ፡ ጎጆ ፡ ያቆምሁት ፡ ንብረቴ ።
ለምን ፡ ተነከቶብኝ ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ ነው ፤
ነገር ፡ ግን ፡ እስተውለህ ፡ ብታመዛዝነው ።
ኀይለኛ ፡ እየሄደ ፡ ያስገብራል ፡ የትም ፤
መሬት ፡ የሁሉ ፡ ነች ፡ ባለቤት ፡ የላትም ።
ትዳር ፡ ለማቋቋም ፡ ቤትን ፡ ለመሥራት ፤
ንብረት ፡ ለመመሥረት ፡ እህል ፡ ለመዝራት ።
አውሬን ፡ እያጠፉ ፡ ደን ፡ እማይመነጥር ፤
ከሰው ፡ ልጅ ፡ መካከል ፡ ይገኛል ፡ ወይ ፡ ፍጡር ።
ስንመለከተው ፡ የኑሮዋችሁ ፡ ቅጥ ፤
ከእንስሶች ፡ እንዋንዋር ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ሲበልጥ ።
ጠቢብ ፡ ሰው ፡ በሥራው ፡ መሬትን ፡ ሲቀድስ ፤
ሁሉን ፡ በማሳመር ፡ ሲያጠዳና ፡ ሲያድስ ።
ደንቆሮ ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፡ እንደናንተ ፡ ያለ ፤
በትልቅ ፡ ስንፍና ፡ የተንቀዋለለ ።
እንደ ፡ እንስሳ ፡ ሁሉ ፡ ምድርን ፡ አረከሳት ፤
ሕዝብ ፡ እየተራባ ፡ ዓለም ፡ ጕን ፡ ሲያንሳት ።
የመሬትዋም ፡ ስፋት ፡ በጣም ፡ ሲጣበብ ፤
እንደኛ ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ የሞላው ፡ ጥበብ ።
እንደናንተ ፡ ያለ ፡ የደከመውን ፤
ዕውቀት ፡ ጦር ፡ መሣሪያም ፡ የጐደለውን ።
እንደ ፡ እንስሳ ፡ ሁሉ ፡ ፈጅቶ ፡ እያባረረ ፤
ሰውንም ፡ ቤቱንም ፡ እየመነጠረ ፤



ላየው ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ለሠሪ ፡ እሚያኰራ ፤
ለዓለም ፡ የሚጠቅም ፡ ብዙ ፡ ብዙ ፡ ሥራ ።
እያከናወነ ፡ ይሠራበታል ፤
የናንተ ፡ሙያ ፡ ግን ፡ ኧረ ፡ ወዴት ፡ አል ።
ሰዎች ፡ ነን ፡ ብላችሁ ፡ ደግሞ ፡ የምትኰሩ ፤
በድንቍርናችሁ ፡ ጥቂት ፡ የማታፍሩ ።
ክብር ፡ አጣን ፡ በማለት ፡ የናንተ ፡ መከራከር ፤
ጅልነት ፡ ያሰኛል ፡ አለመመራመር ።
እናንተን ፡ በመናቅ ፡ የዙራቴ ፡ መንፈስ ፤
ምን ፡ የሚያህል ፡ ሆኖ ፡ ወዴት ፡ እንደሚደርስ ።
እውነት ፡ ለመረዳት ፡ ለማወቅ ፡ ብትፈልግ ፤
ይኸንን ፡ ምሳሌ ፡ ስማና ፡ ልብ ፡ አድርግ ።
የሚያገለግለኝ ፡ አብሮኝ ፡ የሚኖር ፤
አለኝ ፡ የቀጠርሁት ፡ አንድ ፡ አበሻ ፡ አሽከር ፤
እሱም ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ለመነጋገር ፤
የተወራጅነት ፡ ስሰጠው ፡ ጠባይ ፤
መሬት ፡ መሬት ፡ እንጂ ፤ ፊቴን ፡ እንዳያይ ፤
አጥብቄ ፡ ከልክዬው ፡ ተበቈጥቍጠ ፡ ያድራል ፤
ይኸንንም ፡ ትእዛዝ ፡ ፈጽሞ ፡ ይኖራል ።
ደግሞም ፡ ላበሻ ፡ ሰው ፡ ሰላምታ ፡ ስሰጥ ፤
እጄን ፡ ዘርግቼለት ፡ እጁን ፡ መጨበጥ ፤
ትልቅ ፡ ውርደት ፡ ሆኖ ፡ ስለሚታየኝ ፤
መቼም ፡ አላደርገው ፡ ለዚህ ፡ ዙሩ ፡ ነኝ ።
ይህም ፡ እንዳይመስልህ ፡ ያልተገባ ፡ ዙራት ፤
ጣሊያኖች ፡ ደግችን ፡ የተቀደሰች ፡ ናት ።
የሚኬል ፡ አንጄሎ ፡ የዳንት ፡ የማርኮኒ ፤
የነጋሪባልዲ ፡ የነሙሶሊኒ ።
የነጠረ ፡ ደም ፡ ነው ፡ ከወርቅም ፡ የጠራ ፤
ሠርተናል ፡ ባለም ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ትልቅ ፡ ሥራ ።
የብዙ ፡ ዐይነት ፡ ጥበብ ፡ ጌጥ ፡ የሞላባቸው ፤
ከተሞቻችንም ፡ ምስክሮች ፡ ናቸው ።

የናንተ ሕዝባችን የሚሄደው ስብሶ፤
የቤት ዕቃው ሳይቀር ሁሉም የተውሶ::
እሥልጣኔው ቦታ ከቶ ስመድረስ፤
ምልክት የላችሁ የመንቀሳቀስ::
እንደ ሌሎቹማ ብትሠለጥኑ፤
ዕውቀት አግኝታችሁ ኃይለኞች ብትሆኑ::
ዋጋችሁ፤ ሥራችሁ በውነት የሚከበር፤
ያገራችሁ ጠረፍ በሩ አማይደፈር፤
ቢሆንማ ኖሮ ምንም ብንመኝ፤
እናንተን ለማጥቃት ዘዴም አናገኝ::
ግን ደካማ ሲገኝ የሌለው ጉልበት፤
የሚለቀው የለም የሚተኛለት፤
ደግሞስ ለምሳሌ እስኪ እንዲያው ምናልባት፤
ያጋጣሚ ነገር ተገኝቶ ምክንያት::
ነጻ ብትወጡ ምንም ሳትሠሩ፤
እንደ ልማዳችሁ ወድቃችሁ ስትኖሩ::
ብዙ ዘመን [illegible] ጊዜው ቢዘገይ፤
ደግሞ ኖረን ኖረን ምንም ብንቈይ::
መቼም አይሞትና እኛም ምኞታችን፤
ምንም ቢሆን አይቀር ደግሞ መምጣታችን፤
ዐድዋ ድል ብንሆን አርባ ዓመት ቈይተን፤
ይኸውና ዛሬ ተመልሰን መጥተን፤
አሸንፈናችሁ እንዲህ እያጠቃን፤
ደምን ለመበቀል ለመግዛት በቃን::
እያመነመነ ክፉ ድንቍርና፤
ስለ ገደላችሁ የማይተው ስንፍና::
ብልኀት አይገኝም ምንም ቢመረመር፤
እናንተን ጨርሶ ከማጥፋት በስተቀር::
እንደዚህ ሲናገር ቈይቶ እኩል ሰዓት፤
በኋላ ጨረሰ የስድቡን መዓት::



ሰምቼ ፡ እንዳልሰማ ፡ በሆዴ ፡ እያረርሁ ፤
የንዴቴ ፡ ብዛት ፡ መልስም ፡ አልመለስሁ ፤
ሥቄ ፡ ካጠገቡ ፡ ተነሥቼ ፡ ሄድሁ ።
እያንገበገበ ፡ አንጀቱን ፡ ሲያጨሰው ፤
እሮሮ ፡ አታሰማኝ ፡ ይላል ፡ ያገሬ ፡ ሰው ።
መብት ፡ ባጣ ፡ ጊዜ ፡ እኩል ፡ መመለስ ፤
ይኸን ፡ መሳይ ፡ ስድብ ፡ ከጠላት ፡ መላስ ፤
በጆሮው ፡ ሲሰማ ፡ ማነው ፡ የማይጨስ ። ?
እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ክፉ ፡ ንግግር ፤
ከሳት ፡ የሚያቃጥል ፡ ከሬት ፡ የሚመር ።
አዳምጦ ፡ ጨርሶ ፡ ከቆመ ፡ በኋላ ፤
ምን ፡ በድን ፡ ይገኛል ፡ ደሙ ፡ የማይፈላ ?
ደግሞስ ፡ መፈጠሩን ፡ ማነው ፡ የማይጠላ ። ?
የተቃጠለ ፡ ሰው ፡ ያረረ ፡ በሆዱ ፤
ምን ፡ አንጀቱ ፡ ቢነድ ፡ አይቀርም ፡ መብረዱ ።
ንዴቴ ፡ እያለፈ ፡ ደሜ ፡ ሲቀዘቅዝ ፤
ነገሩን ፡ በልቤ ፡ ዐሰቤ ፡ ስተክዝ ።
የተናገረኝን ፡ ይህ ፡ ክፉ ፡ እብሪተኛ ፤
ያመዛዝን ፡ ጀመር ፡ ዐሳቤ ፡ ሳይተኛ ።
ለፖለቲክ ፡ ሥራ ፡ መንግሥት ፡ የላካቸው ፤
የነሱ ፡ ሰባኪዎች ፡ ሹማምንቶቻቸው ።
እኛ ፡ ባበሻ ፡ አገር ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፤
ሕዝቡን ፡ ለማሠልጠን ፡ አገር ፡ ለማልማት ፤
ልጆች ፡ ለማስተማር ፤ ዕውቀት ፡ ለመስጠት ።
ለመልካም ፡ ዐሳብ ፡ ነው ፡ የመጣን ፡ እያሉ ፤
በጣም ፡ አስመስለው ፡ ይቀባጥራሉ ።
ሐቀኛው ፡ ቋሊ ፡ ግን ፡ እውነቱን ፡ አፍርጦ ፤
እኛ ፡ የመጣነው ፡ አበሻን ፡ ቀጥቅጦ ።
በዚያም ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ ሰበብን ፡ ፈልጎ ፤
እንደ ፡ እንስሳ ፡ ሁሉ ፡ እናንተን ፡ ጠራርጎ ።

ባዶ፡ መሬት፡ ብቻ፡ እንዲቀር፡ ነው፡ ብሎ፤
ይኸንኑም፡ ደግሞ፡ መፈጸም፡ በቶሎ።
የሚጣጣሩበት፡ መሆኑን፡ አስረዳ፤
የናዚስትን፡ ዐሳብ፡ ገልብጦ፡ ሲቀዳ።
ፋሺስት፡ አስቀድሞ፡ የዘርን፡ ልዩነት፤
ተቀብሎ፡ አምጥቶ፡ እንዲሞክርበት።
የኢትዮጵያን፡ ሕዝቦች፡ ከምድር፡ ለማስወገድ፤
ከእንስሳ፡ አሳንሶን፡ በሁሉም፡ ረገድ።
ስናመዛዝነው፡ እኛስ፡ ይህን፡ ነገር፤
ሰው፡ በሳት፡ ማቃጠል፡ ሰው፡ ባካፋ፡ መውገር።
ጊዜ፡ ቢያጋልጠው፡ ይህ፡ የተረታ፡ ሰው፤
ለመከላከያ፡ ዛሬ፡ ጉልበት፡ ቢያንሰው።
ለሁሉም፡ በተራ፡ ቀን፡ ይጐድልበታል፤
አሸናፊም፡ ደግሞ፡ አንድ፡ ቀን፡ ይረታል።
ከንቱ፡ ነው፡ ለሰው፡ ልጅ፡ መመካት፡ በኀይሉ፤
ሰው፡ ይፈርድብናል፡ ይቅርብን፡ ሳይሉ።
የሰው፡ ደም፡ ሲያፈሱ፡ ጥቂት፡ አለማዘን፤
በሕሊና፡ በኩል፡ አለማመዛዘን።
ትዕቢት፡ በልቡና፡ እጅግ፡ አሳድጎ፤
ሰውን፡ አለማየት፡ እንደ፡ ራስ፡ አድርጎ፤
በሆነ፡ ባልሆነው፡ ምክንያት፡ ፈልጎ።
ደም፡ እንደ፡ ተጠሙ፡ እንደ፡ ዱር፡ አራዊት፤
መፍጀት፡ በመደዳ፡ ብዙውን፡ ሠራዊት።
ያለ፡ አንድ፡ ርኅራኄ፡ እንደ፡ ጭራቅ፡ ሆድ፤
እረደው፡ እረደው፡ ማለትን፡ መውደድ።
አውሬስ፡ የሚያሰኘው፡ ይኸ፡ ነው፡ በእውነቱ፤
ያለ፡ ስም፡ መሰየም፡ ምን፡ ያደርጋል፡ ከንቱ።
ሳጥናኤልም፡ ልቡ፡ እብሪት፡ ባሳደረ፤
የዘላለም፡ ውርደት፡ ተቀብሎ፡ ቀረ።
የሰው፡ ልጅ፡ በሥራው፡ ቢመካ፡ በከንቱ፤
እንደ፡ ሰናዖር፡ ግንብ፡ ይፈርሳል፡ ብልኀቱ።



ትዕቢት ፡ ትመጣለች ፡ ውርደት ፡ አስከትላ ፤
የተመካ ፡ ሁሉ ፡ ይጠፋል ፡ በኋላ ።
ትዕቢት ፡ ያበዛችው ፡ ጣሊያን ፡ እንዲህ ፡ ኵርታ ፤
ለጥፋት ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ መቼ ፡ ለደስታ ።
በጥበብም ፡ በኀይል ፡ በሀብትም ፡ በሁሉ ፤
ከስዋ ፡ የበለጡ ፡ ብዙ ፡ ሕዝቦች ፡ አሉ ።
ግን ፡ በሥራም ፡ ሆነ ፡ ባነጋገራቸው ፤
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ጥጋብ ፡ የለም ፡ በልባቸው ።
ፍየል ፡ ከመድረስዋ ፡ ቅጠል ፡ መበጠስዋ ፤
እንደሚባል ፡ ሁሉ ፡ ጣሊያን ፡ በመንፈስዋ ።
ተዋርዳ ፡ እንደ ፡ ኖረች ፡ በዚሁ ፡ ትዕቢት ፤
ዐስባ ፡ እንደ ፡ ማራቅ ፡ ልብዋን ፡ ከክፋት ፤
እስዋው ፡ በገዛ ፡ እጅዋ ፡ ስትሻ ፡ ውርደት ፤
የትምክሕትዋ ፡ ብዛት ፡ ጠበበው ፡ መሬት ፤
ብዬ ፡ ይህንን ፡ ቃል ፡ ልመልስለት ።
ቈርጬ ፡ ነበረ ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ ዐስቤ ፤
አመዛዝንሁና ፡ ነገሩን ፡ በልቤ ።
ስላልፈቀደልኝ ፡ የጊዜው ፡ ሁኔታ ፤
ተሰድቤ ፡ መቅረት ፡ ሆነብኝ ፡ ግዴታ ።
አሁን ፡ እያሰብሁት ፡ ጠላት ፡ አጥቂነቱ ፤
ከመግደል ፡ ከመውረስ ፡ ከማንገላታቱ ።
ከሁሉም ፡ ከሁሉም ፡ ስድቡና ፡ ወቀሳ ፤
መቼም ፡ መቼ ፡ ቢሆን ፡ ከልብ ፡ አይረሳ ።
ያኳኋኑን ፡ ነገር ፡ አሁን ፡ እያሰብኩ ፤
የንቀቱ ፡ ብዛት ፡ ይታየኛል ፡ መልኩ ።
አወይ ፡ ማንገብገቡ ፡ እንጀት ፡ ሲያሳርር ፤
ሰው ፡ በሰው ፡ መካከል ፡ ተንቆ ፡ ሲኖር ።
እኔስ ፡ በመጻሕፍት ፡ ያየሁ ፡ የሰማሁት ፤
ጥበብ ፡ የሰውን ፡ ልብ ፡ ያደርገዋል ፡ ትሑት ።
ዕውቀት ፡ ርኅራኄን ፡ ያሰጠዋል ፡ ለልብ ፤
ሲባል ፡ ነበር ፡ እንጂ ፤ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ስድብ ፤

እንዴት ፡ ይናገራል ፡ የሠለጠነ ፡ ሕዝብ ።
እግዜር ፡ የሰውን ፡ ዘር ፡ እንፍጠር ፡ ሲል ፡ ሠራ ፤
ፋሺስቱ ፡ ብልኀ ፡ ግን ፡ አድርጎ ፡ ምርመራ ።
ያሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ አዲሱ ፡ ፈላስፋ ፤
እለና ፡ ተነሣ ፡ የሰው ፡ ዘር ፡ እናጥፋ ።
እኛስ ፡ እናውቃለን ፡ ማ ፡ እንደሚበረታ ፤
ላሸንፍ ፡ እያለ ፡ በጥበቤ ፡ ልርታ ።
ፋሺስት ፡ መግቱ ፡ ቢበጅም ፡ ባይበጅ ፤
ከሰው ፡ ጋራ ፡ አይደለም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እንጅ ።
ለድል ፡ መንገቱ ፡ ያሰኛዋል ፡ ሞኝ ፤
ከእግዚአብሔር ፡ ተጣልቶ ፡ ምን ፡ መቅና ፡ ሊያገኝ ።
የኢትዮጵያ ፡ ልጆች ፡ እናንት ፡ ወጣቶቹ ፤
ያሁኑ ፡ ጊዜና ፡ የወደፊቶቹ ።
ችላ ፡ ሳትሉና ፡ ደግሞም ፡ ሳትቦዝኑ ፤
ይኸን ፡ ማስታወሻ ፡ በቃላችሁ ፡ እጥኑ ።
የጣሊያኖች ፡ ዐሳብ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ነበረ ፤
ሳይበዛ ፡ ባጭሩ ፡ እየዘረዘረ ።
ሰው ፡ ተገገር ፡ ሲሆን ፡ ያለበትን ፡ ዕዳ ፤
የሚያመለክት ፡ ነው ፡ ገልጦ ፡ የሚያስረዳ ።

* * *

ሰነፍ ፡ ይከሥራል ፡ ሠራተኛ ፡ ይከብራል ።

የተሰጠችውን ፡ የሕይወቱን ፡ ጊዜ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ሲያሳልፍ ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ ሥራ ፡ እየሠራ ፡ ቢኖር ፡ የሚሻል ፡ መሆኑን ፡ ለመምረጥ ፡ አቅቶት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይህንኑ ፡ ዐሳብ ፡ በልቡ ፡ ሲያወጣና ፡ ሲያወርድ ፡ የሚውል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ይህንኑ ፡ ሲያስብ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በልቡ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ካባቴ ፡ የወረስሁት ፡ ጥሩ ፡ ርስት ፡ አለኝ ። ይህንን ፡ ርስቴን ፡ እህል ፡ ብዘራበትና ፡ አታክልት ፡ በያይነቱ ፡ ብተክልበት ፡ መጀመሪያ ፡ መሬቴ ፡ ይለማል ፤ ሁለተኛም ፡ ገንዘብ ፡ አገኝበታለሁ ፤ ስለዚህ ፡ ጥቅሚ ፡ በሁለት ፡ ወገን ፡ ይሆናል ። ይህንንም ፡ ለማሠራት ፡ ብዙ ፡ ያባቴ ፡ አገልጋዮች ፡ ስላሉኝ ፡ ሌላም ፡ ሠራተኛ ፡ አያሻኝ ፡ ብሎ ፡ ዐሳቡን ፡ በዚህ ፡ አቆመ ።



ለዚህ ፡ የሚሆነውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሥራ ፡ መሣሪያ ፡ አሰናድቶ ፡ ያባቱን ፡ አገልጋዮች ፡ ጠርቶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ ባባቴ ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ በብዙው ፡ እህል ፡ ለመዝራትና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የምግብ ፡ አታክልት ፡ ለመትከል ፡ ዐስቤያለሁና ፡ ከዛሬ ፡ ጀምራችሁ ፡ ጧት ፡ ጧት ፡ ወደ ፡ ርስቴ ፡ እየሄዳችሁ ፡ እንድትሠሩ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ። ከዚያም ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ በጧት ፡ ተነሥቶ ፡ አገልጋዮቹን ፡ ሂዱ ፡ ሥሩ ፡ እያለ ፡ ይልካቸውና ፡ እሱ ፡ የትም ፡ እየዞረ ፡ ሲጠጣ ፡ ሲጫወት ፡ ሲፈነጥዝ ፡ ይውላል ። ሦስት ፡ ዓመት ፡ የሚሆን ፡ እንደዚህ ፡ ከኖረ ፡ በኋላ ፤ ከእርሻውና ፡ ካታክልቱ ፡ ያገኘው ፡ ገንዘብ ፡ እንኳንስ ፡ ሀብት ፡ ሊሆነውና ፡ ያገልጋዮቹን ፡ ልብስና ፡ ምግብ ፡ ሳይችልለት ፡ ቀረ ።

ዐሳቡ ፡ በጣም ፡ መልካም ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ሳያተርፈው ፡ በመቅረቱ ፡ አዝኖ ፡ ርስቱን ፡ ከሁለት ፡ ከፈለና ፡ አንዱን ፡ እኩሌታ ፡ ሸጠው ። አንደኛውን ፡ እኩሌታ ፡ ግን ፡ አከራየው ። የተከራየውም ፡ ሰው ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ የእርሻና ፡ የአታክልት ፡ ደግሞ ፡ ከብት ፡ የማርባት ፡ ሥራ ፡ እየሠራ ፡ በየዓመቱ ፡ የክራዩን ፡ ዋጋ ፡ ትክክል ፡ ሲከፍለው ፡ ከቈየ ፡ በኋላ ፤ ወደ ፡ ባለቤቱ ፡ ዘንድ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ። ባለቤት ፡ ሆይ ፡ ያንተን ፡ መሬት ፡ በመከራዬቴ ፡ መልካም ፡ ዕድል ፡ ሆነልኝ ። ገንዘብ ፡ አገኘሁበት ። አሁንም ፡ የሦስተኛውን ፡ ዓመት ፡ ክራይ ፡ እነሆ ፡ ተቀበለኝ ። ደግሞ ፡ የምለምንህ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አለ ። ምናልባት ፡ ይህን ፡ የተረፈውን ፡ የርስትህን ፡ እኩሌታ ፡ ለመሸጥ ፡ ፈቃድህ ፡ ቢሆን ፡ ዋጋውን ፡ ልስጥህ ፡ የተዘጋጀሁ ፡ ነኝና ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ አትሽጥብኝ ። ባለቤቱም ፡ ቀድሞ ፡ የተቀበለውን ፡ የመሬቱን ፡ ዋጋ ፡ አባክኖ ፡ ጨርሶ ፡ ገንዘብ ፡ ቸግሮት ፡ ነበርና ፡ ደስ ፡ አለው ። ስለ ፡ ዋጋውም ፡ ነገር ፡ ወዲያው ፡ ተነጋገሩና ፡ ከተከራከሩ ፡ በኋላ ፤ በመጨረሻው ፡ ተስማሙ ።

እኔ ፡ በዚህ ፡ በመሬቴ ፡ ላይ ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ እየዘራሁ ፤ ባንድ ፡ በኩል ፡ አታክልት ፡ በያይነቱ ፡ እያስተከልሁ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ሠርቼ ፡ ምንም ፡ አላተረፍሁም ። አንተ ፡ ቦታውን ፡ ከእኔ ፡ ተከራይተህ ፡ በየዓመቱ ፡ ክራዩን ፡ ትከፍላለህ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ርስቴ ፡ ነውና ፡ ምንም ፡ አልከፍልበትም ፤ አንተ ፡ ለሠራተኞችህ ፡ በየቀኑ ፡ የሠሩበ

ትን ፡ ሒሳብ ፡ ትሰጣቸዋለህ ። እኔ ፡ ግን ፡ ለአባቴ ፡ አገልጋዮች ፡ የሚበ
ሉትንና ፡ የሚለብሱትን ፡ መስጠት ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፤ ሌላ ፡ ትርፍ ፡ ገንዘብ ፡
አላስብላቸውም ። አንተ ፡ በግማሹ ፡ ርስቴ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሠ
ራኸው ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በሙሉ ፡ ላይ ፡ ነበር ። እኔ ፡ በሦስት ፡ ዓመት ፡
ምንም ፡ ሳላገኝበት ፡ አንተ ፡ በሦስት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ጣጣ ፡
ችለህ ፡ መሬቴን ፡ ለመግዛት ፡ የበቃ ፡ ገንዘብ ፡ ያተረፍኸው ፡ እውነት ፡
በኔ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ሠርተህ ፡ ባፈራኸው ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ከሌላ ፡ ዘንድ ፡
ባገኘኸው ፡ ገንዘብ ፡ ነው ? ብሎ ፡ ባለቤቱ ፡ ተከራዩን ፡ ጠየቀው ። ሰው
ዬውም ፡ ባንተ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ሠርቼ ፡ ባተረፍሁት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መለ
ሰለት ።

እኔ ፡ ስከሥር ፡ አንተ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ያተረፍኸው ፡ ምክንያቱ ፡
ምንድነው ፡ ብሎ ፡ መልሶ ፡ ጠየቀው ። አንተ ፡ ጧት ፡ ስትነሣ ፡ አገ
ልጋዮችህን ፡ ሂዱ ፡ ሥሩ ፡ ብለህ ፡ ትልካቸዋለህ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ጧት ፡ ተነ
ሥቼ ፡ ሠራተኞቼን ፡ ኑ ፡ እንሂድ ፡ እንሥራ ፡ እላቸዋለሁ ፤ ምክንያቱ ፡
ይህ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። ሂዱ ፡ ሥሩ ፡ በማለትና ፡ ኑ ፡ እን
ሂድ ፡ እንሥራ ፡ በማለት ፡ መካከል ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ ልዩነት ፡ አለ ፡
ብሎ ፡ አሁንም ፡ ደገመና ፡ ቢጠይቀው ፡ ልዩነቱማ ፡ አንተ ፡ ጧት ፡
ተነሥተህ ፡ አገልጋዮችህን ፡ ሂዱ ፡ ሥሩ ፡ ብለህ ፡ ትልካቸውና ፡ አንተ ፡
ጨዋታና ፡ ፈንጠዝያ ፡ ወደሚገኝበት ፡ ቦታ ፡ እየሄድህ ፡ ገንዘብህንና ፡
ጊዜህን ፡ በከንቱ ፡ ስታሳልፍ ፤ ትውላለህ ። አገልጋዮችህ ፡ ደግሞ ፡
ጊዜያቸውን ፡ በጨዋታና ፡ በመማገጥ ፡ ያሳልፋሉ ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ ሥራ ፡
አይሠሩ ፤ አንተ ፡ ወደ ፡ ጨዋታ ፡ መሄድህን ፡ ስለሚያውቁ ፡ አንተ ፡
የምትሰጣቸውን ፡ መጥፎ ፡ ምሳሌ ፡ እየተከተሉ ፡ በልባቸው ፡ ስንፍና ፡
ያድራል ። አንተም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ሥራ ፡ መሄዳቸውን ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፤
መሥራታቸውንና ፡ አለ ፡ መሥራታቸውን ፡ አጠገባቸው ፡ ሆነህ ፡ ስለማ
ትመለከት ፡ ልትቈጣጠራቸውና ፡ ልትቈጣቸው ፡ አትችልም ። እነሱም ፡
ምንጊዜም ፡ ቢሆን ፡ የሚበሉትንና ፡ የሚለብሱትን ፡ እንደማትነሣቸው ፡
ያውቃሉና ፡ ሥራው ፡ ቢሠራም ፡ ባይሠራም ፡ ግድ ፡ የላቸውም ።



ስለዚህ፡ ያንተ፡ ጉዳት፡ በሁለት፡ በኩል፡ ነው፡፡ መጀመሪያ፡ አንተ፡ አትሠራም፤ ደግሞ፡ ገንዘብ፡ ስታባክን፡ ትውላለህ፡፡ ሁለተኛ፡ አገልጋዮችህ፡ ምንም፡ አይሠሩ፡ ሰነፎች፡ ናቸው፡፡ ግን፡ አንተ፡ በግድ፡ ቀለባቸውንና ልብሳቸውን፡ ትችላለህ፡፡ አንተ፡ ያልከሠርክ፡ ማን፡ ይከሠር፡፡

እኔ፡ ብትለኝ፡ ግን፡ ጧት፡ በማለዳ፡ ከመኝታዬ፡ ተነሥቼ፡ ኑ፡ እንሂድ፡ እንሥራ፡ ብዬ፡ ሠራተኞቼን፡ ከፊቴ፡ አስቀድሜ፡ እንደ፡ ከብት፡ እየነዳሁ፡ ወደ፡ ሥራ፡ እሄዳለሁ፤ እዚያም፡ ስደርስ፡ ባጭር፡ ታጥቄ፡ በመካከላቸው፡ ሆኜ፡ ስሠራ፡ እውላለሁ፡፡ እነሱም፡ እኔ፡ ስሠራ፡ እያዩ፡ ሊጫወቱ፤ ወይም፡ ሊማግጡ፡ በፍጹም፡ አይችሉም፡፡ የስንፍና፡ ምልክት፡ የሚያሳይ፡ ሠራተኛ፡ ቢኖርም፡ በገንዘቡ፡ እቀጣዋለሁ፡፡ ማታም፡ ሲሆን፡ ሠራተኞቼ፡ ወደ፡ የቤታቸው፡ ሲበታተኑ፡ እኔ፡ ከኋላ፡ ቀርቼ፡ የተበላሸውን፡ አስተካክዬ፤ የተሠራውን፡ ተመልክቼ፡ ሁሉንም፡ በሥርዐት፡ አድርጌ፡ ቈይቼ፡ ወደ፡ ቤቴ፡ እገባለሁ፡፡ እንደዚህ፡ ሠርቼ፡ እኔ፡ ያላተረፍኩ፡ ማን፡ ያትርፍ፡፡ ይኸውልህ፡ «ሂዱ፡ ሥሩ፡ በማለትና፡ ኑ፡ እንሂድ፡ እንሥራ፡» በማለት፡ መካከል፡ ያለው፡ ትልቁ፡ ልዩነት፡ ይህ፡ ነው፡ ብሎ ገንዘቡን፡ ሰጠው፡፡ ባለርስት፡ የነበረው፡ ሰው፡ የመሬቱን፡ ሽያጭ፡ ገንዘብ፡ ይዞ፡ ወደ ፈንጠዝያ፡ ቦታ፡ ሄደ፤ ተከራይቶም፡ የነበረው፡ መሬቱን፡ ገዝቶ፡ ወደ፡ ሥራው፡ ተመለሰ፡፡

* * *

<u>ክፉ፡ ሰው፡፡</u>

በትልቅ፡ ቸርነት፡ ሌሊቱን፡ አንግቶ፡
በጽልመቱ፡ ቦታ፡ ፀሓይን፡ አብርቶ፡፡
ጨለማን፡ በብርሃን፡ ለለወጠ፡ ጌታ፤
ምስጋና፡ ሊያቀርቡ፡ ሊያደርሱ፡ ሰላምታ፤
ወፎች፡ እንኳ፡ ዐውቀው፡ ሲያሰሙን፡ እልልታ፡፡
ክፉ፡ ሰው፡ አእምሮው፡ ያነሰ፡ ከእንስሳ፡
ጧት፡ ከመኝታው፡ ከእንቅልፉ፡ ሲነሣ፡፡

በስመ ፡ አብ ፡ ብሎ ፡ በእጁ ፡ ሳያማትብ ፡
መርዘኛ ፡ ልቡናው ፡ የለት ፡ ግብሩን ፡ ሲያስብ ።
እገሌና ፡ እገሌን ፡ በዚህ ፡ አጣልቼ ፤
እገሌንም ፡ ደግሞ ፡ እንደዚህ ፡ አጥፍቼ ።
እያለ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ሊበድል ፡ ሊጐዳ ፤
የተንኰሉን ፡ ወጥመድ ፡ ቋጥሮ ፡ እያሰናዳ ።
ሲያሴር ፡ ያረፍድና ፡ ሲዶልት ፡ ቈይቶ ፤
ክፋትን ፡ በልቡ ፡ ሰብስቦ ፡ አሰናድቶ ፡
ታጥቆ ፡ ሊፈጽመው ፡ ይሄዳል ፡ ተነሥቶ ፤
ሰውን ፡ ሲያበጣብጥ ፡ ሲያፋጀው ፡ አምሽቶ ።
ክፉ ፡ በመሥራቱ ፡ ተሰምቶት ፡ ደስታ ፤
በልቡ ፡ እየሣቀ ፡ ይመለሳል ፡ ማታ ፤
ወዮ ፡ ያ ፡ ክፉ ፡ ሰው ፡ ለዋለበት ፡ ቦታ ።

* * *

<u>የሠራተኞች ፡ ዋጋ ።</u>

አንድ ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ፡ የሕዝቡን ፡ ጉዳት ፤
ነቅቶ ፡ የሚጠብቅ ፡ በብዙ ፡ ትጋት ።
ከመሳፍንቶቹ ፡ አንዱ ፡ መኰንን ፤
እመንገድ ፡ ላይ ፡ አንዱን ፡ ገበሬ ፡ ምስኪን ።
እየደበደበ ፡ በጥፊ ፡ በጡጫ ፤
እየገፈተረ ፡ ሲመታው ፡ በርግጫ ።
ድንገት ፡ ሲያልፍ ፡ አየና ፡ እንዳላየ ፡ ሆኖ ፡
በጣም ፡ ተቈጥቶ ፡ ደግሞም ፡ በልቡ ፡ አዝኖ ።
ጠብቆ ፡ ሲመጣ ፡ እቤተ ፡ መንግሥቱ ፤
ሊቀጣው ፡ ዐስቦ ፡ በዚህ ፡ በጥፋቱ ።
በሌላ ፡ ምክንያት ፡ ጠራውና ፡ ኋላ ፤
እቤትህ ፡ አትሄድ ፡ ምሳ ፡ እዚሁ ፡ ብላ ።
አለና ፡ ነገረው ፡ ለዚያ ፡ መኰንን ፡
የልፍኝ ፡ አሽከሩንም ፡ ጠራና ፡ በጐን ።



ወጡን ፡ በያንቱ ፡ አድርጋችሁ ፡ አውጡ ፤
ግን ፡ ዕንጀራ ፡ ምንም ፡ በፍጹም ፡ አትስጡ ።
ብሎ ፡ ስላዘዘው ፡ እየደጋገመ ፤
አሽከሩም ፡ ትእዛዙን ፡ ትክክል ፡ ፈጸመ ።
ኋላም ፡ መኰንኑን ፡ ለብቻ ፡ አስጠራና ፡
ምሳህን ፡ በመልካም ፡ ተጋበዝህ ፡ ወይ ፡ ደኅና ?
ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፤
ኩቶ ፡ ያለንጀራ ፡ ወጥ ፡ ይበላል ፡ ወይ ።
ወይ ፡ በመርሳት ፡ ይሁን ፡ ወይ ፡ እኔን ፡ ለመጉዳ ፤
አልተረዳሁትም ፡ ምክንያቱን ፡ እንጃ ።
ወጡን ፡ አሳላፊው ፡ በያይነቱ ፡ አውጥቶ ፤
ያቀርብልኝ ፡ መስሎኝ ፡ ዕንጀራም ፡ አምጥቶ ።
ጓጕቼ ፡ ስጠብቅ ፡ ብቅ ፡ ሳይል ፡ ቀረ ፤
ሳልበላ ፡ ተነሣሁ ፡ ተርቤም ፡ ነበረ ፤
ብሎ ፡ እንደ ፡ ስሞታ ፡ ይህን ፡ ተናገረ ።
ንጉሡም ፡ መልሶ ፡ ይህ ፡ የዕንጀራ ፡ ነገር ፤
እንደዚህ ፡ ማጕደሉን ፡ ዐውቀህ ፡ ስትናገር ።
ድካም ፡ ተቀብሎ ፡ በግብርና ፡ ጣጣ ፤
አርሶ ፡ ዘርቶ ፡ አጭዶ ፡ እህል ፡ የሚያመጣ ።
ገበሬን ፡ በመርዳት ፡ እንደ ፡ መደገፍ ፤
በምን ፡ የተነሣ ፡ ይቀበላል ፡ ግፍ ።
አለና ፡ ጥፋቱን ፡ በዘዴ ፡ አመልክቶ ፤
ገሠጸው ፡ ይባላል ፡ በጣም ፡ ተቈጥቶ ።
ከሀብት ፡ ደረጃ ፡ በቶሎ ፡ ለመድረስ ፡
ከገበሬ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አናጢ ፡ ድረስ ።
ሠራተኛን ፡ ሁሉ ፡ አንደኛውም ፡ ሳይቀር ፤
መርዳት ፡ ይገባናል ፡ መውደድና ፡ ማፍቀር ።
ከስፍና ፡ መሬት ፡ ካፈሩ ፡ ተነሥተን ፤
ከሥልጣኔው ፡ ኮርቻ ፡ ከጫፉ ፡ ላይ ፡ ወጥተን ።
ለመስፋፋትና ፡ ለመመቻቸት ፤
ተድላና ፡ ደስታ ፡ ምቾት ፡ ለማግኘት ።

እንረዳው፡ በጣም፡ መነሻ፡ እርካባችን፡
ሠራተኞች፡ ናቸው፡ መቈናጠጫችን።

* * *

<u>አስተዋይ፡ ተማሪ ።</u>

ብዙ፡ ሕፃናቶች፡ ሰብስቦ፡ ከፊቱ፡
አንድ፡ መምህር፡ ቆሞ፡ ከተማሪ፡ ቤቱ።
በምሳሌ፡ አድርጎ፡ እየዘረዘረ፤
ከፍ፡ ባለ፡ ድምጡ፡ እየተናገረ።
ሰው፡ በእግዚአብሔር፡ አምሳል፡ ስለ፡ ተፈጠረ።
በተመልካችነት፡ ብንመራመር፤
ከእንስሳ፡ ይበልጣል፡ በሁሉም፡ ነገር።
ለው፡ የማይበልጥበት፡ ምንም፡ ነገር፡ የለ፤
እያለ፡ ልጆቹን፡ ሲያስተምራቸው፡ ሳለ።
ምንም፡ ሳያስበው፡ ሳይጠረጥር፡ ከቶ።
ከመካከላቸው፡ አንዱ፡ ልጅ፡ ተነሥቶ፡
አንድ፡ ነገር፡ አለው፡ ብንመለከት፤
እንስሳ፡ ከሰው፡ ልጅ፡ የሚበልጥበት።
በለዎች፡ መካከል፡ ለካራሞች፡ ሞልተው፤
እንስሶች፡ ግን፡ መቼም፡ አይስከሩ፡ ጠጥተው።
አለና፡ ቢናገር፡ ሁሉም፡ እየሣቁ፤
ይህ፡ ነገር፡ እንዴት፡ ነው፡ ብለው፡ ቢጠይቁ።
እውነትም፡ ነገሩን፡ አይቶ፡ ቢገምተው፤
ይህን፡ ለማስረዳት፡ መምህሩም፡ አቃተው።
አወይ፡ በመምህር፡ ላይ፡ ያለበት፡ አባዜ፤
የተማሪ፡ አስተዋይ፡ በጠየቀው፡ ጊዜ።

* * *

<u>ፈ ሪ፡ ጦረኛ።</u>

ዐሥር፡ ዓመት፡ ሙሉ፡ አውሮፓን፡ ረግጦ፤
በገዛበት፡ ዘመን፡ ሁለን፡ አንቀጥቅጦ።
ትልቁ፡ ናፖሊዮን፡ የጦር፡ አለቆቹ፤
የተመሰገኑት፡ እኒያ፡ ኀይለኞቹ።



ባርበኝነት ፡ በኩል ፡ ወደር ፡ የሌላቸው ፤
የሚመከት ፡ ጠፍቶ ፡ ለጀግንነታቸው ።
የአውሮፓን ፡ መንግሥታት ፡ ሁሉን ፡ ያስገበሩ ፤
ሞትን ፡ የሚንቁ ፡ ደፋሮች ፡ ነበሩ ።
ከደካሞች ፡ ጋራ ፡ እንዳይበላ ፡ ሠርቶ ፤
በመካከላቸው ፡ ያለ ፡ ቦታው ፡ ገብቶ ።
በጣም ፡ የሚፈራ ፡ የጥይት ፡ አደጋ ፤
ጦር ፡ በመጣ ፡ ቍጥር ፡ የሚኖር ፡ ሲሠጋ ፤
በጦርነትም ፡ ላይ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ሲዋጋ ።
ግንባሩን ፡ የማይሰጥ ፡ ከመሸሽ ፡ በተቀር ፤
ፈሪ ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ የጦር ፡ ሹም ፡ ነበር ።
ወሪያቸው ፡ ሲነሣ ፡ ፈሪና ፡ ዘመቻ ፤
ለጦር ፡ ጓደኞቹ ፡ ነበር ፡ መተረቻ ።
ይህ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ ተጣልቶ ፤
ሽጉጥም ፡ ተማዝዞ ፡ ተታኵሶ ፡ ተመትቶ ።
ታመመ ፡ ተኛና ፡ የዚያኑ ፡ ዕለት ፡ ማታ ፤
ከሰው ፡ ጋር ፡ ተጣልቶ ፡ ሆዱ ፡ ላይ ፡ ተመታ ።
ጥይቷም ፡ ከሆዱ ፡ ገብታለች ፡ ፈጽማ ፤
ብሎ ፡ ሰው ፡ ሲያወራ ፡ ናፖሊዎን ፡ ሰማ ።
እውነት ፡ በሱ ፡ ፍርሀት ፡ አንሥቶ ፡ አምባጓሮ ፤
ሽጉጥ ፡ ለመማዘዝ ፡ ለመታኰስ ፡ ደፍሮ ።
ዐይኑ ፡ ሲያይ ፡ ተመትቶ ፡ እንደ ፡ ጕበዝ ፡ ሁሉ ፤
ጥይት ፡ ወደ ፡ ሆዱ ፡ ገብታለች ፡ ብትሉ ።
የሚያውቅ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሱን ፡ ፈሪነት ፤
ጨርሶ ፡ አያምንህም ፡ ልንገርህ ፡ በውነት ።
ይልቅስ ፡ ጥይቷን ፡ ከምናምን ፡ ጋራ ፤
ውጧት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወሬውን ፡ አጣራ ።
አሁን ፡ ይህን ፡ ወሬ ፡ ተረት ፡ የመሰለ ፤
አምጥተህ ፡ በከንቱ ፡ ባትነግረኝ ፡ ምን ፡ አለ ። ?
ለጆሮ ፡ ከባድ ፡ ነው ፡ ላሳብ ፡ የረቀቀ ፤
ብሎ ፡ ናፖሊዎን ፡ መሰስ ፡ እየሣቀ ።

* * *

## ሞት ፡ ሁሉን ፡ እኩል ፡ ያደርጋል ።

ሀብታምና ፡ ድኻ ፡ ሞተው ፡ ሲቀበሩ ፤
መቃብራቸውን ፡ ሰዎች ፡ ሲቈፍሩ ።
እጅግ ፡ አርጎ ፡ በጣም ፡ ስለ ፡ ተቃረበ ፤
ሀብታም ፡ ተቈጥቶ ፡ እንዲህ ፡ ተሳደበ ።
ምነው ፡ አንተ ፡ ድኻ ፡ እንደዚህ ፡ ደፈርከኝ ፤
ምንስ ፡ አንተን ፡ ዛሬ ፡ ለማጥቃት ፡ ቢያውከኝ ።
ራቅ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ እኔን ፡ ተመልከተህ ፤
አጠገቤ ፡ እንደዚህ ፡ በጣም ፡ ተጠግተህ ፤
እንዴት ፡ ይገባሃል ፡ ደፍረህ ፡ መተኛት ፤
ተነሥ ፡ ሂድ ፡ አሁንም ፡ ከምትሄድበት ።
ድኻም ፡ መለሰና ፡ እንዲህ ፡ ተናገረ ፤
ዐልጋና ፡ መከዳ ፡ ሲያማርጥ ፡ የኖረ ።
ያንተ ፡ ገላ ፡ ነበር ፡ ያለ ፡ ቦታህ ፡ ገብተህ ፤
የተኛህ ፡ አንተነህ ፡ አሁንም ፡ ተነሥተህ ፤
ያን ፡ የለመድከውን ፡ የምቾቱን ፡ ስፍራ ፤
ፈልግ ፡ እሌላ ፡ ዘንድ ፡ እዚህ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፤
ምን ፡ አምጥቶ ፡ ጣለህ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ከጥንት ፤
ወትሮም ፡ ልማዴ ፡ ነው ፡ መሬት ፡ መተኛት ።
ጕበዝ ፡ አይል ፡ ፈሪ ፡ ድኻ ፡ ባለጠጋ ፤
ሁሉን ፡ አስተካካይ ፡ ሞት ፡ የሙሉ ፡ አደጋ ።

* * *

ራዲያርድ ፡ ኪፕሊንግ ፡ የሚባለው ፡ የእንግሊዝ ፡ ደራሲ ፡ ከዚህ ፡ በታች ያሉትን ፡ የምክር ፡ ቃሎች ፡ ተናገረ ።

## ሰው ፡ ለመሆን ፡ ብትፈልግ ።

በዙሪያህ ፡ የሚገኙ ፡ ሰዎች ፡ ናላቸው ፡ ተናውጦ ፡ አላፊነቱን ፡ ሁሉም ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ሲጥሉብህ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ሳትደነግጥ ፡ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ በርጋታ ፡ ተቀበለው ።

ሰዎች ፡ በጠረጠሩህ ፡ ጊዜ ፡ ልብህ ፡ አይሸበር ። በራስህ ፡ ተማመን ፡ እንጂ ፤ ለምን ፡ ተጠረጠርሁ ፡ ብለህ ፡ ቅርታ ፡ አይግባህ ።



ወደ ፡ ፊት ፡ የሚሆነውን ፡ ነገር ፡ ሳትበሳጭና ፡ ሳትሰለች ፡ በትዕግሥት ፡ ጠብቅ ። የማይረባና ፡ ጥቅም ፡ የሌለው ፡ ነገር ፡ በመከተል ፡ ጕልበትህን ፡ አታባክን ።

ሰዎች ፡ በጠሉህ ፡ ጊዜ ፡ ቂም ፡ አታድርግባቸው ። እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ደግነት ፡ አታብዛ ፤ ወይም ፡ በመለማመጥ ፡ ራስህን ፡ አታዋርደው ።

ምኞትን ፡ ተመኘው ፡ እንጂ ፤ የምኞትህ ፡ ባሪያ ፡ አትሁን ።

ሀሳብን ፡ ዐስበው ፡ እንጂ ፤ ነገርህ ፡ ሁሉ ፡ ዐሳብ ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ አይቅር ።

ደስታና ፡ መከራ ፡ ባገኘህ ፡ ጊዜ ፡ ሁለቱን ፡ በመጠንና ፡ በርጋታ ፡ ተቀበላቸው ፡ እንጂ ፤ በደስታ ፡ ጊዜ ፡ ፈንጠዝያ ፡ በመከራ ፡ ጊዜ ፡ መፍራት ፡ አታብዛ ።

ሕይወትህን ፡ መሥዋዕት ፡ ያደረግህለት ፡ ሥራህ ፡ በፈረሰና ፡ በተናደ ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ክፉ ፡ ፈተና ፡ ተቀብለህ ፡ ተስፋ ፡ ሳትቈርጥ ፡ የጠፋውን ፡ ሁሉ ፡ መልሰህ ፡ ለማቋቋም ፡ በደከመ ፡ መሣሪያ ፡ ለመሥራት ፡ ሳታመነታ ፡ ተነሣ ።

ያለህን ፡ የሌለህን ፡ ገንዘብህን ፡ ሁሉ ፡ አንድነት ፡ አከማችተህ ፡ ስትሠራበት ፡ ሁሉንም ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ስትከሥር ፡ አጣሁ ፡ ከሠርሁ ፡ ብለህ ፡ ቃል ፡ ሳትተነፍስ ፡ አሁንም ፡ ሠርተህ ፡ ለማትረፍ ፡ ከሥር ፡ ጀምረህ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አንድ ፡ ብለህ ፡ ድከም ።

ዐሳብህ ፡ ጕልበትህ ፤ ሥሮችህ ፡ ታከቶዋቸው ፡ በደከሙ ፡ ጊዜ ፡ ልብህ ፡ ብቻ ፡ አልሸነፍም ፡ ብሎ ፡ እንዲበረታቱና ፡ እንዲጠነክሩ ፡ ያስገድዳቸዋል ።

ሙያህን ፡ ለማሳየት ፡ ሕዝብ ፡ ከተሰበሰበበት ፡ ጉባኤ ፡ መካከል ፡ ቀርበህ ፡ ስትናገር ፡ አይደናገርህ ። ከንጉሦችም ፡ ፊት ፡ በደረስህ ፡ ጊዜ ፡ ፍርሀት ፡ ናላህን ፡ አያናውጠው ።

የሚጠሉህ ፡ ጠላቶችህና ፡ ደግሞ ፡ የሚወዱህ ፡ ወዳጆችህ ፡ እንኳን ፡ ቢሆኑ ፡ በበደሉህና ፡ ባሳዘኑህ ፡ ጊዜ ፡ ቍስሉ ፡ ለልብህ ፡ አይሰማው ፡

ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይመንህ ፡ እንጂ ፤ ማንም ፡ ቢሆን ፡ እጅግ ፡ አድርጎ ፡ አለመጠን ፡ አይተማመንብህ ።

ያች ፡ ዳግመኛ ፡ የማትመለሰው ፡ አንዲትዋ ፡ ደቂቃ ፡ ትንሽ ፡ ናት ፡ ብለህ ፡ ሳትንቃት ፡ ስድሳ ፡ ሰኮንድ ፡ መሆንዋን ፡ ዐስበህ ፡ የሚጠቅም ፡

ሥራ ፡ ሳትሠራ ፡ በከንቱ ፡ አታሳልፋት ።

ይህን ፡ ምክር ፡ ተከትለህ ፡ የፈጸምህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መሬት ፡ በመላዋ ፡ በላይዋ ፡ ላይ ፡ ያለውና ፡ መልካሙም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ላንተ ፡ ይሆናል ።

* * *

## <u>አንድ ፡ ሰውና ፡ አንድ ፡ ዝንጀሮ ።</u>

መርምረን ፡ አስተውለን ፡ ተመልከተን ፡ ብናይ ፤
በንስሳም ፡ መካከል ፡ አይጣፋም ፡ አስተዋይ ።
አንድ ፡ የሚመራመር ፡ የዝንጀሮ ፡ ብልኅ ፤
እየተበሳጨ ፡ በንዴትም ፡ በእልህ ።
ባመል ፡ በባሕሪያቸው ፡ እያስቀየሙት ፤
የዱር ፡ ጓደኞቹ ፡ ስላልተስማሙት ።
በዚህ ፡ ባንዋንዋሩ ፡ በጣም ፡ ስላዘነ ፤
ዓለም ፡ በቃኝ ፡ ብሎ ፡ ለብቻው ፡ መነነ ።
አንድ ፡ ሰው ፡ እንዲሁ ፡ እሱም ፡ በበኩሉ ፤
በሰዎች ፡ መካከል ፡ ያየው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ።
ተስፋ ፡ የሚያስቈርጥ ፡ ስለ ፡ ሆነበት ፤
ገንዘብስ ፡ ወዳጅስ ፡ ምን ፡ ያደርጋል ፡ ሀብት ፤
አለና ፡ መንኖ ፡ ሄደ ፡ ወደ ፡ ዱር ፤
ቈፍሮ ፡ እየበላ ፡ ለብቻው ፡ ሲኖር ፤
አንድ ፡ ቀን ፡ ሳያስብ ፡ የድንገት ፡ ነገር ።
ከዝንጀሮው ፡ ጋራ ፡ መንገድ ፡ ተገናኙ ፤
ጓደኛ ፡ ለማግኘት ፡ ለካ ፡ እየተመኙ ።
በየበኩላቸው ፡ ይፈልጉ ፡ ኖሮ ፤
ሰውዬውም ፡ ሣቀ ፡ ደስ ፡ አለው ፡ ዝንጀሮ ።
ኋላም ፡ እየደረ ፡ በጣም ፡ ተዋደዱ ፤
ደግሞም ፡ በፍቅራቸው ፡ እየጠኑ ፡ ሄዱ ።
ይልቁን ፡ ዝንጀሮ ፡ የፍቅሩ ፡ ብዛት ፤
ቀኑን ፡ ሳይዘነጋ ፡ ሳይተኛ ፡ ሌሊት ።
በዚያ ፡ በሚወደው ፡ በወዳጁ ፡ ላይ ፤
ምንም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ተደርጎ ፡ እንዳያይ ።



ነቅቶ ፡ ጓደኛውን ፡ ይጠብቃል ፡ በጣም ፤
ምንም ፡ ነገር ፡ ቢሆን ፡ ከጫካው ፡ አይወጣም ።
እንደዚህ ፡ ሁለቱም ፡ እንደ ፡ ተፋቀሩ ፤
ተስማምተው ፡ ተቀምጠው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ኖሩ ።
አንድ ፡ ቀን ፡ ሰውዬው ፡ ሲቈፍር ፡ ሲለፋ ፤
ሲሠራ ፡ ዋለና ፡ ደከሞት ፡ እንቀላፋ ።
እንቅልፍ ፡ ሲወስደው ፡ ወዳጁ ፡ ዝንጀሮ ፤
ምንም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እንዳይነካው ፡ ደፍሮ ።
ነቅቶ ፡ ሲጠባበቅ ፡ አሰናድቶ ፡ ዱላ ፤
ያቺ ፡ መልከ ፡ ጥፉ ፡ ስምዋ ፡ የተጠላ ።
ዝንብ ፡ የምትባለው ፡ የተከለፈለፈች ፤
ተቅበዝብዛ ፡ መጥታ ፡ ፊቱ ፡ ላይ ፡ ዐረፈች ።
የምትነክሰው ፡ መስሎት ፡ ተናዶ ፡ ዝንጀሮ ፤
ቀስ ፡ ብሎ ፡ አንሥቶ ፡ ዱላውን ፡ ሰንዝሮ ።
በደንቆሮ ፡ ሥራ ፡ ጨፍልቆ ፡ ሊጥላት ፤
ዝንብዋን ፡ ካፍንጫው ፡ ጋር ፡ መታና ፡ ገደላት ።
ከዝንብዋ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ወዳጁ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፤
ያ ፡ ቂሉ ፡ ዝንጀሮ ፡ መች ፡ ተመለከተ ።
ኋላ ፡ ደም ፡ ቢበዛ ፡ በጣም ፡ ደነገጠ ፤
ከዚያም ፡ ሬሳውን ፡ እያገላበጠ ።
ትንፋሹን ፡ ቢያዳምጥ ፡ ልቡን ፡ ቢዳብስ ፤
ጭራሽ ፡ የለበትም ፡ ትንፋሽና ፡ ነፍስ ፤
ዱላው ፡ ትልቅ ፡ ኖሮ ፡ የማያላውስ ፤
ያ ፡ ያልታደለ ፡ ሰው ፡ ቃል ፡ ሳይተነፍስ ፤
ድርቅ ፡ ብሎ ፡ ሞትዋል ፡ ሳይንቀሳቀስ ።
እቶ ፡ ዝንጀሮ ፡ ግን ፡ ብልኅነታቸው ፤
ሳይጠቅማቸው ፡ ቀረ ፡ ለዚህ ፡ ጥፋታቸው ።
የወዳጅ ፡ ደንቆሮ ፡ ብርቱ ፡ ነው ፡ መዘዙ ፤
እጠቅማለሁ ፡ ብሎ ፡ ይጐዳል ፡ በብዙ ።
ከደንቆሮ ፡ ወዳጅ ፡ ብልኅ ፡ ጠላት ፤
ይሻላል ፡ ተብሏል ፡ ጥንቱን ፡ ሲተረት ።

* * *

## የፈላስፎች ፡ ንግግር ።

ሀብታም ፡ ይደኸያል ፡ ሐኪምም ፡ ይሞታል ፤
ጐበዝ ፡ ይሸነፋል ፡ ብልኅ ፡ ይሳሳታል ፤
የበራውም ፡ ጠፍቶ ፡ የሠሩት ፡ ይፈርሳል ፤
የቆመውም ፡ ወድቆ ፡ የሣቀ ፡ ያለቅሳል ።
ጌጥም ፡ ሆነ ፡ ጥበብ ፡ ውበት ፡ ሆነ ፡ ክብርም ፤
ያማረበት ፡ ነገር ፡ ማስቀየሙ ፡ አይቀርም ።

*

ፍሬ ፡ መሬት ፡ ወድቆ ፡ ከዋለ ፡ ካደረ ፤
ሰው ፡ ገንዘብ ፡ አግኝቶ ፡ መክበር ፡ ከጀመረ ።
የመጣ ፡ ነውና ፡ ቀድሞውን ፡ ከጥንት ፤
ሁለቱም ፡ አይድኑ ፡ ከመበላሸት ።

*

የሰዎችን ፡ ጠባይ ፡ የተመራመረ ።
አንድ ፡ ፈላስፋ ፡ ሊቅ ፡ እንዲህ ፡ ተናገረ ።
በጣም ፡ በማስተዋል ፡ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፤
ስመለከታቸው ፡ የሰውን ፡ ልጆች ።
እያጣሁባቸው ፡ ግብሩ ፡ እሚመስገን ።
እንቃቸው ፡ ጀመር ፡ እጅግ ፡ አለመጠን ።

*

የደንቆሮ ፡ መንፈስ ፡ ምንኛ ፡ ታደለ ።
ብልጥነት ፡ አላጣም ፡ ጅል ፡ እየመሰለ ።
እንኳን ፡ መጽሐፍ ፡ ማንበብ ፡ ፊደል ፡ ሳያጠና ፤
ሁሉንም ፡ ያወቀ ፡ ይመስለዋልና ፤

*

የሊቅ ፡ ሰው ፡ መከራ ፡ የብልኅ ፡ አባዜ ፤
ሲጨነቅ ፡ መኖር ፡ ነው ፡ ባሳብ ፡ በትካዜ ።
አቶ ፡ ዐሳበ ፡ ቢስ ፡ ይተኛል ፡ ዝም ፡ ብሎ ፤
ከትራሱ ፡ ጋራ ፡ ዐሳቡን ፡ ጠቅሎ ።

*



ዞራትና ፡ ትዕቢት ፡ የሞሉት ፡ እናት ፤
ሰይፍና ፡ ጐራዴ ፡ የመቱት ፡ አንገት ።
አይገላግሉም ፡ እንዲህ ፡ በቀላሉ ፡
እመሬት ፡ ላይ ፡ ወድቀው ፡ ሳይንከባለሉ ።

*

ገንዘብ ፡ መፈጠሩ ፡ ለሰው ፡ አገልጋይ ፤
ሆኖ ፡ ሊሠራበት ፡ አልነበረም ፡ ወይ ።
አሁን ፡ ግን ፡ መስገብገብ ፡ በጣም ፡ ስለ ፡ በዛ ፤
ሰው ፡ ባሪያ ፡ እየሆነ ፡ ለገንዘብ ፡ ተገዛ ።

*

የሐሰት ፡ ወገኖች ፡ ተመችን ፡ እያሉ ፤
ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አድመው ፡ እየተማማሉ ።
እውነትን ፡ ካለም ፡ ላይ ፡ ሊያጠፉዋት ፡ ተነሡ ፤
እውነት ፡ ግን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ መከታ ፡ ለነሱ ።
ታግላ ፡ እያሸነፈች ፡ ስትኖር ፡ ረግታ ፤
ጠላቶችዋ ፡ ሁሉ ፡ በሱዋ ፡ ጥፋት ፡ ፈንታ ።
አንድ ፡ ባንድ ፡ ወድቀው ፡ እየተሰበሩ ፡
ከስማቸው ፡ ጋራ ፡ ሁሉም ፡ ጠፍተው ፡ ቀሩ ።

*

ባለም ፡ ላይ ፡ ተሠርቶ ፡ በብዙ ፡ ጥበብ ፡
ማዕርግ ፡ የሚባለው ፡ የደረጃ ፡ ግንብ ።
በዚህ ፡ በሚያዳግት ፡ ባቀበት ፡ መንገድ ፡
ግማሹ ፡ ሲወጣ ፡ ግማሹ ፡ ሲወርድ ።
ክወደ ፡ ዳር ፡ ቆሞ ፡ ማስተዋሉን ፡ ሳይተው ፡
ምንኛ ፡ ደስ ፡ ይላል ፡ ለተመለከተው ።

*

ብልኅ ፡ አስተዋይ ፡ ሰው ፡ ያለምን ፡ ነገር ፡
ዘልቆና ፡ ጠንቅቆ ፡ የሚመራመር ፡
ትልቅ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ረቂቅ ፡ ምስጢር ።
ብለው ፡ በሹልክታ ፡ አድርገው ፡ ሽፍን ፤
የዚህ ፡ ዓለም ፡ ሰዎች ፡ የሚያወሩትን ፤